# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 353 ነሐሴ 23 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## የሃሳብ የበላይነትን የሚያስቀድም የፖለቲካ ባህል ግንባታ

ፋንታነሽ ክንዴ



በሃሳብ የበላይነት አምኖ የሌሎችን እውነት ከማዳመጥ ይልቅ እኔ ያልኩት ካልሆነ በሚል ግትር አመለካከት ኢትዮጵያን ለዘመናት ዋጋ አስከፍሏታል።

በዚህም ምክንያት በውይይትና ምክክር ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮች አላስፈላጊ ግጭት ሲያስከትሉ ይስተዋላል፡፡ በችግሩ የተነሳ በተለያዩ ጊዜያት በርካታ ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳት ደርሷ፤ እየደረሰም ይገኛል። እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ ሰላሟ የሰፈነባትና ሁለንተናዊ እድገት የተረጋገጠባት ሀገር ለመገንባት የሰለጠነ ፖለቲካ ሥርዓት መገንባት እንደሚገባ ተደጋግሞ ይገለጻል፡፡

ለመሆኑ የሰለጠነ ፖለቲካ ሲባል ምን ማለት ነው? ከዚህ አንጻር በሀገራችን ያለው የፖለቲካ ትርክትና አካሄድስ ምን ይመስላል? ቀጣይ የቤት ሥራችንስ ምን መሆን አለበት? በሚሉ ጉዳዮች ላይ ፖለቲከኛና ምሁራንን አነጋግረናል።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ አባል መብራቱ አለሙ (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ የሰለጠነ የፖለቲካ ባህል በሃሳብ የበላይነት የሚያምን ሥርዓትን ይዟል፡፡ ፖለቲካችን ከምርጫ ቦርድ ሕጋዊ እውቅና አግኝተው ሕዝባቸውንና ደጋፊዎቻቸውን በሃሳብ የሚያነቁበት በሃሳብ የበላይነት የሚያምኑበት በምርጫ ሥርዓት

የሃሳብ የበላይነትን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








## “አየር መንገዱ ለበረራ ደህንነትና ለደንበኞች አገልግሎት ቅድሚያ ሰጥቶ የሚሠራ ተቋም ነው"

- አቶ መስፍን ጣሰው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለበረራ ደህንነትና ለደንበኞች አገልግሎት ቅድሚያ ሰጥቶ የሚሰራ ተቋም ነው ሲሉ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን ጣሰው ገለጹ።

አቶ መስፍን ጣሰው እንደገለጹት፤ አንድ አየር መንገድ በስኬታማነት ሊቀጥል የሚችለው ለደንበኞች አገልግሎት ትኩረት ሰጥቶ ሲሠራ ነው።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪና ተመራጭ ሆኖ እንዲቀጥል የደንበኞችን ፍላጎት የማሟላት፣ የበረራ ደህንነትን የማስጠበቅ እና የላቀ አገልግሎት የመስጠት ሥራን ይሠራል ያሉት አቶ መስፍን፤

“አየር መንገዱ ለበረራ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ለኑሮ ውድነት የተበጀ ልጓም

ታደሠ ብናልፈው

በአዲስ አበባ ከተማ የገበያን ውል ለመያዝ ይቸግራል። አንዳንዴ በሰዓትና በደቂቃ ውስጥ የሸቀጦች ዋጋዎች ይወጣሉ ይወርዳሉ፡፡ ነጋዴዎች በሀገር ውስጥ ጥንቅቅ ብለው ለሚመረቱ ምርቶች ሳይቀር ውጫዊ ምክንያት ሲያስተጋቡ ይሰማሉ፡፡

በገበያው በመዋዠቅ ልጓም አልባ የሆነውን የኑሮ ውድነት ለመቀነስና ገበያውን ለማረጋጋት ከተማ አስተዳደሩ የተለያዩ አማራጮችን እየተጠቀመ ይገኛል፡፡

ከሚጠቀማቸው የገበያ ልጓም መግሪያ አንዱ ሸማች ማኅበራትን ማጠናከር ላይ ያተኩራል፡፡ የሸማች ማኅበራት ሲጠናከሩ የግብርና ምርቶችን ከየማሳው በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ በማስገባት ለማህብረሰቡ በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ ማድረግ እንደሚችሉ ይታመናልና ነው፡፡

ሸማች ማኅበራት ከግብርና ምርቶች ባሻገር የኢንዱስትሪ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ እና ቀጥተኛ የንግድ ትስስር በመፍጠር የዋጋ ንረት የሚያስከትሉ ደላላዎችን ከመስመር በማስወጣት የኑሮ ውድነትን በማረጋጋት ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡

በአዲስ አበባ እየተሠራ የሚገኘው በሸማች ሥጋ ቤቶች እንዲሁም በ132 የሰንበት ገበያ ቦታዎች የተለያዩ



ፓስተር ፈለቀ ሞላ





መቶ አለቃ ታረቀኝ ለማ

ምርቶችን ለግብይት በማቅረብ ነዋሪዎችን ከተጨማሪ ወጪ እና ከዋጋ ንረት የመታደጉ ሥራ እንደ አንድ አብነት የሚቀርብ ነው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ሀብተየስ ዲሮ እንደሚሉት፤ በመዲናዋ እየተከሰተ ያለውን የምርት የዋጋ ግሽበት ለማረጋጋት በሸማች ኅበረት ሥራ ማኅበራት ከዚህም እልፍ ያሉ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡

ማኅበራት በቂ የሆነ ምርት የማከማቸትና በተመጣጣኝ ዋጋ ለማህበረሰቡ የማቅረብ ሥራ መሥራቱ የኑሮ ውድነትን በማረጋጋት ረገድ ትልቅ የሚባል ሚና እየተጫወተ ነው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረት ሥራ ኮሚሽን ብልሹ አሠራርንና ሌብነትን ማስወገድ የቻለ ተቋማዊ ለውጥ ማድረጉን የሚያነሱት ምክትል ኮሚሽነር ሀብተየስ፤ ለውጡም ፍትሐዊ አገልግሎት እንዲያድግ በማድረግ ገበያውን እያረጋጋ እንደሚገኝ ያነሳሉ፡፡

ለኑሮ ውድነት... ወደ ገጽ 8 ዞሯል




# የግንዛቤ እጥረት የሚስተዋልበት የወሊድ ክትትል አገልግሎት

**ማህሌት ብዙነህ**

በኢትዮጵያ በዓመት ወደ 14 ሺህ የሚጠጉ እናቶች ከእርግዝና ጋር በተያያዘ በሚከሰቱ የጤና ችግሮች ህይወታቸውን እንደሚያጡ መረጃዎች ያሳያሉ።

እ.ኤ.አ በ2017 በተባበሩት መንግሥታት በወጣው ሪፖርት እንደሚያሳየውም በየዓመቱ በዓለማችን 295 ሺህ የሚሆኑ እናቶች ከእርግዝና፣ ወሊድና ድህረ ወሊድ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ይሞታሉ። ከእነዚህም ውስጥ 94 በመቶ የሚሆኑት የእናቶች ሞት በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ውስጥ ነው።

የእናቶች ሞት በእርግዝና ጊዜ ወይም ከወሊድ በኋላ ከእርግዝና ጋር ተያይዘው የሚከሰቱትን የጤና ችግሮች ወይም በእርግዝናው ምክንያት ሊባባሱ በሚችሉ ብሎም በህክምና አገልግሎት ችግር ምክንያት ሊከሰት ይችላል፡፡

በእርግዝና እና ወሊድ ጊዜ የሚከሰቱትን የጤና ችግሮች ለመቅረፍም በዋነኝነት የቅድመ የወሊድ እና የድህረ ወሊድ ክትትክ አገልግሎት በትክክለኛ ጊዜ እንዲሁም ብቁ በሆኑ የጤና ባለሙያዎች መሰጠት አለበት።

የእናቶችን ሞት ለመቀነስ ጤናማ የእርግዝና ጊዜ ማሳለፍ አስፈላጊ ቢሆንም በአብዛኛው በሀገራችን ማህበረሰቦች ዘንድ የቅድመ ወሊድና ድህረ ወሊድ ክትትሎችን በጤና ማዕከላት ውስጥ የመከታተል ባህል ዝቅተኛ ነው፡፡

ታዲያ ለዚህም ዋናው መንስኤ የግንዛቤ እጥረት በመሆኑ ስለ እናቶች የጤና ክትትል አስፈላጊነት በተለያየ መልኩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል፤ እየተሠሩም ነው፡፡

በጤና ሚኒስቴር ብሄራዊ የእናቶች ጤና ፕሮግራም አስተባባሪ ሲስተር ዘምዘም መሀመድ እንደሚገልጹት፤ እናቶች ነፍሰጡር መሆናቸውን ከባለቤታቸው ውጭ አይናገሩም፡፡ በጤና ተቋማትም ክትትልም የማድረግ ባህላቸው ዝቅተኛ ነው፡፡

ይህም በዋነኝነት ከግንዛቤ እጥረት እና ከአመለካከት ክፍተት የተነሳ የሚፈጠር በመሆኑ ከዚህ አይነት ባህል ውስጥ የምንወጣበት መንገድ መፈጠር አለበት ይላሉ፡፡

በመሆኑም ነፍሰጡር እናቶችን ተሳታፊ ያደረጉ አዝናኝና አስተማሪ መርሀ ግብሮች መዘጋጀታቸው በቂ ግንዛቤ በመፍጠር እናቶች ወደ ጤና ተቋማት ለመምጣት እንዲወስኑ በማድረግ በኩል ፋይዳው ትልቅ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡




አቶ ሳሙኤል አበራ



ሲስተር ዘምዘም መሀመድ

ነፍሰጡር እናቶችን በማሳተፍ የሚሠሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እናቶች የጤና ክትትል እንዲያደርጉ መንገድን የሚያመላክት መሆኑን በመጥቀስ፤ መሰል መርሀ ግብሮች አባቶችን የሚያሳትፉበት ዕድል ቢፈጠር የተሻለ ውጤት ለማምጣት እንደሚረዳ አመላክተዋል፡፡

የቅድመ ወሊድ ክትትል አንዲት እናት ባረገዘች በ12 ሳምንት ወይም 3 ወር ጊዜ ውስጥ ክትትል ማድረግ መጀመር እንደሚኖርባት ጠቅሰው፤ በዚህም የሥነ-ምግብ እና ምክር አገልግሎት፣ የጤና ምርመራ፣ የክትባት፣ የምክር አገልግሎት በመስጠት በእርግዝና ወቅት ጥሩ አቋም እንዲኖራት የሚሠራ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

በፊት አራት ጊዜ ብቻ ይሰጥ የነበረው የቅድመ ወሊድ ክትትል አሁን ስምንት እና ከዚያ በላይ የተደረገ ሲሆን፤ ተገቢውን እንክብካቤ በማድረግ የእናቶችና ጨቅላ ሕፃናት ሞት በመቀነስ በኩል የበለጠ ውጤት እንዲገኝ የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

ሲስተር ዘምዘም እንደሚገልጹት፤ ሚኒስቴሩ ሁሉም እናቶች ባሉበት ቦታ የሚመጥናቸውን አገልግሎቶችን ተደራሽ ለማድረግ የሰለጠነ ባለሙያ ለማብቃት፣ ግብአት ማሟላት፣ የጤና ተቋማትን ማስፋፋት እየተሠራ ይገኛል።

የጤና ተቋማት ተደራሽ ለማድረግም በማይቻልባቸው አካባቢዎች ተንቀሳቃሽ የጤና እና ሥነምግብ ባለሙያ ቀጥሮ አገልግሎት እየተሰጠ ነው፡፡

የቅድመ እርግዝና፣ ቅድመ ወሊድ እና ድህረ ወሊድ የጤና አገልግሎት በጤና ተቋም እንዲያገኙ ማስቻል መጨረሻው ጤናማ እናትነት የሚቋጭ ነው የሚሉት አስተባባሪዋ፤ ሁሉም እናቶች ይህንን በመገንዘብ ተሳትፎአቸውን ሊያጠናክሩ ይገባል ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

በዘርፉ መርሀ ግብሮችን የሚያዘጋጀው የታዋቂ ኢቨንትስ ሥራ አስኪያጅ አቶ ሳሙኤል አበራ በበኩላቸው፤ የነፍሰጡር እናቶች የጤና ክትትል ግንዛቤን የማሳደጉ ዓላማ በሀገሪቱ በስፋት እየተስተዋለ የሚገኘውን የእናቶች ህይወት ማለፍን ለመቀነስ ነው፡፡

በግንዛቤ ማስጨበጫው ነፍሰጡር እናቶች የሚሳተፉበት የነፍሰጡር እናቶች የቁንጅና ውድድር እንዲካሄድም ይደረጋል፡፡

ውድድሩ ነፍሰጡሮች ምቾታቸው ተጠብቆ ጊዜ እንዲያልፍ ከማድረግ በተጨማሪ ለተለያዩ ስሜቶች ተጋላጭ የሆነውን የእርግዝና ጊዜያቸውን በተዝናኖት የሚያሳልፉበት መሆኑንም ጠቅሰዋል፡፡




ፎቶ - ሀዲስ አብርሃ

አቶ ጉዮ ዋሪዮ

# የኦሮሚያ ክልል ለ3 ሺህ 611 የሕግ ታራሚዎች ይቅርታ አደረገ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚዳንት ሽመልስ አብዲሳ ለ3 ሺህ 611 የሕግ ታራሚዎች ይቅርታ ማድረጋቸውን የክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ አስታወቀ፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቶ ጉዮ ዋሪዮ ትናንት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ፤ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚዳንት ሽመልስ አብዲሳ በ2016 ዓ.ም ለ3 ሺህ 611 የሕግ ታራሚዎች ይቅርታ አድርገዋል ብለዋል፡፡

የክልሉ የይቅርታ ቦርድ በየደረጃው ማጣራት አድርጎ ለፕሬዚዳንቱ በማቅረብ ለሕግ ታራሚዎች ይቅርታ ተደርጓል ያሉት አቶ ጉዮ፤ ሕግን መሠረት በማድረግ ለ3 ሺህ 611 የሕግ ታራሚዎች ይቅርታ መደረጉን ጠቅሰዋል።

ይቅርታ ከተደረገላቸው የሕግ ታራሚዎች መካከል 3 ሺህ 334 ወንዶች ሲሆኑ፤ 247 ደግሞ ሴቶች መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

ይቅርታ የተደረገላቸው የሕግ ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው መልካም ባህሪ ማሳየታቸውና ከቅጣቱ መማራቸው በሚመለከተው አካል የተረጋገጠ መሆኑን ገልጸዋል።

ይቅርታው አንድ አራተኛ የእስር ጊዜያቸውን ያጠናቀቁና ልጅ ይዘው በማረሚያ ቤት የሚገኙ እንዲሁም እርጉዝ ሴቶች እንደሚገኙበት አብራርተዋል።

በማረሚያ ቤት ቆይታቸው የታረሙ፣ የአካል ጉዳት አድርሰው ከተጎጂ ቤተሰብ ጋር የታረቁ፣ የእስርና ገንዘብ መቀጮ የከፈሉና ይቅርታ እንዲደረግላቸው በማመልከቻ ለጠየቁ ታራሚዎች ይቅርታ መደረጉን ጠቁመዋል።

በተጨማሪም እድሜያቸው ከ60 ዓመት በላይ የሆኑ አዛውንቶችና የእድሜ ልክ እስራት ተፈርዶባቸው ከ10 ዓመት በላይ በማረሚያ ቤት ያሳለፉ ይቅርታ እንደተደረገላቸው አብራርተዋል፡፡

የማይድን በሽታ የተያዙ ታራሚዎችን ጨምሮ ለተለያዩ ዜጎች በተቀመጠው መስፈርት መሠረት ይቅርታ መደረጉን አስረድተዋል።

እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑና አንድ አራተኛ የእስር ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ ወጣቶችም ይቅርታ እንደተደረገላቸው የገለጹት አቶ ጉዮ፤ ይቅርታ የተደረገላቸው የሕግ ታራሚዎች ወደ ኅብረተሰቡ በሚቀላቀሉበት ጊዜ እድሉን ተጠቅመው በልማታዊና በሰላም ጉዳዮች ላይ በመሳተፍ አርዓያ ሊሆኑ ይገባል ብለዋል፡፡

የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው፣ በተደጋጋሚ ወንጀል የተሳተፉ፣ በዘረፋ፣ በሙስና እና በአስገድዶ መድፈር ወንጀሎች የተሳተፉት በይቅርታው አለመካተታቸውን ገልጸዋል፡፡

የሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ ሽብርተኝነት፣ አደንዛዥ ዕጽ ዝውውር፣ ሀሰተኛ ማስረጃ ማዘጋጀትና መጠቀም ላይ ተሰማርተው ቅጣት የተጣለባቸው ታራሚዎችም በተመሳሳይ በይቅርታ አሰጣጡ ላይ አለመካተታቸውን አብራርተዋል፡፡

# ድርጅቱ በቀን 150 ሺህ መጽሐፍትን የሚጠርዝ ማሽን ወደሥራ አስገባ

**መስከረም ሰይፋ**

አዲስ አበባ፡- በቀን 150 ሺህ መጽሐፍትን የሚጠርዝ ዘመናዊ ማሽን ወደሥራ ማስገባቱን የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት አስታወቀ።

የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ተመስገን ጋሩማ (ዶ/ር) ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በ178 ሚሊዮን ብር ወጪ ከውጭ ሀገር የገባው አዲስ ማሽን በቀን እስከ 150 ሺህ መጽሐፍት የመጠረዝ አቅም አለው።

ማሽኑ በሰዓት ሰባት ሺህ መጽሐፍትን መጠረዝ ይችላል ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ድርጅቱ በሦስት ሽፍት እየሠራ በመሆኑ በቀን ከፍተኛ መጠን ያለው መጽሐፍትን መጠረዝ እንደሚቻል ጠቁመዋል።

በርካታ የትምህርት መርጃ መጽሐፍት ከውጭ ሀገራት እንደሚገቡ ገልጸው፤ አዲሱ ማሽኑ መጽሐፍቱን በሀገር ውስጥ በመጠረዝ የውጭ ምንዛሬ ወጪን ለመቀነስ እንደሚረዳ ተናግረዋል። በተጨማሪ በሀገር ውስጥ የማዘጋጀት ሒደቱ መጽሐፍት ከውጭ ሀገራት ተጓጉዘው ሲገቡ የሚወስደውን ረጅም ጊዜ የሚያሳጥር መሆኑን አስረድተዋል።

በአሁኑ ወቅት ድርጅቱ መጽሐፍትን ለማተም ከትምህርት ሚኒስቴርና ከክልል ቢሮዎች ጋር በጋራ እየሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ነገር ግን ከተቋማት የሚመጣው ትዕዛዝ ከድርጅቱ የማምረት አቅም ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

ዋና ሥራ አስፈጻሚው እንዳስታወቁት፤ ድርጅቱ የመማሪያና የማስተማሪያ መጽሐፍት፣ ደብተር ፣ ሀገራዊና



ተመስገን ጋሩማ (ዶ/ር)

ክልላዊ ፈተናዎች የማተም እንዲሁም ሌሎች የትምህርት ግብዓቶችን በስፋት የማምረት አቅም ቢኖረውም ባለው አቅም ልክ እየሠራ አይደለም።

በመሆኑም የ2017 የትምህርት ዘመን መጽሐፍትን የማሳተም ፍላጎቱ ያላቸው ሁሉ በወቅቱ ወደ ድርጅቱ ቢመጡ አቅርቦት ሳይጓደልና ጊዜ ሳይባክን የትምህርት ዘርፉን መደገፍ የሚያስችል ዝግጁነት አለ ብለዋል።

በተለይ ድርጅቱ በጥራትም ሆነ በዋጋ ከውጭ ከሚገቡ በተሻለ መልኩ ደብተሮች እያመረተና ለገበያ እያቀረበ ቢሆንም ተጠቃሚው ኅብረተሰብ ለሀገር ውስጥ ምርት ያለው አመለካከት ዝቅተኛ በመሆኑ ገበያው ላይ በስፋት ማቅረብ አለመቻሉን ተናግረዋል፡፡

ማህበረሰቡ የድርጅቱ ምርቶችን የመጠቀም ፍላጎት ካሳየ በአሁኑ ሰአት በጥራት የተመረተ በቂ የመማሪያ ደብተር መኖሩንና በመስከረም ወርም በብዛት አምርቶ ወደ ገበያ የማቅረብ አቅም እንዳለው አብራርተዋል፡፡

እንደ ተመስገን (ዶ/ር) ገለጻ፤ ሌላኛው የሀገር ውስጥ የትምህርት ግብአት ምርቶች እንዳይስፋፉ እንቅፋት የሆነው የወረቀት ምርት እጥረት ነው፡፡

የሀገር ውስጥ የወረቀት አምራቾች አቅምና የጥራት ጉዳይ መሻሻል አለበት ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ድርጅቱ የወረቀት ምርትን ከውጭ እያስገባ በመሆኑ ወጪው ከፍተኛ መሆኑን አስረድተዋል።

ድርጅቱ የሀገር ውስጥ የወረቀት ፋብሪካዎችን ምርት ሙሉ በሙሉ መጠቀም አለማቆሙን ጠቁመው፤ ፋብሪካዎቹ የጥራት አይነታቸውን እንዲያሻሽሉ ድጋፍ የማድረግና ጠቃሚ መረጃ የማቅረብ ሥራ መሥራቱን ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ለሀገር ውስጥ ምርቶች ያለውን አመለካከት ማሻሻል ከተቻለና በወረቀት ሥራ ላይ የተሰማሩ የሀገር ውስጥ አምራቾች ምርታቸውን እንዲያሻሽሉ ድጋፍ ቢደረግ ጥራት ያላቸው የትምህርት ግብአቶች በሀገር ውስጥ ማምረት ይቻላል ብለዋል።



## “ምርታማነትን ለመጨመር በጥራት ሥራ አመራር ዕውቅና ውስጥ ማለፍ ይገባል”

**- ወይዘሮ መዓዛ አበራ የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ዋና ዳይሬክተር**

**ነፃነት አሰሙ**

አዲስአበባ፡- ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር በጥራት ሥራ አመራር ዕውቅና አሠራር ሥርዓት ውስጥ ማለፍ ይገባል ሲሉ የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ መአዛ አበራ ገለጹ።

የድርጅቱ ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ መዓዛ አበራ እንደተናገሩት፤ አገልግሎት ሰጪዎችና አምራቾች በጥራት ሥራ አመራር ዕውቅና ውስጥ ማለፋቸው ምርታማነታቸውን ለማሳደግ ይጠቅማቸዋል።

የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የምርት ጥራትና የሥራ አመራር ሥርዓት እውቅና ሰርተፍኬት አገልግሎት እንደሚሰጥ አስታውሰው፤ በሥራ አመራር እውቅና አሠራር ሥርዓት ውስጥ ማለፍ ምርትና ምርታማነትን የሚጨምር፣ ብክነትን የሚቀንስ፣ ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት እንዲኖር የሚያደርግ እና የተገልጋይን እርካታ የሚጨምር መሆኑን አብራርተዋል።

ድርጅቱ አገልግሎቱን የሚሰጠው ዓለም አቀፍ እውቅናና ተቀባይነት ባለው በአይኤስኦ /ISO 17025/ የአሠራር ሥርዓት መሠረት ነው ሲሉ አስረድተዋል።

አሠራሩ በዓለም አቀፍ ሥርዓት ውስጥ ተግባራዊ የሚደረግ በመሆኑ አገልግሎቶችን በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ ሀገራት ተቀባይነት እንዲያገኙ ያግዛል ብለዋል።

ድርጅቱ ዘጠኝ የተደራጁ የፍተሻ ላብራቶሪዎች እንዳሉት የገለፁት ዋና ዳይሬክተሯ፤ በፍተሻ ላብራቶሪዎቹ ምግብ፣ የግብርና ምርትና ግብአቶች፣ ኬሚካሎች፣ ማዕድኖች፣ የኮንስትራክሽን ግብአቶች፣ ቆዳና ጨርቃ ጨርቅ፣ እንዲሁም የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን እንደሚፈትሹ ገልጸዋል፡፡

በ2016 በጀት ዓመት ለአምራቾች፣ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ ለአስመጪና ላኪዎች፣ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የፍተሻ ላቦራቶሪ፣ በሰርተፊኬሽን፣ እንዲሁም በኢንስፔክሽን አማካኝነት ከ23 ሺህ በላይ አገልግሎቶች መስጠቱንም ዋና ዳይሬክተሯ አስታውሰዋል፡፡

የድርጅቱን የፍተሻ ላቦራቶሪዎች በማደራጀት ረገድ በመንግሥት ደረጃ ሰፊ በጀት ተመድቦ በብድርም በእርዳታም አማካኝነት የፍተሻ መሳሪያዎችንና የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት መጠናከራቸውን አንስተው፤ ባለፉት አምስት ዓመታት ሰፊ ሥራዎች ሲሠሩ መቆየታቸውንም ጠቁመዋል።

በተጨማሪ አስገዳጅ የሆኑ ምርቶች በተለይም ከውጪ የሚገቡና ሀገር ውስጥ የተመረቱ ጥራታቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ሰፊ ቁጥጥርና ክትትል እያደረገ እንደሚገኝ አንስተዋል።

አስገዳጅ የሆኑ ምርቶች ብቻ ሳይሆኑ በፍቃደኝነት አምራች ድርጅቶች መጥተው በምርት ጥራት ሰርተፊኬሽንም ይሁን በተለያየ የአሰራር ሥርዓት የጥራት ተስማሚነት ምዝና እያገኙ መሆኑን ተናግረዋል።

ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነፃፀር በጥራትና ተስማሚነት ሥራዎች ላይ የተሻለ ግንዛቤ እየተፈጠረ ይገኛል ያሉት ዋና ዳይሬክተሯ፤ ድርጅቱ እንደ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ካሉ ሌሎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና ከክልሎች ጋር በመቀናጀት ግንዛቤ እየፈጠረ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የምርት ጥራት ሰርተፊኬት ካላቸው ተቋማት ግዢ እንዲፈፅም ለማስቻል የግንዛቤ ሥራ እንደሚሠራ ዋና ዳይሬክተሯ አመላክተዋል።

# ከ17 ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ የመንገድ ጥገና እና ግንባታ ሥራ በመላ ሀገሪቱ ይከናወናል

**ማህሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ፡- በ2017 በጀት ዓመት ከ17 ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ የመንገድ ጥገና እና ግንባታ ሥራ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማከናወን ማቀዱን የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የኮሙኒኬሽን ሕትመት ቡድን መሪ አቶ ተወዳጅ መልካሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተያዘው በጀት ዓመት ከ17 ሺህ 938 ኪሎ ሜትር በላይ የመንገድ ጥገና እና ግንባታ ሥራ ለማከናወን ታቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡

ከተጠገነው የመንገድ ግንባታ እና ጥገና ሥራ ውስጥ 762 ኪሎ ሜትር ያህሉ የአዳዲስ መንገዶች ግንባታ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በተጨማሪም 314 ኪ.ሜ የነባር መንገዶች ደረጃ ማሻሻል፣ 15 ኪ.ሜ የነባር መንገዶችን የማጠናከር ሥራ እንደሚሠራ ተናግረዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ ከባድ፣ መደበኛ እና ወቅታዊ የመንገድ ጥገናዎች እንደሚካሄዱ ያስታወሱት አቶ ተወዳጅ፤ 126 ኪ.ሜ የመንገዶች ከባድ ጥገና፣ 810 ኪ.ሜ የመንገዶች ወቅታዊ ጥገና እና 13 ሺህ 600 ኪ.ሜ የመንገዶች መደበኛ ጥገና ለማከናወን እቅድ መያዙን አስታውቀዋል፡፡

አቶ ተወዳጅ እንደገለጹት፤ በአሁኑ ወቅት ከባድ፣ መደበኛ እና ወቅታዊ ጥገናን ጨምሮ በመላው ሀገሪቱ ከ300 ፕሮጀክቶች በላይ እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ ለመንገዶች ጥገና ከመንገድ ፈንድ ዘጠኝ ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር መመደቡንም አስታውቀዋል፡፡

በዘርፉ ለሚስተዋሉ የአፈፃፀምና ተያያዥ ችግሮች ጠንካራ አቅም ያላቸው የሥራ ተቋራጮች ውስን መሆናቸውን ተከትሎ በመስኩ ያለው ውድድር በሚፈለገው ደረጃ አለመሆን፣ የዲዛይን ጥራት መጓደል እና የፕሮጀክት ማኔጅመንት ክፍተቶች እንዲሁም የወሰን ማስከበር ችግሮች የዘርፉ ተግዳሮቶች መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

እንዲሁም የግንባታ ግብዓቶች እጥረት እና ዋጋ ንረት፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረት፣ ኢንዱስትሪው በበቂ ደረጃ በምርምር አለመደገፉ፣ ልምድና ብቃት ያለው ባለሙያ እጥረትና የስነምግባር ችግር፣ አጠቃላይ የአቅም እና ከአሠራር ሥርዓት ጋር የተያያዙ ክፍተቶች የሚጠቀሱ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

የእነዚህ ችግሮች በስፋት መስተዋልም የመንገድ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ፣ በጀት እና የጥራት ደረጃ እንዳይጠናቀቁ ከማድረግ ባለፈ በዘርፉ በየጊዜው እየጨመረ የመጣ የዋጋ ንረት እንዲከሰት አድርጓል ብለዋል፡፡

በመሆኑም በ2017 በጀት ዓመት የግንባታ ፕሮጀክቶችን በጥራት፣ በወቅቱ እና በብቃት ተግባራዊ ለማድረግ በግንባታ ሂደት ላይ እና ግንባታቸው ለዘገየ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ማሻሻያ ስትራቴጂ ቀርፆ ተግባራዊ ማድረግ፣ የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን ደረጃ በደረጃ የማስጀመር ሥራ ይሠራል ሲሉ አቶ ተወዳጅ ተናግረዋል።

# ከሀሎማ ወደ ሎጎ ሐይቅ ይገባ ከነበረው ደለል 65 በመቶውን ማስቀረት ተችሏል

**አዲሱ ገረመው**

ወረባቦ፡- ባለፉት ዓመታት በደቡብ ወሎ ዞን ወረባቦ ወረዳ በተከናወኑ የችግኝ ተከላ መርሀ ግብሮች ከሀሎማ ተፋሰስ ወደ ሎጎ ሐይቅ ይገባ ከነበረው ደልል 60 በመቶውን ማስቀረት እንደተቻለ ተገለጸ፡፡

በደቡብ ወሎ ዞን ወረባቦ ወረዳ 02 ቀበሌ የተፈጥሮ ሀብት ባለሙያ አቶ አያሌው ሀሰን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአረንጓዴ ዐሻራ ሳይት በሆነው የሀሎማ ተፋሰስ ላይ ባለፉት ዓመታት በተከናወነው የችግኝ ተከላ ሥራ የሎጎ ሐይቅን ከደለል መታደግ ተችሏል፡፡

ሀሎማ የተሰኘውና በወረባቦ ወረዳ ውስጥ የሚገኘው አካባቢ የሐይቁ ዋና ተፋሰስ መሆኑን የገለጹት አቶ አያሌው፤ በተለይም ሐይቁን ከደለል ለመታደግ በስፍራው የተለያዩ የልማት ሥራዎች ሲሠሩ መቆያታቸውን ጠቅሰዋል፡፡

በዚህም ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር ጥናት በማድረግ የደለል መነሻ የሆነውን ሥፍራ በማልማት ሐይቁን ከደለል መከላከል በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ ተደጋጋሚ የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች ተከናውነዋል ብለዋል፡፡

አቶ አያሌው እንዳሉት፤ ወደ ሐይቁ የሚገባው ደለል 60 በመቶ ያህሉ ከተፋሰሱ የሚነሳ ነው፡፡ ሐይቁን ከደለሉ ለመታደግ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ የደን ችግኞችንም በብዛት መትከል ተችሏል፡፡

በሀሎማ ተፋሰስ ችግኞችን መትከል ከተጀመረ ወዲህ በረሃማነት እየቀነሰ መጥቷል ያሉት ባለሙያው፤ የአየር ንብረት ለውጡ እየተስተካከለ መገኘቱን አንስተዋል፡፡

በተከታታይ ዓመታት የተሠራው የችግኝ ተከላ ሥራ አፈርን ከመሸርሸር መታደግ ከመቻሉም በላይ የእንስሳት መኖን በአግባቡ ማግኘት ማስቻሉንም አስገንዝበዋል፡፡

ደለሉን ለመታደግና አፈር እንዳይሸረሸር በተተከሉ ችግኞች አማካኝነት ከ65 በመቶ በላይ የአፈር ደለል ከሀሎማ ወደ ሐይቁ እንዳይገባ ተደርጓል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ አያሌው ገለጻ፤ የአካባቢው ማህበረሰብ የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሀ ግብርን ጨምሮ በተለያዩ ጊዜያት ችግኞችን ሲተክል ቆይቷል፡፡ በአካባቢው የዘንድሮው የአረንጓዴ ዐሻራ ችግኝ ተከላ ፕሮግራም 81 ነጥብ 23 ሄክታር በችግኝ ለመሸፈን እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው፡፡ በዚህም 90 ሺህ ችግኞች ይተከላሉ፡፡

በተፋሰሱ የተተከሉ የችግኝ ዝርያዎች እንደ ወይራ፣ ጽድ፣ ግራብሊያ፣ ባህር ዛፍና መሰል የደን ዛፎች እንዲሁም ሌሎች የፍራፍሬ ተክሎችና ቡናን ያከተተ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የደቡብ ወሎ ዞን ግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ አሕመድ ጋሎ በበኩላቸው፤ በዞኑ ችግኝ የሚተከልባቸው ሥፍራዎች የአፈር ደለልን ለመከላከል የሚያስችሉ፤ ለፍራፍሬና ደን ልማት የሚያገለግሉና የአፈር ለምነትን የሚጨምሩ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ሀሎማ ተፋሰስ የሐይቅ ዳር በመሆኑ ደለሉን ለመከላከል አካባቢው ለችግኝ ተከላ ልማት ተመርጦ እንዲለማ እየተደረገ ይገኛል ብለዋል፡፡

ሎጎ ሐይቅ በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ከደሴ ከተማ በስተ ሰሜን አቅጣጫ 30 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ የቱሪስት መስህብ ሥፍራ ነው፡፡

ዜና

# የሃሳብ የበላይነትን የሚያስቀድም...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ስልጣን የሚይዙበት የፖለቲካ ሥርዓት ነው፡፡

ይህም ከኋላ ቀር አስተሳሰብ በተለየ መልኩ ከብሽሽቅና እኔ አውቅልሃለሁ ከሚል አመለካከት የጸዳ መሆኑን የሚጠቅሱት ዶክተር መብራቱ፤ ሁሉም አለኝ የሚለውን ሃሳብ ይዞ ይቀርባል፡፡ ማህበረሰቡም ይበጀኛል የሚለውን ሃሳብ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የሚመርጥበት እድል ይፈጠርለታል ይላሉ፡፡

ከፉክክርና ጥላቻ ይልቅ በመቀራረብና በመነጋገር ልዩነቶችን አክብሮ በሚያግባቡ ጉዳዮች ላይ በትብብር መሥራት ሌላኛው የሰለጠነ ፖለቲካ መገለጫ ነው የሚሉት የሥራ አስፈጻሚ አባሉ፤ የፖለቲካ ልዩነታችንን ከሀገር ነጥሎ በማየት ለሀገር ደህንነትና ልማት ቅድሚያ ሰጥቶ መሥራትም ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሥርዓት ስንመለከተው መሻሻሎች እንደሚታዩ ይገልጻሉ፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ ምክር ቤት ሥር ተሰባስበው ሃሳባቸውን ያቀርባሉ፡፡ መንግሥትን ጨምሮ ከተለያዩ ባለድርሻዎች ጋርም ምክክርና ውይይትም ማድረጋቸው ይህን የሚያስረዱ ናቸው፡፡ አሁን ላይ የተጀመረው ሀገራዊ ምክክርም የዚህ አካል ተደርጎ ሚወሰድ ነው ይላሉ፡፡

ይሁን እንጂ አንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ የምምክር ልምዱ በውል ያላደገበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ ዛሬም ድረስ በትጥቅ ትግል ወደ ስልጣን ለመምጣት የሚያስቡ አካላት አሉ፡፡ ይወክለኛል የሚሉትን አካል በመምረጣቸውም የሚዋከቡና ከሥራ እስከመባረር የሚያደርስ እንግልት የሚያጋጥማቸው ዜጎች መኖራቸውንም ይጠቅሳሉ፡፡

ሀገር የምታድገው ፖለቲካችን ሲሰክን ነው የሚሉት ዶክተር መብራቱ፤ የዲሞክራሲ ባህል ግንባታ ላይ ትልቅ ሥራ መሥራት ይጠበቅብናል፡፡ በተለይ በታችኛው የመንግሥት መዋቅር ላይ የሚታዩ ጉድለቶችን ለመቅረፍ መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ ይናገራሉ፡፡

የፖለቲካ ምህዳሩ ቢጠብ እንኳን ሌሎች አማራጮችን ማየት እንጂ ግጭትና ጦርነትን ምርጫ ማድረግ የለብንም የሚሉት ፖለቲከኛው፤ በሃሳብ የበላይነት የሚያምን ማህበረሰብና የፖለቲካ ሥርዓት መገንባት ደግሞ ለመንግሥት ብቻ የሚተው ሳይሆን ተፎካካሪ ፓርቲዎችና ሌሎችም ባለድርሻ አካላትም የየድርሻቸውን ኃላፊነት መወጣት እንዳለባቸው ይጠቁማሉ፡፡

የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ አቶ ጥላሁን ሊበን በበኩላቸው እንደሚያስረዱት፤ የሀገራችን የፖለቲካ ሁኔታሴራ የበዛበትና ብሽሽቅ ላይ ያተኮረ ነው፤ ይህም ሀገራዊ እሴቶቻችንን ያላገናዘበና ሕዝባችንንም የማይመጥን ነው፡፡

የትኛውም ሀገር ላይ ችግሮች አሉ ያሉት ምሁሩ፤ በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ዛሬም ድረስ ችግሮችን ለመፍታትና ስልጣን ለመያዝ የትጥቅ ትግልን አማራጭ ማድረግ የሚያሳዝን ነው፡፡ ይህን ኋላቀር የፖለቲካ ባህል መቀየርና ችግሮችን በሰለጠነ መንገድ በውይይትና ንግግር የመፍታት ባህላችን ሊዳብር ይገባዋል ይላሉ፡፡

ችግሮቻችንን ተነጋግረን መፍታት ባለመቻላችን በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ዛሬም ድረስ ጦርነት ውስጥ እንደምትገኝ የሚጠቅሱት አቶ ጥላሁን፤ ይህም ሕዝባችን ላይ ከሚያደርሰው ጉዳት ባለፈ የሀገሪቱን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ላይም የራሱን ተጽእኖ እየፈጠረ ነው፡፡ በመሆኑም ገዢውን ፓርቲ ጨምሮ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ምሁራንና የሀገር ሽማግሌዎች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት መወጣት ይኖርባቸዋል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

መገናኛ ብዙኃንም ከሚያለያዩ ጉዳዮች ይልቅ የሚያቀራርቡና ሰላምን የሚሰብኩ ሥራዎች ላይ አተኩረው መሥራት እንዳለባቸው ይጠቁማሉ።

እንደ ፖለቲከኛው ምሁሩ ማብራሪያ ከሆነ፤ ሀገር የምታድገውና ዘላቂ ሰላም ማስፈን የሚቻለው ሀገራዊ ፖለቲካው ሲሰክን ነው፡፡ ስለሆነም ከብሽሽቅና እኔ አውቅልሃለሁ ከሚል ኋላቀር የፖለቲካ ባህል ወጥተን በሃሳብ የበላይት የሚያምን የፖለቲካ ሥርዓት መገንባት ያስፈልጋል፡፡ ይህን ለማሳካት ደግሞ መንግሥት፣ ተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎችና ሌሎችም ባለድርሻዎች ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

# “አየር መንገዱ ለበረራ ደህንነትና ለደንበኞች...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በመሆኑም ለደንበኞች አገልግሎትና ለበረራ ደህንነት ቅድሚያ ሰጥተን እንሠራለን ሲሉ አስታውቀዋል።

አቶ መስፍን እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ደንበኛ ንጉስ ነው ብሎ የሚያምንና ዓለም አቀፍ የአቪዬሽን ሕግን አክብሮ የሚሠራ ተቋም ነው። የበረራ ደህንነትን የሚጥሱ ደንበኞች በዓለም አቀፍ የአቪዬሽን ሕግ ተጠያቂ ይሆናሉ።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዓለም አቀፋዊ ተቋም እንደመሆኑ መጠን ዓለም አቀፋዊ መስፈርትን ተከትሎ የሚሠራ ተቋም ነው ያሉት አቶ መስፍን፤ በቀጣይም የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን በየጊዜው በመገምገም ደንበኞችን ለማርካት እየሠራ መሆኑንም አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ አየር መንገድ ሊቋረጥ የማይችል አገልግሎት እንደሚሰጥ ገልጸው፤ ደንበኞች ከመነሻ እስከ መድረሻ ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲያገኙ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

የአገልግሎት ጥራት መኖር ለአየር መንገድ ወሳኝ እንደሆነ የገለጹት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ደንበኞች ሳይጉላሉ ያሰቡበት ቦታ የማድረስ እና ዕቃቸው ሳይጠፋ፣ ሳይበላሽና ሳይሰበር ማድረስን መለኪያ አድርገን እየሠራን ነው ብለዋል።

አየር መንገዱ የአገልግሎት ጥራት ደረጃን በማውጣት ደንበኞችን በአገልግሎት አሰጣጥ የማርካት፣ እያንዳንዱ አውሮፕላን በተመደበለት ሰዓት እንዲወጣ የማድረግ፣ የደንበኞች ሻንጣ ጉዳት ሳይደርስበት ከደንበኞች ጋር እኩል እንዲሄድ የማድረግና ሌሎች በርካታ ሥራዎች መሥራቱን አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከሰሞኑ ባጋጠመው ጭጋጋማ የአየር ሁኔታ በሀገር ውስጥ የበረራ መርሀ-ግብር ወደ መቀሌ ተጉዘው የነበሩ ሁለት አውሮፕላኖች ማረፍ ሳይችሉ ወደ አዲስ አበባ መመለሳቸውን አስታውሰዋል፡፡

ሌላ ወደ መቀሌ ለመብረር በዝግጅት ላይ የነበረው አውሮፕላን የአየር ሁኔታው ለደህንነት አስጊ በመሆኑ መብረር አለመቻሉን አንስተው፤ ስለዚህ ወደ ተርሚናል ውረዱና የሚሆነውን ነገር እንነግራችኋለን ሲባሉ አንዳንድ ደንበኞች አንወርድም መሄድ አለብን፤ አውሮፕላኑ ይከስከስ ያሉ በሕግ እንደሚጠየቁ አስታውቀዋል።

ጥቁር አንበሳ
TIKUR ANBESSA


ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ የጥቁር አንበሳ
ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ስለቆዳ በሽታ ማህበረሰቡ ያለው ግንዛቤ እስከምን ድረስ ነው?

**ሶሎሞን በየነ**

ቆዳ የሰውነት ክፍላችን ከውጭው አየር ንብረት የሚከልል ነው። ከውጭው አየር ንብረት ጋር ካለው ሰፊ የመነካካት እድል አኳያ ይበልጥ ለጥቃትና ለበሽታ ተጋላጭ ነው። ታዲያ አንዳንድ ቆዳ ላይ የሚወጡ በሽታዎች የውስጥ ደዌን ወይም ውስጥ ያለን የተደበቀ በሽታን የመጀመሪያ ፍንጭ ሰጭ ምልክት ሊሆኑ ይችላሉ። በአንጻሩ ደግሞ አንዳንድ የቆዳ በሽታዎች የውስጥ ደዌ ህመም ከማስከተል ባለፈ እስከሞት የሚያደርሱ አሉ።

ከዚህ የምንገነዘበው ቆዳ ላይ የሚወጡ በሽታዎች ቆዳ ላይ ብቻ ተወስነው የሚቀሩ አለመሆናቸውን ነው። ይልቁንም የውስጥ ደዌ የሚያስከትሉ አልያም ውስጥ ላይ ያለብንን የተደበቀ ህመም ፍንጭ የሚሰጡ ናቸው። ስለዚህ የቆዳ በሽታ ቆዳ ላይ ብቻ የሚወጣ ችግር ተደርጎ መወሰድ የለበትም። እንዲሁም የቆዳን ችግር በደፈናው ከውበት ጋር ማገናኘት ተገቢ እንዳልሆነ የሚናገሩት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የቆዳና የአባላዘር ህክምና ክፍል ኃላፊና በሙያቸው ደግሞ የቆዳና የአባላዘር ስፔሻሊስት እንዲሁም ከቆዳ ጋር የተያያዙ የቆዳ አለርጂ ሀኪም ዶክተር አሕመድ መሀመድ ናቸው።



ዶክተር አሕመድ መሀመድ፤

እንደ ዶ/ር አሕመድ ገለፃ፤ በተለይ በነጮች ላይ በስፋት የሚስተዋል እንዲሁም በማህበረሰባችንም የሚከሰት “ሜላኖማ” የተሰኘ የቆዳ ካንሰር አለ። ይህ የቆዳ ካንሰር ልክ እንደሌሎች የውስጥ ደዌ የካንሰር አይነቶች ሰዎችን ለከፋ አደጋ እና ሞት የሚዳርግ ነው። እንዲሁም በኛ ሀገር ደግሞ እንደ ሥጋ ደዌ ... የመሳሰሉ ሰውነትን የሚያጎሳቁሉ፣ እንደልብ ተንቀሳቅሶ ለመሥራት የማያስችሉና ለህብረተሰቡ ሸክም እስከመሆን የሚያደርሱ፣ ህመምተኛው ራሱን ከህብረተሰቡ እንዲያገል የሚያደርጉ ልዩ ልዩ የቆዳ በሽታዎች አሉ።

በመሆኑም ህብረተሰቡ የቆዳ በሽታን ከውበት ጋር ብቻ የሚገናኝ ተራ ነገር አድርጎ መመልከት ፈጽሞ የለበትም። የቆዳ በሽታ ጤናን ከማቃወስ ባለፈ ሕይወትን እስከማጣት፣ ከማህበራዊ ሕይወት እስከመገለል፣ ለህብረተሰቡ ሸክም እስከመሆን የሚያደርስ አንድ የጤና ጠንቅ ነው። ስለዚህ ቆዳ ላይ ያልተለመደ ችግር ሲታይ ፈጥኖ ወደ ጤና ተቋም በመሄድ ሀኪም ማማከር ግድ ይላል።

በዘር፣ በኢንፌክሽን፣ በአየር ንብረት ለውጥ፣ በፀሐይ ብርሀን፣ በንክኪ፣ በተለያዩ ነፍሳት፣ በሥራ ዘርፍ ወይም ባህሪ፣ ... ወዘተ የሚመጡ የቆዳ በሽታዎች እንዳሉ የሚናገሩት ዶ/ር አሕመድ፤ ልክ እንደሌሎች ህመሞች ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ የቆዳ በሽታዎች አሉ። ከተላላፊ የቆዳ በሽታዎች አንዱ ሥጋ ደዌ ወይም /Leprosy/ ነው። የአደጉ ሀገራት ባደረጉት ክትትልና ህክምና በሽታው እንዲቀንስና እስከጭራሹ እንዲጠፋ አድርገዋል። አሁን ላይ በዓለም ውስጥ ሥጋ ደዌ የተወሰኑ ሀገሮች ላይ ነው የሚስተዋለው። በአፍሪካ ከሰሀራ በታች ባሉ ሀገራት በሽታው ጎልቶ የሚስተዋል ሲሆን፤ ከነዚህ ሀገሮች ውስጥ አንዷ ኢትዮጵያ ናት። መከላከሉና ግንዛቤ መፍጠሩ ላይ ትኩረት ተደርጎ ከተሠራ ልክ እንዳደጉ ሀገራት በሽታውን ማጥፋት ይቻላል።

ሆኖም በሀገራችን በበሽታው የተጠቁ ሰዎች ላይ የሚደርሰው የማህበራዊ ቀውስ ጠባሳ እስካሁን ድረስ አልጠፋም። በሽታው የተገኘባቸውን ሰዎች የማግለል፣ ህብረተሰቡን እንዳይቀላቀሉ የማድረግ፣ ... ወዘተ በአብዛኛው የህብረተሰባችን ክፍል ይስተዋላል። ነገር ግን በበሽታው የተጠቁ ሰዎች በጊዜ ህክምና ካገኙ መዳን ይችላሉ። እንዲሁም ሥጋ ደዌ በሽታ ከታከመ ህብረተሰቡ ላይ ስለማይተላለፍ፤ በበሽታው የተጠቁ ሰዎችን ያለአግባብ ማግለል ተገቢ አይደለም። ከዚህ ባለፈ ሌሎች የሚተላለፉ የቆዳ በሽታዎችም ታክመው የሚድኑ ናቸው። ከዳኑ በኋላም ምንም አይነት ተጓዳኝ ችግር አያስከትሉም። ስለዚህ መሰል የሚተላለፉ የቆዳ በሽታዎች ላይ በሽተኛውን በማያገል መልኩ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

ሌላው ለምጥ የተሰኘው የቆዳ ችግር በዘርም ሆነ በንክኪ አይተላለፍም። ነገር ግን በማህበረሰቡ ዘንድ ባለው የተዛባ አመለካከት ለምጥ ያለበትን ሰው ማግባት በዘር ከልጅ ወደ ልጅ እንደሚተላለፍ ተደርጎ ይወሰዳል። ወይም ከሰው ወደ ሰው እንደሚተላለፍ ተደርጎ ይሳላል። ይህ ፍጹም ስህተት ነው። ለምጥ ከሰው ወደ ሰው አይተላለፍም።

በመሆኑም ህብረተሰቡ በተለምዶ ያለምንም የሳይንስ መሰረት የሚባለውን ይዞ ወገኑን ከማግለል መቆጠብ ይኖርበታል። ስለአንድ በሽታ ትክክለኛውን መረጃ ከባለሙያ ጠይቆ ከተረዳና የምክር አገልግሎት ካገኘ በኋላ የተዛባውን አመለካከት ማስተካከልና ማረም ይኖርበታል። በአንጻሩ ደግሞ በባለሙያ እንዲያደርግ የተነገሩትን አስፈላጊውን የጥንቃቄ እርምጃዎችን ደግሞ በአግባቡ መተግበር እንዳለበት ያስረዳሉ።

ከዚህ ባሻገር ህብረተሰቡ በሀኪም ያልተረጋገጠ የኮስሞቲክስ ወይም የመዋቢያ ግብዓቶችን (ምርቶችን) መጠቀም ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ያሳሰቡት ዶ/ር አሕመድ፤ በየማህበራዊ ሚዲያው የህክምና ባለሙያ ያልሆኑ ሰዎች ከመሬት ብድግ ብለው “ይህን ቅባት ብትጠቀሙ፣ እንደዚህ፣ እንደዚህ አይነት ነገሮችን አዋህዳቹህ ብትቀቡ፣ ከውጭ ሀገር ያስመጣናቸው ለቆዳ ተስማሚ መዋቢያዎች ወይም መድኃኒቶች አሉ ወዘተ” የሚል ማስታወቂያዎች በስፋት ያስተዋውቃሉ።

ነገር ግን አንድ ሰው ምክርና ትምህርት ለመስጠት በሙያው የሰለጠነ ወይም የተመረቀ መሆን አለበት። ሆኖም በተለይ የማህበራዊ ሚዲያ ተከታይ የሆነው ወጣቱ ክፍል፤ በየማህበራዊ ሚዲያው ባለሙያ ያልሆኑ ሰዎች የሰጡትን ትምህርት ወይም መረጃ ተቀብሎ ተግባራዊ ሲያደርግ ይስተዋላል። በዚህም “ሲጌጡ ሲሉ ይመለጡ” እንደሚባለው በተለይ ወጣቱ ውበት እጨምራለሁ ብሎ እራሱ ላይ ችግር እያመጣ ነው።

እንዲሁም በህክምና የተረጋገጡ እና በሀኪም የሚታዘዙ የውበት መጠበቂያ ምርቶች አሉ። እነዚህ መድሃኒቶች የጎንዮሽ ጉዳት የላቸውም። በአንጻሩ ግን በህክምና ያልተረጋገጡ የውበት መጠበቂያ ምርቶች ከህክምና ባለሙያዎች ትዕዛዝ ውጭ ለህብረተሰቡ እየተሠራጩ በስፋት ጥቅም ላይ ሲውሉ ይስተዋላል። ይህም ህብረተሰቡን ለጤና ችግር እና ለወጪ እየዳረገው ይገኛል። ከዚህ አኳያ የሕግ ቁጥጥሩ በጣም ሊጠናከር ይገባል።

በመሆኑም በሀኪም ያልተረጋገጡ መድኃኒቶችን ለውበት መጠበቂያነት መጠቀም ነገ ላይ በሂደት ምን እንደሚያመጡ ስለማይታወቅ፤ ችግር ካለ ባለሙያዎች ዘንድ ቀርቦ አስረድቶ ባለሙያ የሚያዘውን የውበት መጠበቂያ መድሃኒቶችን ህብረተሰቡ በመጠቀም ጤንነቱን እንዲጠብቅ፤ ካላስፈላጊ ወጪ እራሱን እንዲታደግ በዚህ አጋጣሚ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለዶሮ ልማቱ ዘላቂነት የተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎችን በአግባቡ እንጠቀም

ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ የውጪ ምርቶችን በስፋት ለማምረት በያዘችው አቅጣጫ መሠረት የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ላይ በትኩረት እየሰራች ነው፤ ይህን ተከትሎም ምርትና ምርታማነቱ እየጨመረ መጥቷል።

ከዚሁ ጎን ለጎን ደግሞ ዜጎች የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ ማድረግ ላይም መሥራት ተጀምሯል። ለእዚህም በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አነሳሽነት የተጀመረው የሌማት ቱሩፋት መርሀ ግብር በዋናነት ይጠቀሳል። መርሀ ግብሩ በዶሮና እንቁላል፣ በወተት ሀብት ፣ በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ በስፋት መሥራት ያስችላል።

መርሀ ግብሩ ሥራ በገባ በጥቂት ጊዜ ውስጥም በተለይ በዶሮና እንቁላል ምርትና ምርታማነት እና ዋጋ ላይ እንዲሁም ገበያ ላይ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት ተችሏል። በልማቱ በሚሳተፉ ዜጎች የአመጋገብ ሥርዓትና ገቢ ላይም እንዲሁ ለውጦችን ማሳየት የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

ከግብርና ሚኒስቴር የተገኘ መረጃ የሚያመለክተውም ይህንኑ ነው። በ2014 ዓ.ም 3 ነጥብ 2 ቢሊዮን እንቁላል የተመረተ ሲሆን፤ ይህ አሀዝ በ2016 ላይ 5 ነጥብ 7 ቢሊዮን ደርሷል። ዘንድሮ ለማምረት ታቅዶ የነበረው 6 ነጥብ 2 ቢሊዮን የነበረ ቢሆንም ከእንቁላል ዋጋ ጋር በተያያዘ የእቅዱን ያህል ማምረት ሳይቻል ቀርቷል።

በዶሮ ስጋ ምርት ረገድም እንደሀገር እስከ 90 ሺ ቶን ይደርስ የነበረውን የማምረት አቅም ፣ ባለፉት ሁለት ዓመታት ምርትና ምርታማነት ማሻሻል ላይ በተደረገው ርብርብ በ2016 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ 205 ሺ ቶን የዶሮ ስጋ ማቅረብ ተችሏል።

ልማቱ እዚህ ለውጥ ላይ የደረሰው ነገሮች ሁሉ አልጋ ባልጋ ሆነውለትም አይደለም። በተለይ ከዶሮና እንቁላል ምርትና ምርታማነት ማደግ ጋር ተያይዞ ገበያ መፈጠር አስፈላጊ ስለመሆኑ ሲጠቆም የነበረው ሁኔታም ይህንኑ ይጠቁማል፤ ምርቱ እየጨመረ ሲመጣ ገበያው ካልተገኘ በምርታማነቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳርፍ ይችላል የሚል ስጋትም በአምራቾቹ በኩል ይሰማ ነበር።

የመኖ አቅርቦት እጥረትና ወላጅ ዶሮ እንደ ልብ ማግኘት አለመቻልም ሌሎች የልማቱ ደንቃራ እስከመሆን የደረሱበት ሁኔታ እንደነበረም አምራቾችም፣ ልማቱን የሚመሩ አካላትም ሲገልጹ ቆይተዋል። እነዚህ ችግሮች ልማቱ ከእስከ አሁኑም በላይ ብዙ ርቀት እንዳይጓዝ የሚያደርጉ መሆናቸውን መገመት አይከብድም።

መንግሥት እነዚህ ችግሮች እንዲፈቱ ሲሠራ ቆይቷል። ከመኖ አቅርቦት እጥረት ጋር የተያያዘውን ችግር መፍታት የሚያስችል ሥራ ተሠርቷል። በእዚህም በየክልሉ ከተሞች የዶሮ መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ተገንብተው ወደ ሥራ ገብተዋል። በሀዋሳና ቢሾፍቱ ደግሞ በርካታ ማቀነባበሪያዎች ተከፍተዋል። አዳዲስ ፋብሪካዎችን ከመትከል በተጨማሪ ነባሮቹም በሙሉ አቅማቸው እንዲሠሩ እየተደረገ ነው።

የእነዚህ ማቀነባበሪያዎች በስፋት መከፈት አልሚዎቹ መኖ ለመግዛት ብዙ ርቀት ሲሄዱ የነበረበትን ሁኔታ ያስቀራል፤ በዚህ ጉዞ ወቅት ሊከሰት የሚችለውን ወጪ ታሳቢ በማድረግ በማምረቻ ላይ የሚኖረውን ወጪን ከመጨመር ያወጣዋል።

የቅድመ ወላጅ ዶሮዎችን በሚፈለገው መጠን ለማግኘትም እንዲሁ መንግሥት የቅድመ ወላጅ ዶሮዎችን በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከውጭ በማስገባት ለአርቢዎች ሲያከፋፍል ቆይቷል፤ ይሁንና ከውጭ ምንዛሬ እጥረት ጋር በተያያዘ ይህም በምርትና ምርታማነትን የማሳደጉ ሥራ በታሰበው ልክ እንዳይሄድ ቀፍድዶ ይዞት እንደነበርም ይገለጻል።

በቅርቡ የሚድሮክ ቢዝነስ ግሩፕና አንድ የውጭ የቅድመ ወላጅ ዶሮ አምራች ኩባንያ በመተባበር በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነውን የቅድመ ወላጅ ስቶክ ፋርም ገንብቶ ማስመረቁ ይህን ችግር እንደሚፈታ ታምኖበታል።

የግብርና ሚኒስቴር መረጃ እንዳመለከተው፤ ይህ ፋብሪካ በአንድ ጊዜ ወደ ስድስት መቶ ሺ ጫጩቶችን የመያዝ አቅም ይኖረዋል። እያንዳንዳቸው ከሚጥሉት እንቁላል ጋር ሲደመር በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዶሮዎችን ለማምረት እንዲሁም ይህም ከሀገር ውስጥ ፍላጎት አልፎ ለውጭ ገበያም ለማቅረብ ያስችላል።

ይህም ሌላው በዶሮ ልማቱ ላይ ይታይ የነበረውን ትልቅ ደንቃራ የሚያስወግድና ልማቱን ወደ ፊት ማስፈንጠሪያ ነው። ወላጅ ዶሮዎች ከውጭ ይመጡ የነበረበትን ሁኔታ ያስቀራል። ከዚህ በተጨማሪም ዶሮዎቹን ለውጭ ገበያ ለማቅረብም የሚያስችል እንደመሆኑም ልማቱ ሌላ የውጭ ምንዛሬ እንዲያስገኝ ያደርጋል።

በቀጣይ ደግሞ ከገበያ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት መሥራት ያስፈልጋል። አምራቾች በመደበኛው መንገድ ከሚፈጥሩት የገበያ ትስስር በተጨማሪ ሌሎች አዳዲስ ገበያዎች ሊፈጠሩላቸው ይገባል። አግሮ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት አለባቸው። በዶሮ አመጋገብ ባህል ላይ ለውጥ ለማምጣት መሥራትም ያስፈልጋል።

አሁን ባለው የአመጋገብ ባህል ዶሮ እርባታው በዋናነት ማእከል የሚያደርገው ዓመት በዓላትን ብቻ ነው። ይህ አካሄድ ከምግብ ሥርዓት አኳያም ትክክል ነው ተብሎ የሚወሰድ አይደለም። በመሆኑም የሚመለከታቸው የምግብ ሳይንስ ባለሙያዎች ዶሮን በተለያየ መንገድ የመመገብን ፋይዳ አስመልክተው ግንዛቤ ማስጨበጥና የመሳሰሉት ላይ ሊሠሩ ይገባል። ይህ ሲሆን ልማቱም የምግብ ሥርዓቱም ገበያውም ተያይዘው ይጓዛሉ። በምግብ ዋስትናና የምግብ ሥርዓት ላይ የሚከናወኑ ተግባሮችም ይበልጥ ውጤታማ ይሆናሉ።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ‹‹የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል!››

ሚሊዮን ሺበሺ

ማህበረሰባችን ስግብግብነትን እና ማጭበርበርን የሚያነውርበት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የኖረ ማህበረሰባዊ ስነ ቃል አለው። ‹‹የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል›› የሚለው አንዱ ነው። የራሱ ያልሆነ ነገር አጭበርብሮ የሚወስድ ሰው ፈጣሪ አይባርክለትም፣ የራሱንም ጭምር ይቀጣዋል ተብሎ ይታመናል። በዘመናዊው የሕግ ቋንቋ ካየነውም አንድ ሌባ ሲያዝ የሰረቀውን ነገር ብቻ ተቀምቶ አይለቀቅም። ቅጣት አለው።

‹‹የቆጡን አውርድ ብላ የብብቷን ጣለች›› የሚለውም ከሚገባን ውጭ ለማግኘት መሞከራችንን የሚያነውር ነው። ‹‹አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል›› የተባለውም ይህንኑ የስግብግብነት በሽታ ለመግለጽ ነው። በሳይንስ እንኳን ብናየው ከልክ በላይ የሚበላ ሰው ጨጓራው መያዝ ከሚችለው በላይ ስለሚሆንበት ለሌላ በሽታ ይዳርገዋል።

በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ያደግን ሰዎች ታዲያ ምን ነክቶን ይሆን በዚህ ልክ ነውረኞች የሆንነው? የአንዳንድ ስግብግብ ነጋዴዎች ነገር አይገርምም ወይ? የት ሆነው ሊበሉት ነው? እነርሱ ብቻ በሕይወት የሚተርፉ እየመሰላቸው ይሆን?

እናቴ ስታወራ የሰማሁት አንድ የ1977 ዓ.ም ታሪክ ትዝ አለኝ። በ1977 ዓ.ም በሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች በተከሰተው ድርቅ ከፍተኛ ረሃብ ተከስቶ ነበር። አንዲት የአካባቢያችን ሴትዮ ጤፍ በጎተራ (ከጭቃ የሚሰራ የእህል ማስቀመጫ) አስቀምጣ መረገችው። መምረግ ማለት የጎተራውን አፍ በባህላዊ መንገድ ማሸግ እንደማለት ነው። ሴትዮዋ ጤፉን ጎተራ ውስጥ አሽጋ ረሃብ ይቆላታል። ጨክኜ መተው አለብኝ ብላ ተወችው። የባሰ ቀን ሲመጣ ብላ ማስመቀጧ ነው። በእሷ ቤት ሳይበሉ ከመዋልና ከማደር በላይ ክፉ ቀን አለ ማለት ነው። አንድ እግሩን ጅብ እየበላው ጓደኛውን ‹‹ዝም በል! ዝም በል! የእኔን እግር ነው›› አለ እንደተባለው ሰውዬ ማለት ነው።

ያቺ ሴትዮ ጤፉ ከጎተራ ውስጥ ተመርጎ ተቀምጦ እሷም በረሃብ ተመርጋለች። እንዲህ እንዲህ እያለች በረሃብ ወደቀች። ጤፍ ጎተራ ውስጥ ማስቀመጧን ያወቁ ሰዎች ተቆጥተው መብላት ጀመረችና እንደምንም ዳነች። ይህ አንድ ጎበዝ ደራሲ የፈጠረው ልቦለድ እንጂ እውነተኛ ታሪክ አይመስልም አይደል?

የዚች ሴትዮ ነገር አንዳንድ የሀገራችንን ስግብግብ ነጋዴዎች ያስታውሱኛል። እንኳን የዶላር ዋጋ ጨመረ ሲባል ሰምተው ይቅርና በሀገራዊ ቀውስ ወቅት ራሱ ለማትረፍ የሚስገበገቡ ናቸው። የት ሆነው ሊበሉት ነው? ሀገርና ሕዝብ ከሌለ በምን ሊያጌጡበት ይሆን? የሌሎች ሰዎች መቸገር እንዴት ለአንዳንዶች እንጀራ ይሆናል?

የሆነ ነገር ሆነ በተባለ ቁጥር የተጋነነ ዋጋ መጨመር ልማዳችን ሆኖ ቀረ። ከሁኔታቸው የምንረዳው የተጋነነ ዋጋ የሚጨምሩት የሚያመጡበት ዋጋ ስለተወደደ ብቻ አይደለም። ሰበብ ፈልገው ማጭበርበር የሚፈልጉ አሉ ማለት ነው። ለምሳሌ፤ የዶላር ምንዛሬ ዋጋ ጨመረ በተባለ በማግስቱ ዋጋ መጨመር የጀመሩ ነበሩ። ያ ዋጋ የጨመሩበት ዕቃ ግን ከወራት በፊት በነበረው ዋጋ የመጣ ነው። የተፈለገው በብዙ እጥፍ ማትረፍ ነው እንጂ ተገቢውን ትርፍ ማግኘት አይደለም። ህሊና ላለው ሰው በዶላር መጨመር ምክንያት ሊጨምር የሚችለው ከጭማሪው በኋላ በገዛው ዕቃ ላይ ነው። አንድ ዓመት አልሸጥለት ብሎ የቆየ ሱሪ በምን አግባብ ነው በአሁኑ ዋጋ የሚሸጠው?

ነጋዴ የሚነግደው ለትርፍ መሆኑ ግልጽ ነው። ይህን ማንም እንዲያስረዳን አንጠብቅም። ነዋሪ በመሆን ብቻ የሚታወቅ ነው። የሆነ ነገር ስንገዛ እንኳን ‹‹ይህን ያህል እንግዛችሁ›› ብለን ዋጋ ስንሰጥ ‹‹አይ! በዚህ ከዚያ ራሱ አልመጣም!›› ይሉናል። ለትርፍ መሆኑን በግልጽ ስለምንተዋወቅ ማለት ነው። ካመጣበት ዋጋ ጨምሮ እንደሚሸጥልኝ ጠንቅቄ አውቃለሁ፤ ምክንያቱም እሱ ብዙ ለፍቷል፣ ሲያመጣውም ወጪ አለበት። ይሄ አልጠፋንም!

ችግሩ ግን ግልጽ የሆነ ማጭበርበር ማድረጋቸው ነው። ከአንድ ዕቃ ብቻ ሙሉውን ማካካስ የሚፈልጉ አሉ። ማግኘት ከሚገባቸው ትርፍ በላይ የሚያገኙ አሉ። ይሄ አልበቃ ብሎ ምርት በመደበቅ ሌላ ተጨማሪ የገበያ ቀውስ እንዲፈጠር ያደርጋሉ።

እኔ የሚገርመኝ፤ የገበያ ቀውስ ሲፈጠር እነርሱንስ አይጎዳም ወይ? አርቆ ማስተዋል ስለተሳነን እንጂ ራስን

**ችግሩ ግን ግልጽ የሆነ ማጭበርበር ማድረጋቸው ነው። ከአንድ ዕቃ ብቻ ሙሉውን ማካካስ የሚፈልጉ አሉ። ማግኘት ከሚገባቸው ትርፍ በላይ የሚያገኙ አሉ። ይሄ አልበቃ ብሎ ምርት በመደበቅ ሌላ ተጨማሪ የገበያ ቀውስ እንዲፈጠር ያደርጋሉ**

በራስ እንደማጥፋት ማለት እኮ ነው። ማህበረሰብ ሲቃወስ እኮ ብዙ ነገር አብሮ ይቃወሳል። ሀገርና ሕዝብ ይተረማመሳል፤ ታዲያ ይሄ በተዘዋዋሪ አይጎዳቸውም ወይ?

ባለፈው ረቡዕ እንደተገለጸው፤ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በየክልል ከተሞች ያለአግባብ ዋጋ የጨመሩ 1 ሺህ 671 የንግድ ድርጅቶች ታሽገዋል። ከዚህ ቀደም በሰሩት ሕገ ወጥ የንግድ ተግባራት ምክንያት ታሽገው የነበሩ 18 ሺህ 789 ድርጅቶች ደግሞ የውል ስምምነት ፈፅመው ወደ ሥራ ተመልሰዋል። ከዚሁ ሕገ ወጥ ጉዳይ ጋር በተያያዘ 82 ነጋዴዎች በዚያን ቀን ብቻ ታስረዋል። በድምሩ ደግሞ 628 ነጋዴዎች ታስረዋል። ከእነዚህ ውስጥ 182 ነጋዴዎች ከእስራት የተፈቱ መሆኑን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታውቋል።

እንግዲህ ልብ በሉ! ‹‹አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል›› ማለት ይሄው ነው። ከልክ በላይ ሲስገበገቡ ታሰሩ። ጊዜና ገንዘባቸውን አባከኑ። ምናልባት እንደ ጥፋታቸው ደረጃ ታስረው የሚቆዩም ይኖራሉ። ንግድ ቤታቸው ታሽጓል። ሲታሸግ ደግሞ ሥራ ያቆማል ማለት ነው። ሥራ ሲያቆሙ የሚደርስባቸውን ክስረት ማሰብ ነው። ታዲያ ይሄን ድርጊታቸውን ‹‹አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል›› የሚለው የማህበረሰባችን አባባል በትክክል አይገልጸውም ወይ?

ህሊና የሚባለውን ነገር እንተወው! ቢያንስ ግን ሀገርና ሕዝብ ካልተረጋጋ በሰላም ሀብታም መሆን ይቻላል ወይ? አይቻልም እኮ! በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት የነበረውን ማስታውስ ቀላል ነው። ስግብግብ ነጋዴዎችን ብዙዎች ሲታዘቧቸው የነበረው ‹‹መኖራችሁን አውቃችሁታል ወይ?›› በሚል ነበር። በዚያው ልክ ደግሞ ቤታቸውን በነፃ የሰጡ፣ የአንድና የሁለት ወር የቤት ኪራይ አንቀበልም ያሉ ነበሩ። ችግር ሲያጋጥም እንዲህ መረዳዳት ሲገባ እንዴት በተቃራኒው ግርግር አገኘሁ ተብሎ ለማጋበስ ይታገላሉ?

ሲቀጥል አሁን አጋጠመ የተባለው ነገር ‹‹የገበያ ቀውስ›› ለመባል የሚበቃ አይደለም። ድሮም የነበረ ነው። ራሳቸው ነጋዴዎች ግርግር ፈጠሩ እንጂ የተለየ የቀነሰም ሆነ የጨመረ ምርት አልነበረም፤ እንዲያውም እንደ ሽንኩርት ባሉት ምርቶች ላይ ቅናሽ ታይቷል ብሏል። የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር። ዳሩ ግን ሁሌም ሰበብ የሚፈልጉ አንዳንድ ስግብግብ ነጋዴዎች ገና ለገና ሲወደድ አትርፈን እንሸጣለን በሚል ሰበብ ምርት መደበቅ ጀመሩ። ደግነቱ የፖሊስ ኃይል ከቀበሩበት እየመነቀረ አውጥቶታል። እንዲያውም እዚህ ላይ አንድ የሰማሁት ፈገግ የሚያሰኝ ነገር አለ። ከዚህ በፊት ዘይት የማይሸጡ ሁሉ ሳይቀር ደብቃችሁ ነው እንባላለን በሚል ዘይት እየገዙ መደርደሪያ ላይ ማስቀመጥ ጀምረዋል።

ህሊና እና ሕግ ሊያስተዳድረን ካልቻለ የግዴታ ቁጥጥር ያስፈልገናል ማለት ነው። ‹‹የከፉ ጎረቤት መብረቅ ይመታዋል›› እንደሚባለው በአንዳንድ ስግብግብ ነጋዴዎች ምክንያት በህሊና እና በሕግ የሚሠሩትም መጉላላቱ ይጎዳቸዋል ነው። የገበያ ቀውስ መፍጠር ጉዳቱ ለራሳችሁም ይተርፋልና አንዳንድ ስግብግብ ነጋዴዎች ከድርጊታችሁ ተቆጠቡ!

# ወቅታዊ

# ‹‹የምግብና ስነ ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ውጤቶች ተገኝተዋል››

*- ዶክተር ፍቅሩ ረጋሳ  የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ*

ማህሌት አብዱል

**ኢትዮጵያ በእንስሳት ሃብቷ በአፍሪካም ሆነ በዓለም ደረጃ የመሪነቱን ቦታ እንደያዘች ይታወቃል። ይሁንና ይህንን ሃብት ጥቅም ላይ በማዋል ለሕዝብና ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ ሚና በመጫወቱ ረገድ ወደኋላ የቀረች መሆንዋ በተደጋጋሚ ሲነሳ ይደመጣል። ይህንን ሃብት በማልማትና ሀገርን ከዘርፉ ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲሁም የሕዝቡን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ እንዲያስችል መንግስት ባለፉት  ዓመታት የተለያዩ መርሃ ግብሮችን ቀርጾ ተግባራዊ አድርጓል።**

**ከእነዚህም መርሃ ግብሮች መካከል በዓለም ባንክ ድጋፍ በ58 ወረዳዎች ላይ ሲተገበር የቆየው የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ፕሮጀክት እንዲሁም ባለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ በመላ ሀገሪቱ እየተከናወነ ያለው የሌማት ትሩፋት ዋነኛው ነው። በእነዚህ መርሃግብሮች አማካኝነት በዘርፉ አበረታች ውጤቶች እየተገኙ ነው፤ ሆኖም ካለው እምቅ አቅም አኳያ ገና ብዙ ተግባራትን ማከናወን ይጠይቃል። በእነዚህና በሌሎችም የዘርፉ ተግዳሮቶች ዙሪያ የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ፍቅሩ ረጋሳን አነጋግረን እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።**

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በተለይ በቀንድ ከብት ሃብት ቀዳሚ ብትሆንም እስካሁን የሚገባውን ያህል ከዘርፉ ተጠቃሚ ያልሆንባቸውን አብይ ምክንያቶች ያስታውሱንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**ዶክተር ፍቅሩ፡-** ኢትዮጵያ በአጠቃላይ በእንስሳት ሃብት በአፍሪካም ሆነ በዓለም ቀዳሚ ሀገር ናት። ለዚህ ደግሞ ያላት አየር ንብረትና ስነም-ህዳር ምቹ መሆኑ በምክንያትነት የሚነሳነው። ያለውን ሃብት በሃብትነት ማስቀመጥ ሳይሆን ማልማት፣ ማሻሻል፣ ማዘመንና ወደ ተሻለ ጥቅም መቀየር ይጠይቃል። ይህ የሀገሪቱ ሕዝብና መንግስት ስራ ነው። የኢትዮጵያ ስታስቲክ ኤጀንሲ በ2021 ያወጣው መረጃ እንደሚያሳየው፤ ኢትዮጵያ 71 ሚሊዮን የዳልጋ ከብት፣ 52 ሚሊዮን ፍየል እና 42 ሚሊዮን በጎች አሏት። የጋማ ከብትና ግመል 20 ሚሊዮን ይጠጋሉ። በጥቅሉ ከ200 ሚሊዮን በላይ የሚጠጋ እንስሳ አላት። በዶሮ በኩል ደግሞ በየጊዜው የሚቀያየር ሲሆን፣ 75 ሚሊዮን ዶሮዎች እንዳሉ መረጃው ያሳያል። ይህንን በአጠቃላይ ስንደምር ሀገራችን የትልቅ ሃብት ባለቤት መሆንዋን ያመለካታል፡፡

ይህም ሆኖ ካለን የእንስሳት ቁጥር ልክ ጥቅም ላይ ማዋል አለመቻላችን የሁላችንም ቁጭት ነው። ሆኖም ጥቅም የምንለካበት መንገድ መስተካከል አለበት። ምክንያቱም ለእኛ እንስሳት ብዙ ነገራችን በመሆናቸውና የሚሰጡንም ጥቅም ከምግብና መጠጥ ያለፈ በመሆኑ ሃብቱ ሙሉ ለሙሉ ጥቅም ላይ አልዋለም ማለት አይቻልም። በተለይ በግብርናው ዘርፍ እንስሳት በርካታ ጠቀሜታ እንዳላቸው ይታወቃል፤ የበሬ ወይም የፈረስ ጉልበት ተጠቅመን እናርሳለን፤ እንወቃለን፤ ለትራንስፖርትና ሸክም እንገለገላለን። በአጠቃላይ ለእያንዳንዱ እንቅስቃሴያችን እንስሳ ትልቅ ሚና አለው። በእርግጥ ሌሎች ሀገራት ወደመከናይዜሽን ሙሉ ለሙሉ ስለተቀየሩ እንስሳቱን የሚጠቀሙባቸው ለስጋቸው ወይም ለወተታቸው ነው። እኛ ይህንን ጥቅምንም ጭምር ከግምት ውስጥ ማስገባት አለብን።

እንደተባለው ከስጋ፣ ወተትና እንቁላል አኳያ ከእንስሳቱ ብዛት ጋር የሚመጣጠን ምርታማነት የለንም። እነዚህን እንስሳት ወደ ውጭ ልከን እያገኘን ያለነው የውጭ ምንዛሬም አነስተኛ የእንስሳት መጠን ካላቸው አንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ የሚባል ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት የስፔሻሊቲ ጉዳይ ነው። በዘርፉ ያደጉ ሀገራት ለወተት የሚይዟቸው ስፔሻሊቲ ዝርያዎች አሉ። ለስጋም እንዲሁ የሚመርጧቸው ዝርያዎች አሉ። እነዚህን ለይተን ማልማት ባለመቻላችን በዘርፉ የሚገባንን ጥቅም እንዳናገኝ አድርጎናል። ስለዚህ ከማልማት አንፃር ሊከናወኑ የሚገቡ ስራዎች አሉ፡፡

ከዚያ አንፃር ዝርያን ማሻሻልን ይጠይቃል። ለምሳሌ እንደሀገር ያሉት የወተት ከብቶች ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው። ስጋም ስፔሻላይዝድ ያደረጉ በዓለም ላይ የሚታወቁ ዝርያዎች በሚፈለገው ልክ የለንም። ከዚያ አልፎ ተርፎ ደግሞ አያያዙ ደካማ የሚባል ነው። ገጠር አካባቢ እንስሳቱ በበረት ውስጥ የሚኖሩ በመሆናቸው ለብዙ ችግር የተጋለጡ ናቸው። ዝናብ የሚዘንብባቸው በመሆኑ የሚተኙት ጭቃ ውስጥ ነው። ይህ ብቻውን እንኳን ምርታማነት ላይ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ አለው። አሁን አሁን እየተሻሻለ ይምጣ እንጂ አመጋገባቸውማ ባህላዊ ሲሆን፣ ጠዋት ጠዋት ለግጦሽ ከማሰማራት በዘለለ በተገቢው መጠን የተመጣጠነ መኖ አይሰጣቸውም፤ ይልቁኑም ግጦሽ ፍለጋ ረጅም ርቀት እንዲጓዝ ስለምናደርጋቸው በተለይ ላሞቹ የሚሰጡን የወተት መጠን ዝቅተኛ እንዲሆን ምክንያት እንደሆነ ግልፅ ነው። በዚህ ሂደትም የበሽታ መከላከል ስራ በቅጡ የማይሰራ በመሆኑ በርካታ ከብቶችን ሳንጠቀምባቸው ይቀራሉ።

ስለዚህ በጥቅሉ ዝርያ ማሻሻል ላይ ባለመስራታችን፤ የመኖ አያያዛችንም ደካማ በመሆኑና የበሽታ  ቁጥጥሩም ጠንካራ ባለመሆኑ ባሉን እንስሳት ልክ ተጠቃሚ እንዳንሆን አድርጎናል። እነዚህ ስራዎች ባለመሰራታቸው ምክንያት ምርታማነት ላይ ያለውን ተፅዕኖ ለአብነት ለማሳየት አንዲት የሀገረሰብ ዶሮ በዓመት 40 እንቁላል ብቻ ስትጥል፤ የፈረንጇ ደግሞ እስከ 320 እንቁላል በዓመት መስጠት ትችላለች። ሁለቱ ሲነፃፀሩ ስምንት እጥፍ ልዩነት አለው፡፡

ወደ ላሞችም ብንሄድ የእኛ ላም በቀን የምትሰጠው ወተት አንድ ነጥብ አምስት ሊትር ሲሆን፣ የተሻሻሉ ዝርያ ያላቸው የወተት ላሞች የሚሰጡት ግን በአማካኝ 15 ሊትር ወተት ነው። ያ ማለት አንዷ የፈረንጅ ላም የእኛን አስር ላም ትተካለች ማለት ነው።

በነገራችን ላይ ሀገራችን በንብ መንጋ ብዛትም ከአፍሪካ አንደኛ ነች። በጥቅሉ 10 ሚሊዮን የሚጠጋ የንብ መንጋ እንዳላት መረጃዎች ያሳያሉ። ከሰሜን ጫፍ እስከ ትግራይ እስከ ቦረና ድረስ፤ ከሱማሌ አጋዴን እስከ አሶሳ ድረስ ተስማሚ የአየር ንብረትና ስነምህዳር አላት። ግን አሰራራችን ኋላቀር በመሆኑ ለቤተሰብ ፍጆታ የሚውል ማር ለማግኘት እንኳን የሚቸግርበት ሁኔታ አለ። እስካሁን ባለው ሁኔታ የንብ ማነብ ስራው እየተመራ ያለው በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል በባህላዊ ቀፎና ዘዴ ነው። ባህላዊ ቀፎ ምርታማነቱ በዓመት በአንድ ጊዜ ቆረጣ 10 ኪሎ ግራም ብቻ የሚገኝ ሲሆን፣ በዘመናዊ  ቀፎ ደግሞ 30 ኪሎ ማግኘት ይቻላል። ዘመናዊ ቀፎዎችን በብዛት በማሥቀመጥና የተለያዩ ተክሎችን በመትከል በአንድ ዓመት ሶስት ጊዜ ማር መቁረጥ ያስችለናል።

**አዲስ ዘመን፡-  እነዚህን ችግሮች በመፍታት የዘርፉን ምርታማነት ለማሳደግ በሚኒስቴሩ የተሰሩ ስራዎችን ቢጠቅሱልን?**

**ዶክተር ፍቅሩ፡-** ግብርና ሚኒስቴር ዋነኛ ስራው ችግሮችን እየፈተሸ መፍትሔ ማበጀት ነው። ለዚህም ነው ባለፉት ዓመታት ዝርያ በማሻሻል፣ የመኖ ፋብሪካ በመትከል፤ ዘመናዊ መሳሪዎችን ለአርሶአደሩ በማከፋፈል ላይ ትኩረት አድርገን የቆየነው። በተለይም በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ችግሮችን ለመፍታትና የአሰራር ስርዓታችንን ለማዘመን ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተን ስንሰራ ቆይተናል። ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ደግሞ የጠቅላይ ሚኒስትራችን ኢኒሼቲቭ በሆነው የሌማት ቱሩፋት መርሃግብ በዘርፉ ከፍተኛ እምርታ ተመዝግቧል፤  የሕዝቡ ፍላጎትና ግንዛቤም ጨምሯል።

ለዘርፉ ምርታማነት መጎልበት መንግስትም የፖለቲካ ቁርጠኝነቱን በማሳየቱ በተጨባጭ በሚታይ መልኩ በቤተሰብ ደረጃም ሆነ እንደ ሃገር ምርታማነት በከፍተኛ መጠን አድጓል። ከዚህ በፊት ምንም አይነት በጀት በበቂ ሁኔታ የማይያዝለት ዘርፍ አሁን ላይ በክልሎች ደረጃ ራሱ ትልልቅ በጀት መያዝ ተጀምሯል። ለምሳሌ አምና ለንብ ቀፎ ብቻ ተብሎ ኦሮሚያ የመደበው 135 ሚሊዮን ብር ነው። ከዚህ በፊት ግን የአርሶ አደሩን ስራ አይቶ እንኳ ለመመለስ የሚያስቸግር የስራ ማስኬጃ ገንዘብ የሚያጥርበት ሁኔታ ነበር።    ግብዓቶችንና አቅርቦትን በማሻሻል፤ ስልጠና በመስጠት ብዙ ለውጦችን ማምጣት ተችሏል።

ለዚህም ለአብነት እንኳን ብንጠቅስ የሌማት ቱሩፋቱ



ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

ከመጀመሩና ከተጀመረ በኋላ የመጡትን ለውጦች ማየት እንችላለን። ዝርያ ማሻሻል ስራ አንፃር ሁለት የውጭ ዝርያዎችን አባላዘር ተጠቅመን ከሌማት ቱሩፋት በፊት (2014 ዓ.ም) ላይ በጣም ትልቅ ስራ ሰራን ብለን በኢትዮጵያ ደረጃ የሰራነው 500 ሺ  ሲሆን፣ በአንድ ዓመት ልዩነት ግን ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን  ከብቶችን ዝርያ ማሻሻል ችለናል። ይህም ከበፊቱ ጋር ሲነፃፀር ከአምስት እጥፍ በላይ ነው። የሚጎትቱንና አቅማችንን የሚፈትኑን ነገሮች ባይኖሩ ከዚያም በላይ መስራት ይቻላል።

ወተትንም ያየን እንደሆነ ከሌማት ቱሩፋት በፊት በአጠቃላይ ከግመል፣ ከፍየልና ላሞች ሰባት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ሌትር የተመረተ ሲሆን፣ ዘንድሮ ዘጠኝ ነጥብ 997 ቢሊዮን ሊትር ወተት ማግኘት ችለናል። በተጨማሪም በ2014 ዓ.ም 26 ሚሊዮን የዶሮ ጫጩት ያሰራጨን ሲሆን፣ ዘንድሮ 72 ሚሊዮን ጫጩት ለአርቢዎች ማድረስ ችለናል። ይህንን ስናይ በሶስት እጥፍ አድጓል ማለት ነው። በዚያው ልክ የእንቁላልና የዶሮ ስጋን በጣም በከፍተኛ ሁኔታ ልዩነቶችን አሳይቷል። ከሁለት ዓመት በፊት ሶስት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን እንቁላል የተመረተ ሲሆን፣ በ2016 ዓ.ም ደግሞ አምስት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን እንቁላል አምርተናል። በእርግጥ እቅዳችን ስድስት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ነበር፤ መሃል ላይ ችግር ስለነበረ የእቅዳችንን 94 በመቶ አሳካተናል። ይህም ትልቅ ስኬት ነው።

ወደ ዘመናዊ ቀፎ ስንሄድ በአጠቃላይ ዘመናዊና የሽግግር ቀፎ ብለን የወሰድነው 2014 ዓ.ም ላይ 905 ሺ ነበር፤ ዘንድሮ ግን የሰራነው ወደ ሁለት ሚሊዮን አካባቢ ነው። ምርቱም ያደገ ሲሆን፣ ከሁለት ዓመት በፊት እንደሃገር 147 ሺ ቶን ይመረት የነበረውን የማር ምርት ዘንድሮ ወደ 272 ሺ ቶን  መድረስ ችሏል። ከጫጩት ዓሳ ስርጭት አንፃር ደግሞ ከአንድ ሚሊዮን ተነስተን ላይ ስድስት ነጥብ አራት ሚሊዮን የዓሳ ጫጩት አሰራጭተናል፤ ይህ እንደሃገር በጣም ትልቅ እድገት የሚባል ነው። ምርቱንም በዚያ ልክ ለማሳደግ የሰራን ሲሆን፣ በዚህ ረገድም ከ78 ሺ ቶን ወደ 132 ሺ ቶን የዓሳ ምርት ከፍ አድርገናል።  በጥቅሉ እነኚህ ውጤቶች ዋና ዋናዎቹ እንጂ በርካታ አበረታች እምርታዎችም ተመዝግበዋል፤ ይህም ሲባል ግብዓት በቀጥታ የሚሆኑትን ነው ያቀረብኩት እንጂ ለእነዚያ ደግሞ አስቻይ የሚሆኑ ብዙ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከዝርያ ማሻሻል ጋር ተያይዞ የተሰራው አበረታች ቢሆንም የሊኩዊድ ናይትሮጂን እጥረት እንዳለ በእርባታ ተግባር ላይ በተሰማሩ አካላት ይነሳል፤ በተለይ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ላይ ያለው ማሽን በተደጋጋሚ ብልሽት የሚያጋጥመው በመሆኑ መቸገራቸውን አይተናል፤ ይህንን ችግር ለመፍታት ምን ያህል ጥረት ተደርጓል?**

**ዶክተር ፍቅሩ፡-** ከዚያ በፊት ግን የማዳቀል አቅማችን ጨምሯል ሲባል የሊኩዊድ ናይትሮጂን ማምረት አቅምም እንዲሁ ማሳደግ መቻላችንን መግለፅ እወዳለሁ። በተደጋጋሚ የሚነሳው  ከዝርያ ማሻሻል ጋር ተያይዞ የሊኩዊድ ናይትሮጂን እጥረት ነው። እርግጥ ወደ 20 የሚጠጉ የሊኩዊድ ናይትሮጂን ማሽኖች በኢትዮጵያ አሉ። ከመቀሌ ጀምሮ ባህርዳር፣ ደብረብርሃን፣ ቃሊቲ፣ ሻሸመኔ፣ ሃዋሳ፣ ሶዶ፣ ወልቂጤ፣ ነቀምት፣ ጅማ፣ ሚዛን፣ ሐረርና ሌሎችም አካባቢዎች ላይ ማሽኑ አለ። ሆኖም አብዛኞቹ ከጊዜ ብዛት በተደጋጋሚ ብልሽት ያጋጥማቸዋል። ይህንን ጉዳይ እግር ለእግር ተከታትለን ለማስጠገን ጥረት አድርገናል። ሆኖም አሮጌ ማሽኖች አፈፃፀማቸው በጣም አነስተኛ በመሆኑ በእነሱ ላይ ተንተርሰን መቀጠል የለብንም። ስርጭቱም ደግሞ አንዳንድ ቦታ ላይ ፍትሐዊ አይደለም፤ ይህንንም ለመቀየር ብዙ ስራ ሰርተናል። በአጠቃላይ ወደ አስር የሚጠጉ የሊኩዊድ ናይትሮጂን ማሽን ግዢ እቅድ ተይዞ በአሁኑ ወቅት የገቡ አሉ፤ አንዱ ቃሊቲ ላይ ተተክሏል፤ የሚቀረን ማስመረቅ ነው። አሶሳ ላይ የግዢ ሂደቱ አልቆ በመጓጓዝ ላይ ነው። ሶስት ደግሞ በዓለም ባንክ ድጋፍ እየተከናወነ ባለው ፕሮጀክታችን አማካኝነት ግዢ ተፈፅሞ መስከረም ላይ የሚገባ ይሆናል። ተጨማሪ አምስት ደግሞ በግዢ ሂደት ላይ ነው። በመሆኑም ከዚህ ቀደም ባልነበረባቸውም ሆነ አሮጌም በሆኑባቸው ቦታዎች ላይ ለመተካትና ከዚህ የበለጠ ለመስራት አቅደን እየተንቀሳቀስን ነው።

እንደተባለው በተለይ ወልቂጤ ላይ ያለው ማሽን ተደጋጋሚ ብልሽት ያጋጥመዋል። ዘንድሮ ይህንን ችግር ለመፍታት ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፤ ሆኖም ከግዢ ሂደቱ መራዘም ጋር ተያይዞ ወዲያው ሊደርስልን ስላልቻለ በጣም በትኩረት የሰራነው ሲበላሽ ፈጣን የሆነ የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙና ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል። ያም ቢሆን ካለው ሰፊ የሕዝብ ፍላጎት አንፃር በነባሩ አሮጌ ማሽን ነው ስንሰራ የነበረው፤ በዚያ ሁኔታ መቀጠል ደግሞ ከመሰረቱ ችግሩን እንደማይፈታ አውቀን ነው ወደ ግዢ ሂደት የገባነው። በኢትዮጵያ በዚህ ደረጃ በአንድ ጊዜ ተገዝቶ አያውቅም። ጥረት እየተደረገ ያለው ማሽኖቹ በሁሉም ክልል እንዲኖርና እዚህ ድረስ መመላለሱን ለማስቀረት ነው። ይህ ከመሰረቱ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# ‹‹የምግብና ስነ ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ...

ከገጽ 6 የዞረ



ችግሩን ይቀርፍልናል ብለን እናምናለን። በቀጣይ ዓመት የሊኩዊድ ናይትሮጂን ጉዳይ በእርግጠኝነት ችግር ሆኖ የሚቀጥል አይሆንም።

ዝርያ ማሻሻል ላይ በአርቴፊሻልና በሊኪዊድ ናይትሮጂን ብቻ ሳይሆን ኮርማ በማሰራጨትም እንዲዳቀሉ እናደርጋለን። በተለይ ራቅ ባሉ አካባቢዎች ላይ የኮርማ ስርጭት በስፋት ይካሄዳል። በተጨማሪም ይህንን እንደስራ ፈጠራ ተጠቅመው አገልግሎት በሰጡ ቁጥር ገቢ የሚያገኙ አሉ። እዚህ ላይ የተመረቱ ዝርያዎች ጤነኛና ምርታማ መሆናቸውን የማረጋገጥ ስራ ይሰራል። አሁን ላይ የኮርማ አባላዘር የማምረቻ ቴክኖሎጂ ኢትዮጵያ ውስጥ የለም፤ እየተገዛ የሚመጣው ከውጭ ነው። ማምረቻው ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲተከል ከውጭ ኩባንያ ጋር መነጋገር ጀምረናል። ይህ መሆኑ ኢትዮጵያ ትልቅ የእንሳስት ሃብት ያላት፣ ዝርያ ማሻሻል ላይ በስፋት እየተሰራ በመሆኑና ለአውሮፓም ሆነ ለመካከለኛው ምስራቅ ቅርብ መሆንዋ የተሻለች በመሆኗ ኩባንያው ፋብሪካውን ቢከፍት አዋጭ ይሆናል። በመሆኑም ችግሩን ከመሰረቱ ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ አዲስ አበባና ቢሾፍቱ ላይ ተወስነው የነበሩ የመኖ ማቀነባበሪያዎች ለማስፋት ከፍተኛ ስራ ሲሰራ ነበር። የመኖ ማቀነባበሪያ ክልሎች ቢያንስ አንዳንድ እንዲኖራቸው የሚል አቅጣጫ ተሰጥቶ አዳዲስ እየተከፈቱ ነው። በቅርቡ አሶሳ ላይ ተተክሏል። ከዚህ በፊት ከቦንጋ ቢሾፍቱ ድረስ እየመጡ ነበር የሚወስዱት። አሁን እዛው ቦንጋ በመተከሉ ወጭና እንግልት ቀርቶላቸዋል። ጅግጅጋ ላይም አዲስ ማቀነባበሪያ የተተከለ ሲሆን፣ ሃዋሳ ላይ ሁለትና ሶስት በግልም ሆነ በኢንተርፕራይዞች ተከፍተው እየተሰራ ነው። ባህርዳር ላይ ትልቅ ኤክስፖርት ደረጃ የሚያደርግ ፋብሪካ ተክቷል። አዲስ አበባና ቢሾፍቱ ላይ ተጨማሪ ብዙ አሉ፣ እነሱም በሙሉ አቅማቸው እንዲሰሩ እየተደረገ ነው። ሆኖም አሁን ላይ በሚሊዮኖች እጥፍ እየጨመርን በመሆኑ በዚያው ልክ መኖ መጨመር አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- በሌማት ትሩፋት መርሃግብሩ የተያዘው ውጤታማነት ቆላማ አካባቢዎች ላይ ለምን መድገም አልተቻለም? በተለይ በእነዚህ አርብቶአደር አካባቢዎች የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ እንደሃገር ፈተና የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?**

**ዶክተር ፍቅሩ፡-** እንደሀገር ባለፉት ዓመታት የግብርና ምርታማነት ለማሳደግ በተሰሩ ስራዎች የምግብና ስነ ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የሚችሉ ውጤቶች ተገኝተዋል። ሆኖም በተለይ ትልቁ የእንስሳት ቁጥር ያለው ቆላማና አርብቶአደር አካባቢዎች ላይ እንደመሆኑ በሚፈለገው ደረጃ ተሰርቷል ማለት አይቻልም። እነዚህ አካባቢዎች ደግሞ እንደሚታወቀው ለብዙ ችግሮች ተጋላጭ ናቸው። በተለይም የአየር ንብረት አሳሳቢ የሆነባቸው በመሆናቸው የሚፈለገው ለውጥ አልመጣም፤ አብዛኛው የሌማት ትሩፋት የሚሰራባቸው አካባቢዎች ለጥምር ግብርና ምቹ በሆኑ ደጋና ወይናደጋ አካባቢዎች ነው። አስቀድመን ያነሳቸው እንደሊኪዊድ ናይትሮጂን ማምረቻ ያሉ መሰረተ ልማቶች በእነዚህ አካባቢዎች ባለመኖራቸው ማዳቀልና ማባዛትም አስቸጋሪ ነው። የዶሮ ማባዣ ማዕከላት በአብዛኛው ያሉት ደጋና ወይናደጋው ክፍል ነው። እነዚህ አካባቢዎች ደግሞ የተረጋጋ ሕይወት የሚኖሩ ማኅበረሰቦች ያሉባቸው ናቸው። በመሆኑም ከመጀመሪያውም ለዝርያ ማሻሻል የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማቶች አልተዘረጉም።

ከዚያ በተጨማሪ በየጊዜው በዓለም ላይ የሚከሰተው የአየር ንብረት ለውጥ ብዙ ጉዳቶችን ሲያደርስ ነበር። አንድ ጊዜ ጎርፍ፤ ሌላ ጊዜ ድርቅ ይከሰታል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ እንስሳት ይሞታሉ። እንስሳ ሞተ ማለት ደግሞ እዚያ አካባቢ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሕይወታቸው የተመሰረተው በእንስሳቱ ላይ በመሆኑ መፈናቀል፤ የኑሮ መሰረቱ መናጋት፣ ለበሽታና ለሞት መጋለጥ ይመጣል። በዚህ አካባቢ ያለውን ችግር ለመፍታት ሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን በዋናነት የሚሰራው የውሃ አቅርቦቱን ማሻሻል ነው። ይህንን በሁሉም ክልል በሚባል ደረጃ የውሃ ስራ ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ነው። ለእንስሳቱ ውሃ ለማጠጣት ብቻ ሳይሆን ለመኖ ልማት የሚሆንም ነው። በእነዚህ አካባቢዎች የሚሰሩት የልማት ስራዎች በግብርና ሚኒስቴር ብቻ አይደሉም፤ ቆላማና አርብቶአደሮች አካባቢ ሚኒስቴር፣ በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርና የተለያዩ ድርጅቶች ጭምር ነው።

አፋር፤ ሱማሌ፣ ኦሮሚያ ደግሞ ቦረና አካበቢ ላይ በእኛ ሚኒስቴር የተቆፈሩ የውሃ ጉድጓዶች አሉ። ከዚሁ ጎን ለጎን መኖ ልማት ላይ በስፋት እየተሰራ ነው። ሰሞኑን ቦረና ላይ ታይቶ የማይታወቅ መኖ ለምቷል። ስለዚህ ግብርና ሚኒስቴር ከመኖ ዘር አቅርቦት ጀምሮ ለሁሉም ክልል በየዓመቱ የተሻሻለ መኖ አቅርበን በእነኚህ የግጦሽ ቦታዎች ላይ እንዲተከሉ ይደረጋል። ከዚህ ቀደም የነበረው ያልተሻሻለ ዝርያ በመሆኑ ምርታማነቱ አነስተኛ ነው፤ ይህም እንዲሻሻል ሚኒስቴሩ እየሰራ ነው። እኔ የምመራው ቡድንም በየዓመቱ ይሰማራል፤ በየዓመቱ ድጋፍ ያደርጋል።

መኖ ልማት ላይ በተፈጥሮም በስፋት የሚመረትባቸው ወቅቶች አሉ፡፤ ይሁንና ከብቶቹ የሚችሉትን ግጠው ሌላው የሚበሰብስበትና የሚባክንበት ሁኔታ ነበር። በዚህ ሁኔታ ደግሞ ያለውን ችግር በዘላቂነት መፍታት አያስችልም። በመሆኑም መኖ ስናመርት በአግባቡ መሰብሰብ፤ ማከማቸትና በጥንቃቄ መያዝ አለበት በሚል በርካታ የመኖ ማከማቻ በየክልሉ እንዲሰራ ተደርጓል። ይህም ትርፍ ሲመረት በጊዜያዊነት የሚጠቀሙትን ተጠቅመው ሌላውን አስቀምጠው በድንገተኛ ጊዜ ከመሃል ሀገር ጭነን የምንወስደውን ያስቀራል። እንደአጠቃላይ በድርቅና በጎርፍ ምክንያት የሚመጡትን ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት እየሰራን ነው። አልፎ አልፎ የሚከሰቱት ውስን ችግሮች በስተቀር አሁን ላይ እየተካሔደ ባለው አሰራር የምግብና ስነ ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ የግብርና ሚኒስቴርም ቁልፍ ተግባር ነው፤ በዚያው ልክ እየሰራን ነው፤ በዚህ መልኩ ከተረጂነት ለመላቀቅ እየተኬደበት ነው።

ይህም ብቻ ሳይሆን ከቀንድና ጋማ ከብት ልማት ባሻገር አርብቶአደሮቻችን ዶሮ ልማት ላይ እንዲገቡ፤ የውሃ አካላት ያሉባቸው አካባቢዎች ላይ ዓሳ በማምረትና በተወሰኑት የእንስሳት ውጤቶች ላይ የተመሰረተውን ኑሯቸውን የተለያየ አማራጭ እንዲኖራቸው ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው። የማር ምርትንም በተመሳሳይ በተሻለ ሁኔታ እንዲሰሩ በሌማት ትሩፋቱ ድጋፍ እየተደረገላቸው ነው። እንደተነሳው አብዛኛው የእንስሳት ሃብታችን ያለው እዚያ አካባቢ ቢሆንም በወተት በኩል የተሻሻለ ዝርያ ያለው በከተማና በከተማ ዙሪያ ነው። በዚያ ልክ እዚያ ቆላማ አካባቢዎች ላይ መስራት ያስፈልጋል።

ከሁሉ በላይ የግብርና ሚኒስቴር ዋና ተልዕኮም የምግብና የስነ-ምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ነው፤ ከዚያ አልፎ ከውጭ የሚገቡትን መተካትና ወደ ውጭ የሚላኩትን የግብርና ምርቶች መጠን ማሳደግና የስራ እድል መፍጠር ነው። እንደ አጠቃላይ ከሰራነውና ካስመዘገብነው አንፃር ጥሩ መሻሻሎች አሳይተናል። ከሚጠበቅብን አንፃር ግን ብዙ መሄድ አለብን። የጠቀስኳቸውን የሚኒስቴሩን ዓላማ ከማሳካት አንፃር ብዙ ስራዎች መስራት አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- በሌማት ትሩፋቱ ምርታማነትን ቢጎለብትም የገበያ ትስስሩ ላይ በአምራቾቹ የሚነሱ ቅሬታዎች አሉ፤ በተለይ እንቁላልና ወተት ምርት በስፋት ቢመረቱም የገበያ ጉዳይ አሳሳቢ እንደነሆነባቸው ይጠቀሳል፤ በአንፃሩ ደግሞ በተለይ ከተሞች አካባቢ እነዚህ ምርቶች የቅንጦት ምግብ ሆነው ኅብረተሰቡ እንደልቡ እያገኘ አይደለም። እነዚህን ሁኔታዎች ለማጣጣም ምን እየተሰራ ነው?**

**ዶክተር ፍቅሩ፡-** ይህ ችግር የለም አልልም፤ ይህ የሆነባቸው በርካታ ምክንያቶች ግን አሉ። በተለይ በአጭር ጊዜ ውስጥ ስርነቀል የሆነ ለውጥ ሲመጣ ክፍተት መፈጠሩ አይቀርም። በተለይ ደግሞ የእንስሳት ምርት የሚበላሹ ነገሮች በመሆናቸው ወዲያውኑ ለተጠቃሚዎች መድረስ መቻል አለባቸው። ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነው የሌማት ትሩፋት መርሃግሩ ማሳያ ያልነው የዘንድሮ የእንቁላል ምርት ነው። ከሶስት ሚሊዮን ወደ አምስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሲደርስ ገበያውን ማስተሳሳር ካልተቻለ የሚፈጥረው ነገር ይታወቃል። ያም ቢሆን መመገብ ካለብን አንፃር ይህ ምርት በጣም ትንሽ ነው። አንዳንድ ቦታ ላይ ደግሞ እንቁላሉ ተመርቶ ቤት ውስጥ ረጅም ጊዜ በመቀመጡ ችግር ይደርስበታል። ወተትም ከጥሬ ባለፈ እሴት ተጨምሮበት የሚያመርትና ወደ ገበያ የሚያደርሱ አግሮ ኢንደስትሪዎች በዚያው ልክ ሊኖሩን ይገባል።

ከዚህ አንፃር በእንቁላል በኩል እስከአሁን የእሴት መጨመር ስራ ኢትዮጵያ ውስጥ አልተሰራም። ሌላ ሃገር ወደ ዱቄት ተቀይሮ እንቁላሉን ብቻ ሳይሆን ዱቄቱም በብዙ መልኩ ጥቅም ላይ ይውላል። ሌላው ይቅርና የቀዝቃዛ ማስቀመጫ ስርዓት መፍጠር ያስፈልጋል። በዝቅተኛ ሙቀት ከተቀመጠ እስከ ስድስት ወር ሊያገለግል የሚችልበት እድል አለ። እነዚህን መሰረተ ልማቶች መዘርጋት ያስፈልጋል። በወተት በኩልም በተለያዩ መንገዶች እሴት ተጨምሮበት ታሽጎ ረጅም ጊዜ እንዲያገለግል በተለይ ከእኛ ባህል አንፃር በፆም ወቅት እሴት ተጨምሮበት ፆም ሲፈታ ሰው በእርጎ፤ በቂቤና በአይብ መልኩ እንዲመገብ ለማድረግ መሰራት አለበት። በርካታ የወተት ማቀነባበሪያዎች አሉ፤ ግን እየተመረተ ካለው ምርት አንፃር ብዙ መስራት ያስፈልጋል። ከዚህ ቀደም የነበሩት ፋብሪካዎች ወተት አጣን ብለው ቅሬታ ያቀርቡ ነበር፤ አሁን ደግሞ በእነሱና በአምራቹ መካከል የዋጋ አለመግባባት አለ። እነኚህ ነገሮች ሙሉ ለሙሉ መፈታት አለባቸው።

ለምሳሌ ከምባታ ከፍተኛ የወተት ምርት ያለበት ቦታ ነው። እስከ 97 በመቶ ዝርያው የተሻሻለ ከብት ያለበት ቦታ ነው። የዚያ አካባቢ ማኅበረሰብ ዋነኛ ጥያቄ የገበያ ትስስርና ማቀነባባሪያ ጉዳይ ነው። እዚህ ላይ አንደኛ ወተትን ወደገበያ እንዲያቀርቡ የሚያስችላቸውን ማቀዝቃዣ ተሽከርካሪ ገዝተን ሁለት ለኦሮሚያ ሁለት ለአማራ፤ አንድ ለሲዳማ፤ አንድ ለደቡብ፤ አንድ ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ሰጥተናል። ስለዚህ ከንባታ አካባቢ ያለው ጥያቄ መኪና ከመስጠት በተጨማሪ የወተት ማቀነባበሪያ ዘንድሮ ተገንብቷል። ሲዳማ ላይ በጣም በስፋት የወተት ምርት አድጓል፤ በነገራችን ላይ በሌማት ቱሩፋት ምርጥ አፈፃፀም ያለው ሲዳማ ነው። ዛሬ ከሐዋሳ በዚያ ቦቴ መኪና አስር ሺ ሊትር ወተት ወደ አዲስ አበባ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ይመጣል። በተመሳሳይ ከአማራ ክልል ሰሜን ሜጫ ከተባለ ስፍራ በየቀኑ ወተት ይመጣ ነበር።

ስለዚህ ምርትና አግሮ ኢንዱስትሪውን ለማገናኘት ድጋፎች እያደረግን ነው። ግን እኛ እያለምን ያለነው በአጭር ጊዜ በጣም ከፍተኛ ምርት ይመጣል ብለን ነው። በዚያ ልክ ደግሞ እነዚህ እሴት መጨመር የሚያደርጉ ኢንዱስትሪዎች መጨመር አለባቸው። ማኅበራትን አደራጅተን ማምረቱ ብቻ ሳይሆን ወደ አግሮ ኢንዱስትሪ እንዲገቡ ጥረት ማድረግ ይገባል። እሴት መጨመርና የገበያ ትስስር ትልቁ የቤት ስራችን ነው። በፊት ስለምርት ነበር የምናነሳው፤ አምርተን ደግሞ ለገበያ ካልቀረበ እየተመረተ ያለውን ወደኋላ የሚመልስ ስለሆነ እሱን እንደትልቅ ኃላፊነት ወስደን በቀጥታ ስራው ከሚመለከታቸው ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርና ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር ተቀናጅተን አሁን እንደ ችግር የሚነሱትን ነገሮች መፍትሔ መስጠት የግድ ይላል።

**አዲስ ዘመን፡- የእንስሳት ሃብቱን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በዓለም ባንክ ድጋፍ በ58 ወረዳዎች ላይ ላለፉት ስድስት ዓመታት ሲተገበር የቆየው ፕሮጀክት የመጀመሪያው ምዕራፍ ተጠናቋል። ስመሆኑ አፈፃፀሙ ምን ይመስላል? የሁለተኛው ምዕራፍ ዝግጅትስ በምን ደረጃ ላይ ነው?**

**ዶክተር ፍቅሩ፡-** ስለሁለተኛ የፕሮጀክቱ ምዕራፍ በመንግስት ደረጃ በይፋ ስልተገለፀ ብዙም መናገር አልችልም፤ በሂደት ላይ ነው። ይህ ፕሮጀክት አንቺም እንዳነሳሽው ላለፉት ስድስት ዓመታት ደጋና ወይና ደጋ ላይ ባሉ 58 ወረዳዎች ላይ ሲተገበር ቆይቷል። በግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በምንሰራው ስራ በርካታ አስተዋፅዎችን አበርክቷል። ለምሳሌ አስቀድሜ ያነሳሁልሽን የወተት መኪና የገዛነው በዚህ ፕሮጀክት አማካኝነት ነው። በ27 ወረዳዎች ላይ ሞዴል የዶሮ መንደር ብለን የዶሮ ማሳደጊያ ተቋማትን አሳድገናል። በዚሁ ፕሮጀክት ወጣቶች እዚያ ላይ ተደራጅተው የአንድ ቀን ጫጩት ይወስዱና እስከ 65 ቀን አሳድገው ቄብ ሲሆኑ ይሸጣሉ። የዓሳ ጫጩት የምናሰራጨው በዚሁ ፕሮጀክት አማካኝነት ሲሆን፣ የዓሳ ማስፈልፈያ ማዕከላትን አርባምንጭ፣ ባቱ፣ ባህርዳር፣ ሰበታና ሃዋሳ ላይ ተገንብተዋል። ዓሳን ለማጥመድ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች እስከ ጀልባ ድረስ ገዝተን አሰራጭተናል፡፡

ዝርያ ማሻሻል ላይ እንዲሁ አስቀድመን ያነሳነው የሊዊኪድ ናይትሮጂን በመንግስት በጀት የሚቻል አይደለም፤ የገዛነው በዚህ ፕሮጀክት ነው። ያታው የተለየ ኮርማ አባላዘር ስናሰራጭ የነበረውም በዚሁ ፕሮጀክት በተመደበ በጀት ነው። እንደአጠቃላይ አስተዋፅኦው በሃገርም ሆነ በፕሮጀክት ደረጃም ጥሩ የሚባል ነው። ከዚያ ባለፈ ያለፕሮጀክት ወረዳ በወጥነት መሰራት ያለባቸው ስራዎች አሉ። ለምሳሌ በሽታ መቆጣጠር ላይ ደስታ መሰል በጎችና ፍየሎች ላይ የሚከሰት በሽታን ለመከላከል በሃገር ደረጃ ስትራቴጂ ቀርፀን በ2027 ከኢትዮጵያ እናስወግዳለን ብለን ክትባት እየሰጠን ነው፤ ይህንን ስራ የሚደግፈው ፕሮጀክቱ ነው፡፡

ከቴክሎጂ ሽግግርም አንፃር ሆለታ ላይ የዴሪ ማዕከል ብለን እየሰራን ነው። ብዙ ቴክሎጂዎችን ወደ ኢትዮጵያ ሊያስገባ የሚችል ስራ እየተሰራ ነው። እንደ አጠቃላይ በዚህ ፕሮጀክት እየተሰራ ያለው ስራ ከፕሮጀክት ከጊዜያቸው በላይ ዘመን የሚሻገሩ ለሃገር ሃብት ሆነው የሚቀጥሉ ስራዎችን ነው። ለወጣቶች፤ ለሴቶች፤ ለአቅመ ደካሞች ትልቅ አቅምና የስራ እድል የፈጠረ ፕሮጀክት ነው። የጋራ ፍላጎት ኖሯቸው ተደራጅተው የጀመሩ ማኅበራት አሁን ላይ ብዙዎቹ አቅማቸው አድጎ ወደ ሕብረት ስራ ማኅበራት እየደረሱ ነው።

ሁለተኛው ምዕራፍ ሊቀጥል የቻለውና ድጋፍ ያገኘነው በመጀመሪያው ምዕራፍ ባስመዘገብነው ውጤታማ ስራ ነው። ስለዚህ ሁለተኛው ምዕራፍ የነበሩትን መልካም ተሞክሮች ይዘን የምንቀጥልበት፤ ካለፈው ወረዳ ቁጥር የበለጠ ወረዳዎችን ጨምረን የምንሰራበት፤ በጀቱ በእጥፍ የሚሆንበት፤ አሁን ላይ ፈቃድ አግኝተናል፤ ያለነው ሰነድ የማጥራት ስራ ላይ ነው። አብዛኛው ግን ትኩረት የሚያደርገው ቅድም እንደከፍተት ያየናቸውና መስራት አለብን ባልንባቸው ስራዎች ላይ ነው። በተለይም እሴት መጨመርና በከፍተኛ ካፒታልና አቅም የሚሰሩ ስራዎች ላይ ያተኩራል። ጥናቱ ሲጠናቀቅ በይፋ የምናሳውቀው ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር ፍቅሩ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# በጉራጌ ዞን ለመስቀል በዓል ከ800 ሺህ በላይ ቱሪስቶችን ለመቀበል ዝግጅት ተደርጓል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**


ወይዘሮ መሠረት አመርጋ

አዲስ አበባ፡- በዞኑ ለመስቀል በዓል ከ800 ሺህ በላይ ቱሪስቶች ለመቀበል ዝግጅት መደረጉን የጉራጌ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ገለጸ፡፡ ከመስከረም ዘጠኝ እስከ 12 ቀን 2017 ዓ.ም የባህል ፌስቲቫል እንደሚዘጋጅም ተገልጿል፡፡

የጉራጌ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ ወይዘሮ መሠረት አመርጋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመጪው የመስቀል በዓል ከ800 ሺህ በላይ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገራት ቱሪስቶች ለመቀበል ዝግጅት ተደርጓል፡፡

የመስቀል በዓል በማህበረሰቡ ዘንድ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ይዘቱን ጠብቆ ሲከበር ቢቆይም፤ በዞኑ እንደ መንግሥት ባህሉ የበለጠ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገር ለማድረግ በተለያዩ ዝግጅቶች ላለፉት ስድስት ዓመታት ተከብሯል ያሉት ኃላፊዋ፤ የዘንድሮው ሰባተኛው ዙር አከባበርም በተለያዩ ተግባራት ለማክበር በቂ ዝግጅት እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

በክልል ደረጃ በመስቀል በዓል ቱሪዝምን ለማነቃቃት “መስቀል በጉራጌ” የባህል ፌስቲቫል ከመስከረም ዘጠኝ እስከ 12 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ በእኖር ወረዳ እንደሚከበርም አብራርተዋል፡፡

ከዚህም ጎን ለጎን ኢኮኖሚውን ማነቃቃት የሚችሉ ባዛርና ኤግዚቢሽኖች በወልቂጤ ከተማ እንደሚዘጋጅ ጠቁመዋል፡፡

ወይዘሮ መሰረት አክለውም፣ በኤግዚቢሽኑ ባህልን ሊያስተዋውቁ የሚችሉ የተለያዩ የእደ ጥበባት ውጤቶች፣ ባህላዊ ቁሳቁሶች፣ ባህላዊ ምግቦች እንዲሁም የኪነ ጥበብ ሥራዎች ይቀርባሉ ያሉ ሲሆን፤ በተጨማሪም ፋሽን ሾው፣ የባህልና የቋንቋ ሲምፖዚየም እንዲሁም የተለያዩ የፓናል ውይይቶች እንደሚቀርቡ ተናግረዋል፡፡

በዓሉ በፌስቲቫል ደረጃ መከበሩ የተደበቁ ባህሎች እንዲወጡ ለማስቻል፣ ባህልን በደንብ ለማስተዋወቅ እና የተጻፉ መረጃዎች ለትውልድ ለማስተላለፍ እንዳስቻለም ነው መምሪያ ኃላፊዋ ያብራሩት፡፡

እንደ ወይዘሮ መሠረት ገለጻ፤ በመስቀል በዓል ወደ አካባቢው ለሚመጡ እንግዶች የጉዞ እንግልት እንዳይኖር ብሎም አላስፈላጊ ወጪ እንዲሁም ከታሪፍ በላይ ክፍያ እንዳይኖር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን እየተሠራ ነው፡፡

የቱሪስቶች የቆይታ ጊዜን ለማራዘም እና ተገቢው አገልግሎት እንዲኖር ለማስቻል በተለይ ከመሰረተ ልማትና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከማስፋፋት አኳያም ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡

በዓሉ በሰላማዊ መንገድ እንዲካሄድ እንዲሁም ወደ ዞኑ ያመሩ ቱሪስቶች የሚፈልጉትን አገልግሎት እንዲያገኙ ለማስቻል በዞኑ ዋና አስተዳዳሪ የሚመራ ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ሥራ መግባቱን ጠቅሰዋል፡፡

በዞኑ የመስቀል በዓል ከፍተኛ የቱሪስት ፍሰት ያለበት በዓል መሆኑንም አስረድተዋል፡፡

# ለኑሮ ውድነት የተበጀ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ኮሚሽኑ ስርቆትንና ብልሹ አሠራርን በማስወገድ የተለያዩ የግብርና ምርቶችን በቀጥታ ከአምራቹ ማሳ ወደ አዲስ አበባ እንዲገቡ በማደረግ፤ ማህብረሰቡን የማገልገል ሥራ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ያብራራሉ፡፡

ማህበረሰቡን በፍትሕዊነት የማገልገል ሥራም በመዲናዋ የሚታየውን የምርት የዋጋ ንረት እያረጋጋ ይገኛል ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

የምርት አቅርቦት በሚገኝባቸው በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ቀጥተኛ የንግድ ትስስር በመዘርጋት፣ አምራቾች ምርታቸውን ለመዲናዋ ነዋሪዎች የሚያቀርቡበት አሠራር በፍጠር፤ ጥራት ያለው ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ የማደረግ ሥራ እየተሠራ ነው፤ ይህም የሚታየውን የኑሮ ውድነት እያስታገሰ ይገኛል ሲሉም ያብራራሉ፡፡

ለኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርቶችን በቀጥታ ከአርሶ አደሩ ማሳ ግብይት ፈጥረው በሸማች መጋዘን እንዲያከማቹ ፍቃድ መሰጠታቸውን በመጥቀስ፤ ከክልል ማህበራት ጋርም የግብይት ትስስር ፈጥረው የምርት አቅርቦት እጥረት እንዳይገጥም እንዲያደርጉ መሆኑን ነው የተናገሩት፡፡

ይህም ማህበረሰቡ ጥራት ያለው ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ ግብይት እንዲፈጥር እድል ከፍቷል ሲሉ ይናገራሉ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ በዓላት በተቃረቡ ቁጥር ጥቂት ነጋዴዎች ምርቶችን በመደበቅ የዋጋ ንረት እንዲፈጠር የማድረግ ሥራ እንደሚሠሩ በማንሳት፤ ምርትን በሚደብቁና የዋጋ ጭማሪ የሚያደርጉ ጥቂት ነጋዴዎች የሚፈልጉት የምርት አቅርቦት እጥረትና የዋጋ ቀውስ እንዳይከሰት በሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት መጋዘን በቂ የምርት ክምችት በማድረግ ለማህበረሰቡ ተደራሽ የማድረጋ ሥራ ተሠርቷል፤ እየተሠራም ነው ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

በመዲናዋ በበዓላት ወቅት የሚከሰትን ያልተጠበቀ የኑሮ ውድነት ለማርገብ አምራችና ሸማችን በቀጥታ የሚያገናኝ ኤግዚቢሽን እና ባዛር የማዘጋጀት ሥራ እየተሠራ መሆኑንም ይጠቅሳሉ፡፡

በበዓልም ሆነ በአዘቦት ወቅት የሚገጥምን የምርት እጥረት፣ የዋጋ ንረትና የአቅርቦት ችግርን ለመፍታት እየተሠራ ያለው ሥራ በመጪው አዲስ ዓመት ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡

የለሚ አዲስ ዩኒየን ምክትል ሰብሳቢ ፓስተር ፈለቀ ሞላ በበኩላቸው፤ በአዲስ አበባ ከተማ የሚስተዋለውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት በሸማች ኅብረት ሥራ ኮሚሽን በኩል ምርትን በቀጥታ ከአምራቹ ለሸማቾች በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ገበያውን የማረጋጋት ሥራ እየሠራ መሆኑን ነው የሚናገሩት፡፡

የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን በሸማች ኅብረት ሥራ ሱቆች እና በሰንበት ገበያዎች በየአካባቢው እንዲቀርቡ በማደረግ የዋጋ ንረትን ከማረጋጋት በተጨማሪ ማህበረሰቡን ከትራንስፖርት ውጪ የማዳን ሥራ እየተሠራ ነውም ይላሉ፡፡

በአንዳንድ ክልሎች ያለው የፀጥታ ችግር ምርት ወደ መዲናዋ በቀጥታ ለማስገባት ፈተና መሆኑን የሚጠቅሱት ፓስተር ፈለቀ፤ ያለውን ተግዳሮት በተለያዩ አማራጮች በመጠቀም ማለትም ሰላም ከሆኑ ክልሎችና ከአዲስ አበባ አቅራቢ ከሚገኙ አምራቾች የግብይት ትስስሮሽ ፈጥሮ ችግሩን መፍታት መቻሉን ያብራራሉ፡፡ የተለያዩ የግብርና ውጤቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለማህበረሰቡ ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየተከናወነ መሆኑንም ይገልጻሉ፡፡

የሸማቶች ማኅበራት ምርትን በተመጣጣኝ ዋጋና በጥራት ተደራሽ በማድረግ በኩል እየሠራ ያለው ሥራ ማህበረሰቡ በነጋዴዎች የሚደርስበትን የዋጋ ጫና እየፈታ እንደሚገኝ ነው የተናገሩት፡፡

በበዓላት ወቅት በመዲናዋ የሚከሰተውን የምርት አቅርቦት እጥረትና የዋጋ ግሽበት ለመከላከል የኢንዱስትሪ እና የግብርና ምርቶች የማከማቸት ሥራ ተሠርቷል፡፡ በመጪው የዘመን መለወጫ በዓልም አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኅብረት ሥራ ኮሚሽን በግብርና እና በኢንዱስትሪ ምርቶች የአቅርቦት ችግርና የዋጋ ንረት እንዳይከሰት እየሠራ ያለው ሥራ የሚበረታታ ነው ሲሉ የጉለሌ ክፍለ ከተማ የዩኒየኖች የቦርድ ሰብሳቢ መቶ አለቃ ታረቀኝ ለማ ነግረውናል፡፡

በመዲናዋ ከዕለት ወደ ዕለት እየተባባሰ የመጣውን የምርት የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት በሸማች ኅብረት ሥራ በኩል ከፍተኛ ሥራ እየተሠራ ነው፤ እየተሠራ ያለውም ሥራ ገበያውን ማረጋጋት የቻለ ነው ለማለት የሚያስደፍር ነው ብለዋል፡፡

መንግሥት ያደረገውን የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ተከትሎ የተስተዋለውን ምርት የመበደበቅና የዋጋ ጭማሪን በመከላከል ገበያን የማረጋጋት ሥራ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ተሠርቷል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አንዳንድ ነጋዴዎች ምርትን በከፍተኛ ዋጋ ለማህበረሰቡ በማቅረብ የኑሮ ውድነት እያባባሱ መሆኑን ጠቁመው፤ የኑሮ ውድነቱ እንዳይባባስ ሸማች ማህበራት እየሠሩት ያለውን ሥራ አጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል ይላሉ፡፡ መንግሥትም ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ አለበት ሲሉ ይመክራሉ፡፡


## ብሔራዊ ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር 01/2017

የሽመልስ ሃብቴ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የተለያዩ ለትምህርት ስራ የሚውሉ ፣ አላቂ የጽህፈት እቃዎች ሎት 1፣ለአላቂ የፅዳት እቃዎች ሎት 2፣ለደንብ ልብስ አቅርቦት እና ልብስ ስፌት አገልግሎት ሎት 3፣የስፖርት እቃዎች እና የኤሌክትሪክ እቃዎች ሎት 4፣5፣ ለህጻናት ዴኬር እቃዎች አቅርቦት ሎት 6፣ለቋሚ እቃዎች አቅርቦት ሎት 7፣የህንፃ መሳሪያዎች አቅርቦት እና የጥገና ስራዎች ከነሙሉ አክሰሰሪው የሚሰራ ሎት 8፣9፣ ለህትመት ስራዎች ሎት 10 በመስኩ የተሰማሩ ነጋዴዎች ባለሙያዎችን አወዳድሮ በግልፅ ጨረታ መግዛት እና ማሰራት ይፈልጋል፡፡

**ተጫራቾች ማሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች፡-**

- በተጠቀሰው እሴት ታክስ ተመዝጋቢ መሆናቸውን የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
- የጨረታ ማስከበሪያ የሚመለስ ወይም በባንክ በተረጋገጠ CPO ለሎት 1፣2 እና 3 1,500 (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር ብቻ) ለሎት 4፣5፣6 1000 (አንድ ሺህ ብር) ሎት 7 2000 (ሁለት ሺህ ብር)እና ለሎት 8፣9፣10 1000 (አንድ ሺህ ብር ብቻ)ማቅረብ ይጠበቅባችኋል፡፡
- ናሙና ለሚያስፈልጋቸው እቃዎች የጨረታ ሰነድ በሚያስገቡበት ወቅት ናሙና ማቅረብ አለባቸው፡፡ ናሙና ካላቀረበ ውድቅ የምናደርግ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- ዕቃዎቹን በመ/ቤቱ የግዥ የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 8 ድረስ ማቅረብ ይኖርባችኋል፡፡
- ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት ዘወትር በስራ ሰዓት ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል መውሰድ ይችላሉ፡፡
- የጨረታ መወዳደሪያ የአንዱ ዋጋ ቫት/ ተጨማሪ እሴት ታክስን ያካተተ መሆን አለበት፡፡
- ቫትን ያላካተተ ከሆነ ቫት እንዳካተተ ይቆጠርበታል፡፡
- ተጫራቾች ለጨረታ ሲመጡ የዘመኑን የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያለው፣የጨረታ ሰርተፍኬት ያለው፣የተሰማሩበት የስራ መስክ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና በምታስገቡት ሰነድ ላይ በእያንዳንዱ ፔጅ ላይ የድርጅቱን ክብ ማህተም ማድረግ ይኖርባችኋል፡፡ ከሌላችሁ ብትወዳደሩም መስሪያ ቤቱ ውድቅ የሚያደርግ መሆኑን ከወዲሁ እናሳውቃለን፡፡
- አሸናፊው ተጫራች ማሸነፉ ከተረጋገጠበት በ15ኛው ቀን ውል መፈፀምና 10% የውል ማስከበሪያ በጥሬ ገንዘብ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ተጫራቾች ሰነዳቸውን ዋናውንና ኮፒውን በታሸገው ኤንቨሎፕ በማድረግ ጨረታ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን እስከ 10ኛው ቀን እስከ 11፡00 ሰዓት ድረስ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ በዛው እለት በ11፡00 ሰዓት ተዘግቶ በቀጣዩ ቀን በ4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡

መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ፡-** ሜክሲኮ ከላንድማርክ ሆስፒታል አጠገብ ቂ/ክ/ከ/አስ ሽመልስ ሃብቴ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት

ስልክ ቁጥር 011 5 57 47 36/ 011 5 51 94 13 /011 5 57 44 67

**በቂርቆስ ክ/ከተማ አስተዳደር በወረዳ 10 የሽመልስ ሃብቴ**
**አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት**

# ኢንቨስትመንት

# ‹‹አዲስ ቱሞሮ›› - የነገዋ አዲስ አበባ አዲስ የገፅታና የኢኮኖሚ አቅም

አንተነህ ቸሬ

ሀገራት የኢንቨስትመንት ዘርፋቸውን በማሳደግ ጥቅል አገራዊ እድገታቸውን ዘላቂ ለማድረግ ከሚተገብሯቸው አሰራሮች መካከል አንዱ ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎችን (Special Economic Zones) ማቋቋም ነው። ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች የሚፈጥሩትን የስራ እድል፤ ለአገር በቀል የሎጂስቲክስ ኢንዱስትሪው መስፋፋት የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ፤ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰትን፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን፣ የባለሙያዎችንና የሠራተኞችን ክህሎት ለማሳደግ እንዲሁም የዋጋ ግሽበትን ለመቀነስ የሚኖራቸውን ወሳኝ ሚና እንዲሁም የወጪና ገቢ ንግድን ለማቀላጠፍ ያላቸውን አበርክቶ በአጠቃላይ ለሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት መሻሻል የሚኖራቸውን ጉልህ ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት አገራት ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎችን ያቋቁማሉ፣ ያስፋፋሉ።

የምጣኔ ሃብት ሳይንስ ጥናቶች እንደሚያስረዱት፤ ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች ኢንቨስትመንትን በማሳደግ ለስራ እድል ፈጠራ፣ ለምርት አቅርቦት እና ለውጭ ምንዛሬ ግኝት ከፍተኛ አዎንታዊ አስተዋፅዖ ያበረክታሉ። የእነዚህ ቀጣናዎች ዋና ዋና ዓላማዎች የስራ እድል ፈጠራን እና ምርትንና ምርታማነትን መጨመር፣ የወጪ ንግድን ማስፋትና የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ እንዲሁም ካፒታልና ቴክኖሎጂን መሳብ ናቸው። ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች የራሳቸው የምርት ስፍራ/ወሰን፣ የአስተዳደር ስርዓት፣ የታክስ ሕግጋት እና የጉምሩክ ስርዓት አላቸው። ቀጣናዎቹ በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ፣ በጥሬ እቃ አቅርቦት እንዲሁም በምርት አቅርቦትና ግብይት ተግባራት ላይ የሚሰማሩ አካላትን ቁጥር ይጨምራሉ። ይህም የልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች ልማት ከኢንቨስትመንት እድገት ጋር ቀጥተኛ ትስስር እንዳለው ማሳያ ነው።

ኢኮኖሚያዊ ትስስር ስር እንዲሰድ ለማድረግ እንዲሁም የግብርና ልማትን፣ የምግብ ዋስትናን፣ የኢንዱስትሪ ልማትንና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት ወሳኝ የሆነውንና የሰዎች፣ የካፒታል፣ የእቃዎችና አገልግሎቶች ነፃ እንቅስቃሴ የሰፈነበት አህጉራዊ ገበያ ለማምጣት ያለመው ‹‹አጀንዳ 2063›› ስኬታማ እንዲሆን ነፃ የኢኮኖሚ ቀጠናዎች ልማት አስፈላጊ እንደሆነ በአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት መመስረቻ ሰነድ ላይ ተጠቅሷል። ከዚህ በተጨማሪም ለንግድና ኢንቨስትመንት በቂ መሰረተ ልማት ለመዘርጋት እንዲሁም ቀረጥን በመቀነስ ወይም ደረጃ በደረጃ በማስወገድ እና ለንግድና ኢንቨስትመንት ማነቆ የሆኑትን ቀረጥ ያልሆኑ መሰናክሎችን ለማስወገድ በስምምነቱ አባል ሀገራት ዋስትና ያለው የእቃዎችና አገልግሎቶች ገበያ ለመፍጠርና ለማስፋፋትም ነፃ የኢኮኖሚ ቀጠናዎች ወሳኝ ሚና እንዳላቸው በሰነዱ ላይ ተመላክቷል።

ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች የግል (Private) እና የመንግሥት (Public) ኢንቨስትመንቶችን በማበረታታት የኢንቨስትመንት ዘርፉ እንዲያድግ ያስችላሉ። ቀጣናዎቹ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን (Foreign Direct Investment - FDI) በመሳብ የግል ባለሃብቶች በስፋት በኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ ያደርጋሉ። በሌላ በኩል ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች ሰፊ የመሰረተ ልማት ዝርጋታዎችን የሚፈልጉ በመሆናቸው መንግሥት በመሰረተ ልማት ኢንቨስትመንት (Infrastructural Investment) ላይ እንዲሰማራ በማድረግ የመንግሥት ኢንቨስትመንት እንዲነቃቃ እድል ይፈጥራሉ። በአጠቃላይ ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች ለባለሃብቶች ምቹ እድሎችን የሚፈጥሩ በመሆናቸው ባለሃብቶች በኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሰማራት ተነሳሽነት ይኖራቸዋል።

በልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች ውስጥ የሚተገበሩ ሕጋዊ አሰራሮች ቀለል ያሉና ቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረዶችን የሚቀንሱ በመሆናቸው ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ለመሰማራት የሚያደርጉትን ጥረት በአንፃራዊነት ቀላል ያደርጉላቸዋል። በነፃ የንግድ ቀጣናው ውስጥ ገብተው የሚሠሩ ባለሀብቶች፣ አስመጪና ላኪዎችም ሆኑ ድርጅቶች የልዩ ልዩ ማበረታቻዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ። ይህ ደግሞ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ ጉልህ ሚና ይኖረዋል።

ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር እንዲሁም መሬትን ጨምሮ ሌሎች እምቅ ሀብቶች ያላት ኢትዮጵያ ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎችን በማቋቋም ረገድ በመዘግየቷ ከእነዚህ ቀጣናዎች ልማት ማግኘት የሚገባትን ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅም ማጣቷ ተደጋግሞ ሲገለፅ ቆይቷል። የሀገሪቱን የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ እግር ከወርች አስረው የያዙት አንዳንዶቹ መሰናክሎች ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች በሚያስገኟቸው ጥቅሞች የሚፈቱ ናቸው። ስለሆነም ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎችን በማቋቋም የሀገሪቱን ተጠቃሚነት ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች ለማልማት የሚያስችሉ ስራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል።

የልዩ ኢኮኖሚ ቀጣናዎች ልማት በሕጋዊ ማዕቀፍ የተደገፈ እንዲሆን የሚያስችሉ ብሔራዊ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ፖሊሲ እና የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጅ (1322/2016) ተዘጋጅተው ወደ ስራ ተገብቷል። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ነሐሴ 27 ቀን 2014 ዓ.ም ባካሄደው 11ኛ መደበኛ ስብሰባው፣ በብሄራዊ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ረቂቂ ፖሊሲ ሰነድ ላይ ውይይት በማድረግ፣ ፖሊሲው በሥራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል። ምክር ቤቱ ፖሊሲው በስራ ላይ እንዲውል ውሳኔ ያሳለፈው ኢትዮጵያ ለአገራዊ የኢኮኖሚ እድገት የጎላ አስተዋፅዖ ባለውና ከጊዜ ወደ ጊዜ በፍጥነት እየተስፋፋና እየጎለበተ በመጣው ዓለም አቀፍ እና ቀጣናዊ የንግድ ትስስር ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንድትሆን አስቻይ ሁኔታዎችን መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ ነው። ፖሊሲው የአገሪቱን የወጪ ንግድ ስርዓት ለማሻሻል፣ የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ስበትን ለማሳደግ፣ የወጪ ንግድ አቅምን ለማጎልበት፣ ሰፊ የስራ እድሎችን ለመፍጠር እንዲሁም በአገሪቱ ዋና ዋና የንግድ ኮሪደሮች የደረቅ ወደቦችን ለማስፋፋትና የሎጂስቲክ አገልግሎትን ለማቀላጠፍ የሚያግዙ ስርዓቶችን እውን ለማድረግ የሚያስችል እንደሆነም ተገልጿል።

ከዚህ በተጨማሪም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ 10 ቀን 2016 ዓ.ም ባካሄደው ሦስተኛ ዓመት የሥራ ዘመን 21ኛ መደበኛ ስብሰባው የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጅን አፅድቋል። የውጭ ኢንቨስትመንትን በቀላሉ ለመሳብ፣ ሰፊ የስራ ዕድል ለመፍጠር፣ የአምራች ዘርፉን ለማበረታታት፣ የምጣኔ ሀብት ትስስርን ለማጠናከር፣ የውጭ ምንዛሪ ገቢን ለማሳደግ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማሳለጥ እንዲሁም ተግባራዊ የተደረገውን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ስርዓት ዲዛይንና ትግበራ ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስርዓት በማሳደግ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ከፍ ለማድረግ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው ተገልጿል።

እነዚህን የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ፋይዳዎችን እንዲሁም የፖሊሲና አዋጅ ዝግጅቶችን መሰረት በማድረግ በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች ግዙፍ የሆኑ የልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ግንባታዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። በአዲስ አበባ ከተማ የሚገነባው ‹‹አዲስ ቱሞሮ›› ልዩ የኢኮኖሚ ዞን እና ግንባታው በኦሮሚያ ክልል የሚከናወነው ‹‹ገዳ›› ልዩ የኢኮኖሚ ዞን የዚህ እንቅስቃሴ ማሳያዎች ናቸው።

ግንባታው በአዲስ አበባ፣ ጎተራ አካባቢ፣ በ35 ሄክታር መሬት ላይ የሚያርፈው ‹‹አዲስ ቱሞሮ›› ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣና (Addis Tomorrow Special Economic Zone)፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በቻይናው ‹‹ቻይና ኮሚዩኒኬሽንስ ኮንስትራክሽን›› ኩባንያ (China Communications Construction Company - CCCC) ሽርክና የሚገነባ ግዙፍ ፕሮጀክት ሲሆን፣ የባህል፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፓርክ እንዲሁም የቢዝነስና የንግድ፣ የመኖሪያና የመዝናኛ ማዕከላትን ያካትታል። ልዩ የኢኮኖሚ ዞኑ በግሉ ዘርፍና በመንግሥት ሽርክና ከሚገነቡ ግዙፍ የልማት ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ ሲሆን፣ በአዲስ አበባ በተለያዩ አካባቢዎች ከሚከናወኑ የልማት ስራዎች ጋር ተቀናጅቶ የሚተገበር ነው።

**የምጣኔ ሃብት ሳይንስ ጥናቶች እንደሚያስረዱት፤ ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች ኢንቨስትመንትን በማሳደግ ለስራ እድል ፈጠራ፣ ለምርት አቅርቦት እና ለውጭ ምንዛሬ ግኝት ከፍተኛ አዎንታዊ አስተዋፅዖ ያበረክታሉ**

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ግንባታውን ባስጀመሩበት ወቅት፣ ልዩ የኢኮኖሚ ዞኑ አዲስ አበባን እንደስሟ ውብና አዲስ ለማድረግ የሚከናወኑ ተግባራት አካል እንደሆነ ተናግረዋል። አዲስ አበባን ውብና አዲስ ለማድረግ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል አንዱ በግልና በመንግሥት አጋርነት የሚሰሩ በከተማ ውስጥ ያሉ ከተሞችን መገንባት እንደሆነ የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፣ እነዚህ ፕሮጀክቶች የነገዋን አዲስ አበባን መልክ የሚያሳዩ በመሆናቸው ከፍተኛ ሀብት የሚጠይቁ፣ የተለየ ዲዛይን ያላቸው፣ በሰፋፊ ቦታዎች ላይ የሚገነቡ፣ እጅግ ማራኪ የሆኑ እንዲሁም አስፈላጊ መሰረተ ልማቶችን የያዙ እንደሆኑ አስረድተዋል።

‹‹አዲስ ቱሞሮ›› ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ረዘም ያለ ጊዜ የወሰዱ ንግግሮች የተደረጉበት መሆኑን አስታውሰው፣ ግንባታው መጀመሩ አዲስ አበባን ውብና ተመራጭ የማድረግን ዓላማ ለማሳካት አጋዥ እንደሚሆን ገልፀዋል። ‹‹በግሉ ዘርፍ ከፍተኛ መነቃቃት እየታየ ነው። በቅርቡ የተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርም የግሉ ዘርፍ በብዛት ኢትዮጵያ ውስጥ በኢንቨስትመንት ላይ እንዲሰማራ በር የሚከፍት ነው። የምንዛሬ ገበያው እንዲስተካከል እያደረገ እንዲሁም ብዙ ሕገ ወጥ ስራዎችን ወደ ሕጋዊነት እያመጣ ነው። በዶላርና በብር መካከል ያለውን ያልተገባ ዝምድና ለማረቅ የሚያግዝ ነው። ኤክስፖርት በማድረግ፣ ገቢን በማስገባትና በማስፋት፣ አዳዲስ ኢንቨስትመንት በመሳብ፣ ከውጭ የሚላክ ገንዘብ (ሬሚታንስ) በሕጋዊ መንገድ እንዲመጣ በማድረግ ኢኮኖሚያችንን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያነቃቃ ይጠበቃል። ‹አዲስ ቱሞሮ› ልዩ የኢኮኖሚ ዞንም የዚሁ አካል ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል›› ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው፣ ፕሮጀክቱ የአዲስ አበባን ገፅታ የመቀየርና የሕዝቡን ሁለገብ ተጠቃሚነት የማሳደግ ጥረት አካል እንደሆነ ተናግረዋል። ‹‹ግንባታው የተጀመረው ‹አዲስ ቱሞሮ› ልዩ የኢኮኖሚ ዞን በከተማችን ውስጥ አዲስ ከተማን የመገንባት ያህል ግዙፍ ፕሮጀክት ሲሆን እንደቀደሙት ፕሮጀክቶች ሁሉ ለከተማችን አዲስ ገፅታን የሚያላብስ፣ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነቷን የሚያጎላ፣ ተጨማሪ የውበት ምንጭ የሚሆን፣ በርካታ የስራ እድሎችን የሚፈጥር፣ ንግድን የሚያሳልጥ፣ ትልቅ ዓለም አቀፍ የግብይት ማዕከልን ለከተማችን የሚጨምር እንዲሁም መኖሪያ ቤቶችንና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ጨምሮ በርካታ መሰረተ ልማቶችን የያዘ ነው›› ብለዋል።

ከለውጡ ማግሥት ጀምሮ አዲስ አበባን እንደስሟ ውብ፣ አበባ ለማድረግ በማለም በርካታ ስራዎች መሰራታቸውን የጠቆሙት ወይዘሮ አዳነች፣ በየዓመቱ እየተጠናቀቁ ለአገልግሎት የበቁ የሕዝቡን የኑሮ ጫና ያቃለሉ ፕሮጀክቶችን ጨምሮ የከተማዋን ጎስቋላ ገፅታ የቀየሩ፣ ሰፋፊ የስራ እድሎችን የፈጠሩ፣ አገልግሎቶችን ያሳለጡና ገቢን ያሳደጉ ሜጋ ፕሮጀክቶች የስኬቶች ማሳያዎች እንደሆኑ አስረድተዋል። ይህ ጉልህ ስኬት ሊመዘገብ የቻለው መንግሥት የመፈፀም አቅሙን በማሳደግ፣ ብክነትን በመቀነስ፣ የልማት አጋሮችንና የሕዝባችንን ሁለንተናዊ አቅም በማስተባበር እንደሆነም ገልፀዋል።

የ‹‹አዲስ ቱሞሮ›› ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ግንባታን የሚያከናውነው የ‹‹ቻይና ኮሚዩኒኬሽንስ ኮንስትራክሽን›› ኩባንያ ምክትል ስራ አስኪያጅ ቼን ዦንግ፣ የፕሮጀክቱ ግንባታ ትብብርን በሚያጠናክር እንዲሁም የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግርን በሚያሳልጥ መልኩ እንደሚከናወን ገልፀዋል። ‹‹የኩባንያችንን እውቀትና ሃብት የኢትዮጵያን ሕዝብና መንግሥት ተጠቃሚ ለማድረግ እናውለዋለን›› በማለት ተናግረዋል። የኢኮኖሚ ዞኑ ሕዝብ ተኮር፣ ዘመናዊና ጤናማ ከተማን ለመፍጠር እንደሚያስችልም ገልፀዋል።

ኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ጥቅም ከሚሰጠው ከልዩ የኢኮኖሚ ቀጣና ስርዓት ርቃ መቆየቷ ብዙ ጥቅሞችን አሳጥቷታል። የእነዚህ ጥቅሞችና እድሎች መታጣት ደግሞ በአጠቃላይ እድገቷ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳሳደረባት አይካድም። በሀገሪቱ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደሩ ያሉት አንዳንዶቹ መሰናክሎች ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎችን በማቋቋም ቀጣናዎቹ በሚያስገኟቸው ጥቅሞች የሚፈቱ ናቸው። ስለሆነም ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎችን ለማቋቋም የተጀመሩትን ጥረቶች በማጠናከር ሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገቱ ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲያስመዘግብ ማድረግ ይገባል።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ጎሜ

# ተቋማትን ከማጠልሸት ጀርባ ያሉ ስውር ደባዎች

**እስማኤል አረቦ**

ጠንካራ ተቋማት የጠንካራ ሀገር መሰረቶች ናቸው። የጠንካራ ተቋማት ባለቤት የሆኑ ሀገራት ጽኑ መሰረት ያላቸው በመሆኑ ሀገርን ከትውልድ ወደ ትውልድ ያሸጋግራሉ፤ የሀገርን ገጽታ ይገነባሉ፤ ዓለም አቀፍ ተጽዕኖም ይፈጥራሉ፤ ቋሚ አምባሳደር ሆነውም ሀገርን ያስተዋውቃሉ። በአጠቃላይ የሀገር መለያ ሰንደቅ ዓላማ ተደርገው ይወሰዳሉ።

ይህንኑ በመረዳት ኢትዮጵያም ዘላቂ የሆኑ ተቋማትን ለመገንባት ጥረት በማድረግ ፩ ላይ ትገኛለች። መንግስት በተቀያየረ ቁጥር የማይቀያየሩ፤ ዛላቂነት ያላቸውና በየትኛውም ግዜና ቦታ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ከፍ አድርገው የሚያስተዋውቁ ተቋማትን ለመፍጠር ዘርፈ ብዙ ጥረቶች እየተደረጉ ነው። በዚህ ረገድም ዓለም አቀፍ ዕውቅናን ያገኙ ተቋማት ከመኖራቸውም ባሻገር ከወዲሁም የብዙዎችን ቀልብ መሳብ የቻሉና ከኢትዮጵያም አልፈው አፍሪካን ማኩራት የሚችሉ ተቋማትም ብቅ ብቅ እያሉ ነው።

ዓለም አቀፍ እውቅናን ካገኙና ከኢትዮጵያ አልፈው የአፍሪካ ኩራት ከሆኑ ተቋማት ውስጥ አንዱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ነው። የኢትዮጵያ አየር መንገድ መንግስታት በተቀያየሩ ቁጥር የማይዋዥቅና ጥንካሬውንም አስጠብቆ ከዘመን ወደ ዘመን መሸጋገር የቻለ የጠንካራ ተቋማት ምሳሌ ነው።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በኢንዱስትሪው የአቪዬሽን ኦስካር ተብሎ በሚጠራው የስካይትራክስ መድረክ ለ7ኛ ጊዜ የአፍሪካ ምርጡ አየር መንገድ ሽልማትን አሸንፏል። አየር መንገዱ በተጨማሪም የአፍሪካ ምርጥ የቢዝነስ ክፍል አየር መንገድ ሽልማትን ለ6 ተከታታይ ዓመታት ማሸነፍ ችሏል።

እንዲሁም አየር መንገዱ የአፍሪካ ምርጥ የኢኮኖሚ ክፍል አየር መንገድ ሽልማትን ለ6 ተከታታይ ዓመት ለማሸነፍ በቅቷል። ከዚህ ባለፈም በአፍሪካ የኢኮኖሚ ክፍል ምርጥ ምግብ አገልግሎት ሰጪ አየር መንገድ ሽልማትን አሸንፏል።

ሆኖም ይህ የአፍሪካ ኩራት የሆነው አየር መንገድ ከውጭና ከውስጥ ጠላቶች በተደረገ ቅንጅት ስሙን የማጥፋት ዘመቻ ከተከፈተበት ሰነባብቷል። የኢትዮጵያን እድገትና ብልጽግና የማይመኙ ሀገራት ከውስጥ ባንዳዎች ጋር በመተባበር በረባ ባልረባው የአየር መንገዱን ስምና ዝና የማጠልሸት ደባ ውስጥ ገብተዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግዙፍና ዘመናዊ የአቪየሽን ዘርፍ ነው። በተወዳደረበት መስክ ሁሉ የሚያሸንፍና ከኢትዮጵያም አልፎ የአፍሪካ ኩራት የሆነ ተቋም ነው። ሆኖም ከዚህ ግዙፍ አየር መንገድ ጋር ተወዳድረው ማሸነፍ ያልቻሉና አልፎ ተርፎም የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ መጉዳት የሚፈልጉ ሀገራትና አካላት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የአየር መንገዱን ዝና ለማጠልሸት በርካታ ዘመቻዎችን በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

ጥቂቶቹን ለማስታወስ ሰኞ ነሐሴ 09/2014 ዓ.ም. ከሱዳን የተነሳ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የመንገደኞች አውሮፕላን አብራሪዎች "እንቅልፍ ጥሏቸው" መዳረሻቸውን አልፈው እንደነበር የሚያወሳ ዘገባ ተሰራጭቶ ነበር። በተደረገው ማጣራትም ዘገባው ሀሰት መሆኑ ተደርሶበታል።

ከጥቂት ሳምንታት በፊት የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን ውስጥ የተቀረጸው ተንቀሳቃሽ ምሥል አንዲት ተሳፋሪ በአየር መንገዱ ሠራተኞች ከአውሮፕላኑ እንድትወርድ ስትጠየቅ እና ተሳፋሪዋ አልወርድም እያለች ከሠራተኞቹ ጋር የምታደርገውን የተካረረ ክርክር የሚያሳይ ምስል ተጋርቶ ነበር። ይህንን ጉዳይ በዋነኛነት ታዋቂው ኬንያዊ የሲንኤንኤን ጋዜጠኛ ላሪ ማዶዎ ጉዳዩን ከልክ በላይ ሲያጦዘው ነበር። ይህ ጋዜጠኛ በዚህ ልክ ጉዳዩን ማጦዙ ከጋዜጠኝነት ሙያው ይልቅ ጉዳዩን መወዳደር የተሳነውን የኬንያን አየር መንገድ በአቋራጭ ለመጥቀም የተደረገ ሴራ መሆኑን ልብ ይሏል።

ሰሞኑን ደግሞ በአየር ጸባይ ለውጥ ምክንያት ወደ መቀሌ የሚጓዝ የሀገር ውስጥ በረራ ጉዞ መቋረጥን ምክንያት በማድረግ አየር መንገዱን የሚያብጠለጥሉ ሰዎች ስድብና ዛቻ የማህበራዊ ሚዲያው ዋነኛ አጀንዳ ነበሩ።

በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያን አየር

> **ዘመን አመጣሾቹ የኢትጵያ ጠላቶች በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ በመቆም ጉዞዋን ለማደናቀፍ በብዙ ደክመዋል። ጠንካራ ተቋማትን በማጠልሸት የኢትዮጵያን የእድገት ጉዞ ለማሰናከል ከጠላት ጋር አብረው ትውልድ ይቅር የማይለው ደባ ፈጽመዋል**

መንገድ ዝና ጥላሸት ለመቀባት የሚደረጉ ጥረቶች በተቀናጀ መልኩ እየተፈበረኩ ነው። ከግለሰቦች አልፎም ሀገራት ጭምር ጥቃቅን ሰበቦችን እየፈለጉ የአየር መንገዱን ዝና የሚያወርዱ መረጃዎችን ሲያሰራጩ ለመመልከት ችለናል።

ሆኖም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዘመን ተሻጋሪ ልምድ እና እውቀት ያለው ተቋም በመሆኑ በወሬ የሚረታ ቁመና የለውም። ስለሆነም እንደትላንቱ ሁሉ ዛሬም ሆነ ነገ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አንግቦ በአፍሪካ ሰማይ ላይ ይነግሳል።

ሌላኛው የስም ማጥፋት ሰለባ እየሆነ ያለው ተቋም የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ነው። የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት 116 ዓመታትን ያስቆጠረ ዕድሜ ጠገብ ተቋም ነው። የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ጀግንነት መለያው፤ ድል ማድረግ ዓርማው ነው። የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በተሰማራበት የግዳጅ ቀጠና የማይደረምሰው ተራራ፤ የማይወጣው አቀበት፤ የማያሸንፈው ጠላት የለም። ይህን እንኳንስ ወዳጅ ጠላትም የሚመሰክረው ነው።

ሆኖም የውጭና የውስጥ ጠላቶች በመቀናጀት የሰራዊቱን ስም ለማጠልሸት ሲሯሯጡ ይታያሉ። ሰራዊቱ ያለመገለጫውና ያለተግባሩ መገለጫ ለመስጠትና ለማጠልሸት የሚሞክሩ የውጭ ጠላቶችና በገንዘብ የተገዙ ባንዳዎች ብዙ ናቸው። ሆኖም ከሕዝብ አብራክ የወጣውና የጀግኖች ስብስብ የሆነው የመከላከያ ሰራዊት በወሬና በአሉባልታ የሚረታና የሚናድ አይደለም።

ይልቁንም ከጊዜ ወደ ጊዜ በድል ላይ የድል አክሊል እየደረበ የሕዝብ ጥቅምንና የሀገር ሉአላዊነቱን የማስጠበቅ ቁመና ከምንግዜውም በላይ ጎልብቶ ይገኛል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ከሕዝብ አብራክ የወጣ በመሆኑ ሁልጊዜም ሕዝባዊና ሀገራዊ ተልዕኮዎችን አንግቦ ይንቀሳቀሳል። የሀገሪቱን ሉአላዊነትን ለማስከበርና የዜጎችን ሰላም ለማረጋገጥ መስዋዕትነትን ይከፍላል። በዱር በገደሉ ይዋደቃል። ደሙን ያፈሳል፤ አጥንቱን ይከሰክሳል። ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነትን ያስቀጥላል።

እንደ አየር መንገድ እና የመከላከያ ሰራዊት ሁሉ የውጭ ጠላቶችና የሀገር ውስጥ ባንዳዎች የስም ማጥፋት ዘመቻ የተከፈተበት ሌላኛው ተቋም የአባይ ግድብ ነው። የአባይ ግድብ በአፍሪካ ግንባር ቀደሙ የኃይል ማመንጫ ሲሆን ግድቡ ከኃይል ማመንጫነቱ በሻገር የአይበገሬነትና የአልሸነፍ ባይነት ተምሳሌትም ተደርጎ ይወሰዳል።

እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር 2003 ላይ ጅማሬው የተበሰረው የአባይ ግድብ ከ15 ዓመታት በኋላ ወደ ፍጻሜው ተቃርቧል። ሆኖም ግድቡ የመሰረት ድንጋይ ከተጣለበት ጊዜ አንስቶ እስካሁኗ ሰዓት ድረስ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ኢትዮጵያ ግድቡን እንዳታጠናቅቅ በብዙ ተደክሟል።

በተለይም የኢትዮጵያ፣ ግብጽና ሱዳን የሶስትዮሽ ድርድር ሁሌም እንከን እንዲኖረው በግብጽ በኩል በብርቱ ሲሰራበት ሰንብቷል። ከመነሻው ጀምሮ ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ ምንም አይነት የልማት ሀሳብ እንዳይኖራት ለዘመናት ስትባዝን የኖረች ግብጽ፣ የሕዳሴ ግድቡ የመሰረት ድንጋይ ሲቀመጥ በኢትዮጵያ ላይ የማስፈራሪያና የማስጠንቀቂያ ዶፍ ስታዘንብ መክረሟ የሚታወቅ ነው።

ከማስፈራራትና ከያዙኝ ልቀቁኝ በኋላ ዶሴዋን በመያዝ፤ ' ሲሆን ሲሆን ግድቡ እንዳይገነባ በማደርገው ጥረት ከጎኔ ይቆማሉ፤ ካልሆነም ኢትዮጵያ ላይ ጫና ያሳድሩልኛል' ወዳለቻቸው አካላትም፤ አገራትም ዘንድ ተንከራትታለች። ይሁንና ኢትዮጵያ በግብጽ ግልምጫም ሆነ ዛቻ እንዲሁም በሌሎቹ አገራት ጫና ከአቋሟ ዝንፍ ሳትል ግንባታዋን ሌት ተቀን ስታስኬደው ከርማለች።

ነገር ግን በዚህ ሁሉ ውስጥ ያጋጠማት ፈተና በርከት ያለ ከመሆኑም በላይ በየምክንያቱ ብዙ ነገሮችን እንድታጣ ተደርጋለች። በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ኢኮኖሚዋ እንዲዋዥቅ በብዙ ተጥሯል። ምክንያቱ ሌላ ይምሰል እንጂ በአገር ቤትም ሆነ በውጭ አገር ባሉ ዜጎቿ ጫና ተፈጥሯል።

ግብጽ የሕዳሴ ግድቡን ወደጸጥታው ምክር ቤት በማመላለስ ኢትዮጵያ በብዙ ጫና ውስጥ እንድታልፍ ከማድረጓም በተጨማሪ ሐሰተኛ በሆነ መረጃዋ፤ አንዳንድ አቅላቸውን በሳቱ አካላት ግድቡ በቦንብ እንዲጋይ እስከማሰብ ተደርሷል። ስለ ዓባይ ግድብ ምንም የማያገባው የአረብ ሊግም በጉዳዩ ላይ ተደጋጋሚ መግለጫ እስከማውጣት ደርሷል።

ከዚህ በሻገርም በሀገር ውስጥ ጭምር ሰዎችን በገንዘብ በመግዛት ሁከትና ረብሻ እንዲስፋፋ እና ኢትዮጵያ እንድትፈራርስ በብዙ ተደክሟል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶር) ሰሞኑን እንደተናገሩት ከሞላ ጎደል 15ሺ የሚሆኑ በገንዘብ የተገዙ ሰዎች የሕዳሴውን ግድብ ለማስተጓጎል በኢትዮጵያ ተሰማርተው ነበር። እነዚህ ሰዎች በየሚዲያው በመውጣት፤ በየማህበራዊ ሚዲያውና በየዩቱቡ በመገኘት ያልተቋረጠ አሉባልታና ስም የማጥፋት ዘመቻ ሲያደርጉ ቆይተዋል፤ አሁንም በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

በአጠቃላይ የአባይ ግድብ ከዳር እንዳይደርስ የውጭና የውስጥ ኃይሎች ሲያደርሱት የነበረውን ተጽዕኖ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደሚከተለው ገልጸውት ነበር። ‹‹ሲሚንቶ ከማምረት አጓጉዞ እዚህ ቦታ እስካለው ሥራ 15 ሺህ የሚጠጋ የተለያየ ስም ያላቸው በመነሻነት የኛ የሆኑ፤ ግን የተገዙ፣ የተሸጡ ሰዎች ይሄ ሥራ አሁን ያለበት ደረጃ እንዳይደርስ፣ እንዳይቋጭ ብዙ ጊዜ እና ገንዘብ ሕይወት አጥፍተዋል።

ብዙ አልተናገርንም፤ ምክንያቱም ለንግግር አይመችም። አሁንም ዘርዝሬ አልገልጸውም። ነገር ግን ሰው ለግንዛቤ እንዲያመቸው አንድ ተርባይን ሲመረት፣ ሲገዛ፣ ከፋብሪካው ጅቡቲ እስኪደርስ ያለውን ጣጣ ትቼ ያው ገንዘቡም ችግር ነው። ከተመረተም በኋላ ጅቡቲ ማድረሱም ከባድ ነገር ነው። እሱን ትቼ ከጅቡቲ ወደብ ያለውን ሂደት ጨርሼ እዚህ ቦታ ለማድረስ ምን ያክል ቀን የሚወስድብን ይመስላችኋል፤ በትንሹ 45 ቀናት አካባቢ ይፈጅብናል። አንድ ተርባይን ከጅቡቲ ተነስቶ እዚህ እስኪመጣ በዝቅተኛ 25 ኪሎ ሜትር በቀን ይጓዛል በጣም በከፍተኛ ከተጓዘ 40 ኪሎ ሜትር በቀን ይጓዛል።

በየ40 ኪሎ ሜትሩ እያደረ ነው የሚመጣው፣ ከዚህ ጅቡቲ ስንት እንደሆነ ማስላት ይቻላል። በየ40 ኪሎ ሜትሩ አንድ አንድ ቀን ይፈጅበታል። ትልቅ ነው መኪናው የተለየ ነው። በፍጥነት መጓዝ አይችልም በጣም ሳይፈጥን እንደ ሰው ቀስ እያለ ነው የሚጓዘው አንድ ተርባይን ከጅቡቲ አንቀሳቅሰን እዚህ ለማድረስ 45 ቀናት ይፈጅብናል። ይህ በመደበኛው መንገድ መኪኖቹ ምንም እንቅፋት ሳይገጥማቸው ሲጓዙ ነው።

ነገር ግን ላለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ተርባይኑ ቀርቶ ሲሚንቶ ከደርባ እዚህ ስናመጣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር እያዳንዱን መንገድ አስፓልት ስላልሆነ ለእያንዳንዱ ትራክ ፈንጂ እየለቀመ አልፎ አልፎም አደጋ ሲያጋጥም እየተጋፈጠ ፈንጂ እየለቀመ ነው የሚጓዘው። ከደርባ ተጭኖ ዝም ብሎ እዚህ አይደርስም።

አንዳንድ ጊዜ 20፣30ና 40 መኪና እየጫነ፣ እያዳንዷን መኪና እየፈተሸ ነው ትራንስፖርት አድርገው እዚህ የሚደርሱት። ፈንጂ ስለሚቀበር በየመንገዱ። መሀል ላይ መንገድ ተበላሽቶብን ነበር መንገዶቹ ፒስታ ስለነበሩ ተበላሽተው ጠጋኝ ኮንትራክተር አላገኘንም፣ ብዙዎቹ ኮንትራክተሮች ካለው መሠረታዊ ችግር አንጻር አልፈለጉትም።

መከላከያ መንገድ እየጠገነና እየሠራ ፈንጂ እየለቀመና ትራንስፖርት እያደረገ በየቦታው ደግሞ የሚያጋጥመውን ችግር እየተዋጋ ነው ይህንን ግድብ ያጠናቀቀው። ብዙ አልቅሰንበት፣ ደክመንበት፣ ደምተንበት ነው የሠራነው።››ሲሉ የሁኔታውን አስቸጋሪነት አብራርተዋል።

ሆኖም የእነዚህ ሀገራትና እነሱ የላኳቸው ሰዎች ምኞት ሳይሞላ ኢትዮጵያውያን ግድቡን ወደ ማጠናቀቅ ደረጃ ደርሰዋል። ዛሬ የሕዳሴ ግድብ ወደ ኋላ ከ205 እስከ 210 ኪሎ ሜትር ተኝቷል። ዛሬ የሕዳሴ ግድብ ወደታች ጥልቀቱ መቶ 133 ሜትር ደርሷል። ዛሬ ሕዳሴ ግድብ የጣናን ሀይቅ እጥፍ አድጓል። ጣና እስከ 30 ቢሊዮን ነው። ይሄ 62 ነጥብ አምስት ነው፤ ደብል አድርጓል። የጣና ውሃ ስፋቱ ብቻ ሳይሆን በጣም ሻሎው ነው። 13፣ 14 ሜትር ነው ጥልቀቱ። ይሄ 133 ገደማ ሜትር ጥልቀት አለው። በጣም ጥልቅ ነው ማለት ነው። ወደታችም ወደኋላም ወደጎንም በጣም ሰፊ ስለሆነ የጣናን እጥፍ/ደብል ውሃ ሆኗል።

በአጠቃላይ ከጥንት እስከ ዛሬ የቅርብ እና የሩቅ ጠላቶች ከሀገር ውስጥ ባንዳዎች ጋር ተባብረው ኢትዮጵያን ለመበታተን መሄድ እስከሚችሉት ድረስ ተጉዘዋል። በተለይም ዘመን አመጣሾቹ የኢትጵያ ጠላቶች በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ በመቆም ጉዞዋን ለማደናቀፍ በብዙ ደክመዋል። ጠንካራ ተቋማትን በማጠልሸት የኢትዮጵያን የእድገት ጉዞ ለማሰናከል ከጠላት ጋር አብረው ትውልድ ይቅር የማይለው ደባ ፈጽመዋል።

የውጭና የውስጥ ጠላቶች በአንድነት በማህበር ለሀገሪቱ መደከምና በሂደትም መፈራርስ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚሉትን ኃይል በማደራጀት፤በማስታጠቅና በማሰልጠን ታሪካዊ ጠላትነታቸውን በገሃድ ሲያስመሰክሩ ነሮዋል።

እነዚህ የውጭና የውስጥ ጠላቶች የዚህን ኩሩ ሕዝብ የዘመናት ዕሴቶች ለመናድ ከመሯሯጣቸውም በሻገር የሀገሪቱ መሰረት የሆኑ ተቋማት እንዲዳከሙና አለፍ ሲሉም እንዲከስሙ በብዙ ሰርተዋል። ሆኖም በጠንካራ አመራርና በኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ጥረት ተቋማቱ ከሀገር ውስጥ አልፈው ለሌሎች ሀገራትም አለኝታ በመሆን የድል አክሊል ተጎናጽፈዋል።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## ቲያጥሮን ምን በሳው?

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ቲያጥሮንን የበላ፣ ቲያትርን የነከሰ ጥርስ መኖሩ እርግጥ ነው። ውስጥ ውስጡን ደግሞ ጥቁር ሀሩንም ሆነ ወርቃማውን ቲያትር ሸበት ወሮታል። በሆነ ዘመን ላይ ደግሞ ቲያጥሮንን አስረክበን ቲያትርን ተቀብለናል። የተቀበልነውም በሽበት ተወሮ ከአናቱ ላይ ችፍፍ ብሏል። የጥቁር ዞማው በነጭ ሽበት ተለውጦ፣ ከጀርባ በወገብ አልፎ ተነስንሷል።

ቲያጥሮንም ቲያትር ነኝ ሲል ራሱን ከዷል። እና አሁን የምንመለከተው የኛ ቲያጥሮን ወይንስ የእነርሱ ቲያትር... ለዚሁ ምላሽም ከዕለታት በአንዱ ቀን የቀጠሮዬን ሰዓት ተጠባብቄ ወደ ጸሀፊ ተውኔትና ባለቅኔው አያልነህ ሙላት ዘንድ አመራሁ። አራቱን የመኖሪያ ቤቱን ደረጃዎች ሳለከልክ ወጥቼ ከማማው ቢሮው ላይ አገኘሁት። ከቲያጥሮን እስከ ቲያትር ብዙ ቢለኝም ለመጻፍ የቻልኩት ግን ጥቂቷን ብቻ ነው።

ከዚሁ የቲያትር ፎቴ ላይ ፊቱ ቁጭ ብዬ ገና በጥያቄ ስጀምር ነበር፤ “ቲያጥሮን የሚል የግእዝ ቃል እንዳለን ታውቃለህ?” ሲል ጥያቄዬን በጥያቄው አከናነበው። እርግጥ ነው አብዛኛዎቻችን ቲያትርን እንጂ ቲያጥሮንን አናውቅም። ለተራው ቀርቶ ለምሁራኑም የቸገረ ዓይነት ነው። ቃሉ የግእዝ ሲሆን በብዙ ጥንታዊ የብራና ጽሁፎች ውስጥም እናገኘዋለን። ትርጉም ካሉም ዛሬ “ቲያትር” ለምንለው የተውሶ ቃል አባት ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። አያልነህም ከማያቆርጠው ጥልቅ ጥያቄው ጋር ቀጠለ፤ ”ቲያትር ሳይኖር ቲያጥሮን ከየት መጣ? እስካሁን ይህን እንኳን ለመተርጎም አልቻልንም። ...ስለዚህ መጀመሪያም ቲያትር (ቲያጥሮን) ነበረን።

ላሊበላን ያህሉን ሥርቶ፣ ላሊበላ የሚባሉ አዝማሪያንን፣ አልቃሾችን...በሰበሰበ የዛግዌ መንግሥትና ማኅበረሰብ ቲያትር አልነበረም ማለት አይቻልም። የጎንደርን ሕንጻዎች ብንመለከት በውስጥ የቲያትር አዳራሽ፣ የቲያትር መድረክ አለ...” በማለት በወኔ በታጀበ አንደበቱ ገለጻልኝ። ያለው እውነት ነበር። እሳት ባልነደደበት አመድ አይታይምና ቲያትር ሳይኖር ቲያጥሮን የሚል የግእዝ ቃል ባልኖረን ነበር። ነገር ግን፤ “ቲያጥሮን”ን በጅብ ይሁን በቁማር የተበላን ዕለት ነበር ቲያትርን በማስተዛዘኛነት የተቀበል ነው። ተቀብለንም ዛሬ ላይ ቲያትር መቶ ዓመት ሞላው ስንል ከተበላን እንጂ እንደ አዲስ ከተዋወቅነው ከመሰለን ተሳስተናል። በየዓመቱ የምናከብረው የቲያትር ልደትም ቢሆን የእነርሱ እንጂ የኛ አለመሆኑን ልብ ይለዋል።


“ቲያትር መቶ ዓመት ሞልቶታል እንላለን፤ ግን የፈረንጅ እንጂ የኛ አይደለም። በቲያትር መድረክ ላይ የምንጠቀማቸው ነገሮች የኛ አይደሉም። በብሔር ብሔረሰቦች ላይ የተገነባ ነገር የለንም።”

ታዲያ ይህ ሁሉ እያለ ኢትዮጵያዊ ቲያትር አለ ለማለት ይቻል ይሆን? ኢትዮጵያዊ ቲያትር ስንልስ... እዚህ ጋር ቲያትር የሚለው ቃል ፈረንጂኛ በመሆኑ ሳይሆን ፈረስ ያለ ኮርቻ አይጋለብምና ይህን ቃል ስንረከብ አብረው የገቡ ነገሮች በመኖራቸውም ጭምር ነው። ጸሀፊ ተውኔት አያልነህ ቀደም ሲል ያነሳው ሀሳብ ነበርና አሁንም ለጥያቄው ሌላ ጥያቄ አከለ። “ለመሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ ኢትዮጵያዊ ቲያትር የምንለው በአማርኛ ስለተሠራ ነው?...” የሚል ጥያቄያዊ ምላሽ የጫነውን ጣል በማድረግ “የኔ ቲያትር ተተርጉሞ በእንግሊዝም ሆነ በጣሊያን ሀገር ታይቷል... እና ታዲያ በእንግሊዝኛ ስለተሠራ ቲያትሩ የእንግሊዝና እንግሊዛዊ ሆነ ማለት ነው? ... አይደለም!” ከዚህ በመቀጠልም ኢትዮጵያዊ ቲያትር ልንል የምንችለው ከቱባው ባህሏ ጋር ራሷኑ ኢትዮጵያን የሚመስል መሆን እንዳለበት አስቀመጠ። ኢትዮጵያ ግን መልኳ የማን ነው? በማንስ እንመስላት? ...ከሳለው መልክና ምስል በኋላ፤ በቲያትር ውስጥ ይህን መልክ ያጠለሹት ነገሮችንም አንስቷቸዋል።

የዚህ አንደኛውና ዋነኛው ችግር የሚመዘዘውም ቲያጥሮን ከስሞ ቲያትር መለምለም ከጀመረበት ጊዜ ነው። በልምላሜው ማግስት ከእኛነት ባህር እየተሻገርን ወደ እነርሱነት መትመም ጀምረን ነበር። ለዚህ ማሳያ የኛ ከሆነው ይልቅ በእነ ሼክስፒርና ፑሽኪን ቲያትሮች ተከትበን ነበር። በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሳይቀር የቲያትር ትምህርት ቤቶች ቢኖሩም ትምህርቱ ግን የእንግሊዝኛው ግልባጭ ትርጉም፣ የእነ ሼክስፒር ሀ ሁ ነበር። በእኛው አማርኛ የእነርሱን የቲያትር ካልኩሌሽን ነበር የምናጠናው። የቲያጥሮንን ባንዲራ ቀደን፣ የቲያትርን ዓርማ ከልባችን ላይ ሳይቀር ሰቅለነዋል። እናም እንደነበረው አቀባበላችን እና ትምህርታዊ የቲያትር ሥርዓታችን ቢሆን ኖሮ፤ ጥያቄው ኢትዮጵያዊ ቲያትር አለ ወይ? ብቻ ሳይሆን ነበር ወይ? እንድንል ጭምር የሚያስገድደን ነበር። ዳሩ እንዲህ ቢሆንም፤ በየዘመናቱ የኢትዮጵያን የቲያትር ጽላት ተሸክመው እዚህ ባደረሱ የቲያትር ባለሙያዎች እና መሰሎቻቸው ብርታት “የለም!” እንዳንል አድርገውታል። መሠረቱ በተናወጠው የእሳት ባህር ላይ እየቀዘፉም ቢሆን በቲያትሩ ውስጥ ኢትዮጵያዊነት እንዳይጠፋበት መስዋዕትነት ከፍለዋል። በልዩነት የምናመሰግነው ዘመንና በልዩነት የምናመሰግናቸው የቲያትር ጠቢባን መፈጠራቸውም እንዲህ ባለው ውስጥ ነው።

ያለፈው ተከድኖ ይብሰልና ከዚህ ሁሉ ማዕበል ውስጥ ሆኖ ወርቃማ የቲያትር ዘመን ነበር ስለምንላት ጉዳይም እናንሳለት። ጉዳዩ ማንንም በክርክር የሚያካርር አይደለም። አሁን እዚህ ሆነን በቲያትር ሽበት የተወረርን የሚመስለን ቲያትር ድኩማን ሁሉ፤ ዞረን ወደኋላ ብርቱ ወጣት የነበርንበትን እየናፈቅን፣ በጉብዝናችን ወራት በትዝታ ሽበታችንን እንደምናሽ እርግጥ ነው። ታዲያ ያን ትዝታ በውስጡ ሆነው ለኖሩት ለእነ አያልነህ ሙላትስ የኛ እውነት የእነርሱም ሀቅ፣ የኛ ትውስታ የእነርሱም ትዝታ ይሆን? እኛ ወርቃማ በምንለው ውስጥ እነርሱ ነበሩ። የነበሩ እነርሱስ ወርቃማ የሚሉት የትኛውን ነው? “አዎን ወርቃማ ዘመን ነበር...አብዮት የሚባለው ነገር ሲመጣ በጊዜው ብዙ ሕዝብ አልቋል። ብዙ ወጣትም ተቀጭቷል። ነገር ግን በጥበቡ ዓለም ውስጥ ሰላማዊ የሚባለው ጊዜ ነበር። ቀደም ሲል በዘውዱ ሥርዓት የነበሩትም ያለምንም ልዩነት ቀጥለዋል። አዳዲሶችም ወጥተው ሁሉም በአንድነት ተቀነባብሮና ተዋህዶ መሥራት ጀመረ። ...እንደ ጋሽ ጸጋዬና አቶ መንግስቱ ለማም ይጽፉና ይጠይቁ ነበር። ሌሎች ብዙዎችም ነበሩ። ሁላችንም የምንሠራው በአንድነት ተዋህደን ስለነበረ ያ ነገር ጥንክሬ ሆኖነናል። የቀደመውና አዲሱ በሚገባ ስለተዋሃደም ወርቃማ ዘመን ለመባል በቅቷል” ይላል ጸሀፊ ተውኔቱ አያልነህ ሙላት። እንደ ብዙዎች እሳቤም ወርቃማው ዘመን ማለት ብዙዎች የሚጠቅሱትን ያን 70ዎቹን ነበር።

በጊዜው የኛ ዳግማዊ ቲያጥሮን ባይወለድም እንደ ቲያትር ግን ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍ ብለው እንዲታዩ ከመስዋዕትነት ጋር ቆመዋል። “ማን ይናገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ” እንዲሉ አያልነህ ራሱ ከወርቃማው ዘመን ባለወርቆች አንዱ ነበር። ቲያትር የሕዝብን እንባ አባሽ፣ ቲያትር የሀገር ሰላም ፈጣሪ፣ ቲያትር ሕዝብን አጽናኝ፣ ቲያትር መሪን መካሪ ካልሆነ ምኑን ቲያትር ሆነ? የሚል ውስጣዊ መርህ ያላቸው ይመስል ነበር። በእርግጥም መሆን የነበረበትም እንዲያ ነው። በዚህ ወርቃማ ቲያትር በመሥራት ፍጥጫ ውስጥ ከፊት ከነበሩት መካከል ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድኅን፣ መንግሥቱ ለማ፣ ጸሀፊ ተውኔት አያልነህ ሙላትን ጨምሮ ጥቂት አውራዎች ነበሩ። ያኔ መጀመሪያ ላይ አያልነህ ሙላት 3ኛ ዲግሪውን ሊማር ራሺያ ገብቶ ነበር። “ትምህርቴን ልጨርስ አካባቢ ጋሽ ጸጋዬ ወደ ራሺያ መጥቶ ነበርና ካልመጣህ ሲል ጎትቶ ይዞኝ መጣ። እኔ ከመምጣቴ ቀደም ብሎ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ። ሲመለስም ጽፎ አዘጋጅቼው የነበረውን ‘እሳት ሲነድ’ የሚለውን ተውኔት ተሸክሞ መጣ። አባተ መኩሪያን አዘጋጅ፣ ገብረ ክርስቶስ ደስታን ደግሞ በመድረክ ዲዛይን፣ በጣም የታወቀውን ተፈራ አቡነ ወልድን ደግሞ በሙዚቃ አድርጎ እኔም በሌለሁበት ቆንጆ ሙዚቃዊ ተውኔት አድርጎ ሠራው” በማለት የሁለቱን መጀመሪያ አያልነህ ያስታውሳል። እሳቱም ደህና ይነድ ጀመረ። ከእነዚሁ ምሰሶዎች መካከል አያልነህ ከሎሬት ጸጋዬ ገ/መድኅን ጋር የበለጠ ትስስር ነበረው። ወርቃማውን ዘመን ለመሥራት ከከፈሏቸው መስዋዕትነቶችም፤ አንደኛው ሁለቱንም በአንድ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ከአንድ እስር ቤት፣ ከአንድ ክፍል ውስጥ አገናኝቷቸዋል። “እኔና ጋሽ ጸጋዬ ሁለታችንም የባህል ሚኒስትር ሠራተኞች ነበርን። እርሱ ቋሚ ተጠሪ፣ እኔ ደግሞ የቲያትር ጥበባት ድርጅት ኃላፊ ነበርኩ። በአንድ በጻፍኩት ቲያትርም በጣም ከባድ የሆነ...በደርግ መቃብር ላይ ሕዝባዊት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ትገነባለች... (ሻጥር በየፈርጁ) በሚለው ቲያትር ምክንያት ታሰርኩ። ጸጋዬን ደግሞ ሰበብ ፈልገው አንድ የደርግ አባልን ተሳድበሃል በማለት በአንድ ቀን ሁለታችንንም ወስደው እስር ቤት አስገቡን” ሲል፤ ካወሳው ውስጥ አንዱ ነበር።



ፀሐፊ ተውኔት አያልነህ ሙላት፣

በዚሁ መንደርደሪያ ወደ ቁጥቋጧው የቲያትርና ፖለቲካ ጋራ እንሻገር። ከቲያጥሮን መሰወር ወዲህ በሀገራችን ቲያትር አንገት ላይ ከቆሙ ነገሮች አንዱ ፖለቲካው ነበር። አንድም በፖለቲካ ተጨፍልቋል። ሁለትም በፖለቲካው ተረስቷል። በቀደሙት በዘውድና በደርግ ከበድ ባለ የሳንሱር ቡጢ ቢደቆስም እስከ ቤተ መንግሥት ድረስ ከፍ ያለ ቦታ ነበረው። በትንሹ ለማሳያነት...መሪዎቹ ሳይቀሩ በየቲያትሩ ምረቃና ልዩ ዝግጅት ላይ እየተገኙ ኋላም ባለሙያዎቹን ሸልመውና አበረታተው ይወጡ ነበር። ወዲህ ቀረብ ስንል ደግሞ የፈነዳው አብዮት ከከሰመ ወዲህ ውስጥ ውስጡን ስውር መርፌዎች ቢኖሩበትም ከላዩ ላይ የተጫነው ሳንሱር ግን ሊነሳለት ችሎ ነበር። ችግሩ ግን ጭነቱን እንዳነሱለት በል ደህና ሰንብት ተብሎ በዚያው ተረሳ። አትድረስብኝ! አልደርስብህም! ዓይነትም መስሎ ታየ። የቲያትሩ ቅዝቃዜና የሚያንሰፈስፍ ብርድ የሚጀምረውም ከዚሁ ነው። ይህንን በተመለከተም አያልነህ ሙላት ያነሳው ሀሳብ እጅግ ሰፊና ጥልቅ ቢሆንም በትንሽ በትንሹ መቀንጨቡ የግድ ነውና ካለውም...

“በመጀመሪያ ደረጃ እኛ ኢትዮጵያውያን ቀድሞ ያነበረብን ከባህላችን ውጭ የሆኑ ነገሮችን ተላምደናል። በመቀጠል ቲያትሩም ሆነ ኪነ ጥበብ ከፖለቲካ ውጭ የሚራመድ አይደለምና ፖለቲካው ሊመራውና ሊደግፈው ይገባ ነበር። ነገር ግን...በዚህም ምክንያት ኪነ ጥበብን ለኪነ ጥበብ የሚለው እሳቤ ይከሽፋል። ... ኪነ ጥበብን ያልያዘ መንግሥት፣ በኪነ ጥበብ ያልተዋቀረ መንግሥት፣ የትም ሊደርስ አይችልም። አሁን አይደለም ትናንትና እንኳን አዝማሪውም ሆነ ሌላው አድዋ ድረስ ዘምቶ፣ በኪነ ጥበብ ተዋግቶ እያዋጋባት የመጣች ሀገር ናት። መንግሥትም ቢሆን እነዚህ ምን አሉ? እያለና የእነርሱን ቃል እየሰማ ነበር የሚሠራው። አሁን እዚያ አካባቢ ያሉ ነገሮች በሙሉ ትኩረት ተነፍጓቸው ቀስ በቀስ ፖሊሲ አልባ ሆነው ይታያሉ” የሚል ነበረበት። ኪነ ጥበብ በፖለቲካው ሥርዓት ውስጥ ፖሊሲ አልባ ሆኖ መሰንበቱን በተመለከተ በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የኪነ ጥበብና ስነ ጥበብ ዘርፍ ኃላፊዋ ክብርት ነፊሳ አልማህዲ በአንድ ወቅት ሲሉ የሰማሁትን አስታወስኩ። “በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ኪነ ጥበብ የሚመራበት የራሱ የሆነ ፖሊሲ ሊኖረው የግድ ነውና ይህን ችግር ለመፍታት ሕገ ደንቦችን አርቅቀን ለማጸደቅ በመሥራት ላይ ነን” ሲሉ ነበር የተናገሩት። ይህ እውን ቢሆን በኪነ ጥበቡ ቅርጫት ውስጥ ላለው ቲያትርም እፎይታ ነበር። ካለፈው ወርቃማ ዘመን ልንወስደው የሚገባ አንድ ነገር አለ። ይኸውም ሙያውን በሙያው ላለ አዋቂ መስጠትን ነው። ለአብነትም ዛሬም ድረስ የምናወድሳቸው እነ ሎሬት ጸጋዬ ገ/ መድኅንና እነ ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌን የመሳሰሉትን ፈርጦች ብንመለከት በፖለቲካው ውስጥም ትልቅ ሚና የነበራቸው ናቸው። በሥሩት ትልቅ ድልድይ ከፖለቲካው ጋር እንዲተያይ አድርገው ጉልበት ፈጥረውለታል። ዘርፉ የሚያስፈልገውን ያውቃሉና ከፖለቲካው ለኪነ ጥበብ የሚገባትን ቆርሰው ሲሰጡ ነበር። ድልድዩን ሠርተው ያን ዘመን አሻግረውታል። ለቲያትር ውድቀት አንደኛው ምክንያት ምናልባትም የዚህ ድልድይ መሰበር ይመስላል።

የሲኒማ ቤቱ ግዙፍ ጥላ በቲያትር ቤት አናት ላይ አጥልቶ ይሆን? እንደ አንድ ታዛቢ ምናልባትም እነዚህ ነገሮች ይታያሉ...አብዛኛው የቲያትር ባለሙያ ፊቱን ወደ ሲኒማው አዙሯል። የቲያትር ተመልካቹም ምርጫውን በፊልሞች ላይ አድርጎ ቲያትር ቤቱን አራቁቶታል። ዘመናዊነት ያመጣው ቴክኖሎጂ ደርሶ ከቲያትር ላይ ፊቱን አጥቁሯል። ስለእነዚሁ ሁለት ነገሮችስ አያልነህ ሙላት የሚለው ምን ይሆን...”በቲያትሩ ጠንከር ያሉ ጉዳዮች ቢሠሩ እንደኔ የፊልሙ ጉዳይ ለቲያትር የሚያሰጋ አይመስለኝም። በቲያትሩ ከመጀመሪያውም በተለያዩ ትላልቅ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ከቲያትር ዝግጅት አንስቶ ያስተምራሉ። ፊልም ግን ምናልባት በአንዳንድ የግል ተቋማት ውስጥ ካልሆነ በስተቀር በተለይ መጀመሪያ ላይ ምንም አልነበረውም። እየተሠራ ያለውም በቲያትር ቤት ዳይሬክተሮች ነው። በሲኒማውም ቢሆን አዲስ ነገር ልናይ አልቻልንም። ...እናም ኢትዮጵያን የሚሸት ነገር ማምጣት እስካልቻልን ድረስ ቲያትር በፊልም እየተዋጠ ነው ብንል ለኔ ምንም ልዩነት የላቸውም” ይላል። ሆኖም ሲኒማው ላይ ብቻ ከማተኮር ባለሙያዎቹ ባሉበት ቲያትር ውስጥ ሆነው ትልቅ ነገር መሥራት ይኖርባቸዋል ሲልም ተናግሯል። ሲኒማውም ከቲያትር ጋር እኩል ጠቀሜታ አለውና መዘንጋት የለበትም።

አሁንስ በዚሁ እንቀጥል? ወይንስ ዳግማዊ ቲያጥሮንን እናንግሥ? “አሁን ዋናው ኃላፊነት ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ነው። ፈረንጅ የሰጠንን ዝም ብሎ ማስተማር ሳይሆን ወደኛ መመለስ አለብን። የራሳችን የሆኑ ጥናትና ምርምሮች ያስፈልጉናል። በቲያትር የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ሀገር በቀል የነበረው ነገር ጠፍቶ በባዶ መሬት ላይ ነው የበቀልነው። የብሔር ብሐረሰቦችን ባህል መሠረት አድርገን እዚያ ላይ ነው ዘመናዊነት መብቀል ያለበት። አሁን እኮ እኛ የፈረንጅ ተቀጢላዎች ነን። አያልነህ ሙላት ምናምን የምትለው.. ደራሲ ምናምን የምትለው ስለፑሽኪን ያወራሃል። ስለ ሼክስፒር ያወራሃል። ስለ ዶስኮቭስኪ ያወራሃል። ...ስለማንኛውም ቢሆን ያወራሃል። ነገር ግን ስለ እማሆይ ገላነሽ፣ ስለ አይናማው ጎሹ፣ ስለ ሼክ ጅብሪል ለሦስት ደቂቃ ብቻ ንገረኝ ብትለኝ አላውቅም። ከፈረንጅ ሊቅ የተማርነውና የምንማረው ምን ያህል ደንቆሮ እንዳደረገን ተመልከት እንግዲህ...” አለኝ አያልነህ ልቡ ተነክቶ አንድ ትልቅ ቁጭት ውስጥ እንዳደረ ያሳብቃል።

በስተመጨረሻ ሁሉን ጨርሰን ልሰናበተው ስል ቢሮውን ካካለለው መደርደሪያ ላይና ታች በረድፍ ተጠግጥገው ከሚገኙት መጽሐፍት መካከል የታጨቁትን ጥራዞች ተመልክቼ ቀልቤን ስለሳቡት እኚህ ምንድናቸው ስል ጠየቅኩት። ገና ያልታተሙ መጽሐፍትና መድረክ ያላዩ ቲያትሮች እንደሆኑ ከነገረኝ በኋላ አንድ በአንድ እያነሳ አስመለከተኝ። የሚገርም ብቻ ሳይሆን የሚያሳዝንም ጭምር ነበር። “ገና መድረክ ያላዩ...” በእርጅና ተረቶ ሊሞት ጥቂት ቀርቶት እርሱ ግን ገና ከ30 ዓመታት በኋላ የሚያፈራ ዛፍ ሲተክልና፣ ሰዎች ሲሳለቁበት የነበረው የአንድ ሰው ታሪክ ትዝ አለኝ። አያልነህም ስለቲያትርና ቲያትር ጽፎ ዛሬም በቃኝ ብሎ አልተቀመጠም። በግርምቴ መሀልም ቆይ ለምንድነው እየጻፍክ የምታከማቸው... ለምንስ ነው ቲያትሮቹ ያልተሠሩትና አሁን የማይሠሩት? ስል ነበር የጠየቅኩት ቀና ብሎ ከተመለከተኝ በኋላ ቅሬታ ባዘለ ድምጸት እንዲህ ነበር ያለኝ “እኔ እንደሆን ዕድሜዬ ገፍቷል። ምናልባት አንድ ቀን የገባው ትውልድ ሲመጣ ለእነርሱ ይሆናል” አለኝ። ከታላቁ ሰው ጋር የነበረኝ ትልቁ ንግግር ነበር።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## አካል ጉዳተኞችና የአረንጓዴ ዐሻራ ተሳትፎ

**አስናቀ ፀጋዬ**

በኢትዮጵያ 17 ሚሊዮን የሚጠጉ የተለየያ የአካል ጉዳት ያለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እንዳሉ ይታመናል። ይህም ሁለት አነስተኛ የቆዳ ስፋት ካላቸው ሀገራት የህዝብ ቁጥር ጋር ይስተካከላል። በኢትዮጵያ ካለው ከፍተኛ የሆነ የአካል ጉዳተኞች ቁጥር አንፃር ግን አካል ጉዳተኞች ልክ ሌሎቹ ዜጎች አመቺ የሆኑ መሰረተ ልማት፣ የትምህርት፣ ስራና ሌሎችም ማህበራዊ አገልግሎቶችን በበቂ ሁኔታ ተጠቃሚ ሲሆኑ አይታይም። ያም ሆኖ አካል ጉዳተኞች በማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ያላቸውን ተሳትፎ እየጨመሩ መጡ እንጂ አልቀነሱም።

አሁን አሁን ደግሞ ለአካል ጉዳተኞች ከሙአለ ሕፃናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ድረስ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ በመሆኑ ሁለንተናዊ ውጤት እየተመዘገበ መጥቷል። በተለይ ለአይነ ስውራንና ሌላም አይነት የአካል ጉዳት ላለባቸው ብቻ ታስበው የተገነቡ የቅድመ መደበኛና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጥራት ያላቸውና ከመደበኛው ተማሪ የሚበልጡ እንጂ የማያንሱ ተማሪዎችን በማፍራት ረገድ ቁልፍ ሚና እየተጫወቱ ይገኛል።

በተመሳሳይ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች አመቺ ሆነው በመሰራታቸውና እነርሱን አካተው እያስተማሩ በመሆኑ በተማሪዎቹ ውጤት መሻሻል ላይ ትልቅ ለውጥ መጥቷል። ይህም ለውጥ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ታይቷል። ይህንንም የከተማ አስተዳደሩ የ2016 ዓ.ም እቅድ አፈፃፀሙን ባቀረበበት ወቅት አስታውቋል።

በሌላ በኩል በቀዳማዊ እመቤት ዝናሽ



አካል ጉዳተኞች በአረንጓዴ ዐሻራ ንቁ ተሳትፎ አድርገዋል፤

ታያቸው አነሳሽነትና በሌሎች የረድዔት ድርጅቶች የተገነቡ የአይነ ስውራን አዳሪ ትምህርት ቤቶችም የአካል ጉዳተኞችን የትምህርት ተደራሽነትና ጥራት ያረጋገጡና ለነገዋ ኢትዮጵያ ከሌላው ዜጋ እኩል በሁለንተናዊ መልኩ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ናቸው። እንዲያም ሆኖ ግን በኢትዮጵያ ካለው የአካል ጉዳተኞች ቁጥር አንፃር ይህ ጅምር እንጂ ፍፃሜ አይደለም። አካል ጉዳተኞችን በሁለንተነዊ መልኩ ተጠቃሚ ለማድረግ አሁንም በርካታ ስራዎችን በመንግሥትና በሁሉም ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት መስራት ይጠይቃል።

ከዚህ ባለፈ የአካል ጉዳተኞች የማህበራዊና ሀገራዊ ጥሪ ተሳትፏቸውም ቀላል የሚባል አይደለም። ከዚህ በፊት አካል ጉዳተኞች በተለያዩ ሀገራዊ ጥሪዎች ላይ ያላቸውን ንቁ ተሳትፎ በሚገባ አሳይተዋል። በዓባይ ግድብ ግንባታ የገንዘብ፣ እውቀት፣ ጉልበትና ሌላም አስተዋፅኦ አድርገዋል። እርዳታ ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችም የገንዘብና የአይነት ድጋፍ አድርገዋል። በሌሎችም ህዝብን አንድ በሚያደርጉ ሀገራዊ ጥሪ ተሳትፈዋል።

አካል ጉዳተኞች በዘንድሮ የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሀ ግብርም በነቂስ ወጥተው አረንጓዴ ዐሻራቸውን አሳርፈዋል። አካል ጉዳተኞች በዘንድሮ የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሀ ግብር ለመሳተፍ ዝግጅታቸውን ቀድመው ነበር የጀመሩት። በዚህ ዓመት በመላው ሀገሪቱ ለስድስተኛ ጊዜ እየተከናወነ ባለው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር 7 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞች ለመትከል ታቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል። በዚሁ መሰረትም አካል ጉዳተኞች በዚህ የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሀ ግብር በንቃት ተሳትፈዋል።

በዘንድሮው የአንድ ጀንበር የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር 600 ሚሊዮን ችግኞች የተተከሉ ሲሆን፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመገኘት መርሀ ግብሩን አስጀምረዋል፤ አረንጓዴ ዐሻራቸውንም አኑረዋል። በመርሀ ግብሩ ከልጅ እስከ አዋቂ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች በንቃት እንዲሳተፉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ባቀረቡት አካል ጉዳተኞችም ጥሪውን ተቀብለው በመርሀ ግብሩ ተሳትፈዋል።

በዕለቱ አዋቂዎች በነፍስወከፍ ከ20 በላይ፣ ታዳጊዎች ከ10 በላይ ችግኝ በመትከል ለነገ ሀገር ተረካቢዎች የምትመች ሀገር ለማስረከብ የሚደረገውን ጥረት በማገዝ ኃላፊነታችንን እንወጣ ባሉት መሠረት የተለያዩ የአካል ጉዳት ያለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 በተዘጋጀው ቦታ በመገኘት አረንጓዴ ዐሻራቸውን አሳርፈዋል።

የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን ዋና ዳይሬክተር አቶ አባይነህ ጉጆ እንደሚሉት፣ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ፌዴሬሽኑ በንቃት እየተሳተፈ ይገኛል። ፌዴሬሽኑ አባላቱን በማስተባበር በዘንድሮው የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሀ ግብር በንቃት ተሳትፏል። ለዚህ ተሳትፎም ፌዴሬሽኑ ከአባላቱ ጋር በመሆን ከወራት በፊት ቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል።

በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 በተዘጋጀው ቦታ የችግኝ ተከላው የተከናወነ ሲሆን፤ በመርሀ ግብሩ 17 ሺህ አካል ጉዳተኞች ተሳትፈዋል። ችግኝ ከመትከል በተጨማሪ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የእንክብካቤ ስራ ለመስራት እቅድ ተይዟል። በቀጣይም አካል ጉዳተኞች ከአንድ ጀንበር የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር በተጨማሪ በቀጣዩ አመትም በዚሁ መርሀ ግርብር በመሳተፍ አረንጓዴ ዐሻራቸውን በማሳረፍ ሀገራዊ ተሳትፏቸውን አጠናክረው መቀጠል አለባቸው።

# ዓለም አቀፍ

## ደቡብ አፍሪካዊው ቢሊየነር ዳንጎቴን በመብለጥ የአፍሪካ ቁጥር አንድ ሀብታም ሆነ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ደቡብ አፍሪካዊው ቢሊየነር ዳንጎቴን በመብለጥ የአፍሪካ ቁጥር አንድ ሀብታም ሆነ።

ደቡብ አፍሪካዊው ቢሊየነር ጆናታን ሩፔርት ናይጄሪያውን ባለሀብት አሊኮ ዳንጎቴን በመብለጥ የአፍሪካ ቁጥር አንድ ሀብታም መሆኑን የብሉምበርግ ቢሊየነርስ ኢንዴክ መረጃ ያመለክታል።

ሩፔርት ካርቴር እና ሞንትብላንክ የመሳሰሉ ብራንዶች ያሉትን እና በዓለም ግዙፍ ከሚባሉት የቅንጦት እቃ አምራች ኩባንያዎች ውስጥ አንዱ የሆነው የሪችሞንት ባለቤት ነው። የሩፔርት ጠቅላላ የሀብት መጠን ከ1 ነጥብ 9 ቢሊዮን ዶላር ወደ 14 ነጥብ 3 ቢሊዮን ዶላር ሲያድግ ከዓለም 147 ደረጃ እና ከዳንጎቴ ደግሞ 12 ደረጃዎችን ከፍ እንዲል አድርጎታል።

ብሉምበርግ እንደዘገበው ከሆነ፤ የናይጄሪያዊው ሀብት በ1 ነጥብ 7 ቢሊዮን ዶላር ቀንሶ አጠቃላይ ሀብቱ 13 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር ሆኗል። የዳንጎቴ ሀብት መጠን መቀነስ አብዛኞቹ ኩባንያዎቹ ያሉባትን የናይጀሪያን የኢኮኖሚ ፈተና የሚያሳይ ነው።

ዳንጎቴ ግሩፕ የተባለው የንግድ ድርጅታቸው በነዳጅ ማጣሪያ ኩባንያው በፈጠረው የምርት መዘግየት እና በአቅርቦት መዛባት ምክንያት በርካታ ችግሮች አጋጥሞታል። ሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ችግር ውስጥ ብትሆንም፣ ዳንጎቴ ባለፈው ጥር ወር



ጆናታን ሩፔርት

በፎርብስ መጽሄት ለተከታታይ 13ኛ ጊዜ የአፍሪካ ቁጥር አንድ ሀብታም ተብለው ነበር።

ነገርግን ብሉምበርግ በቅርቡ ያወጣው መረጃ ዳንጎቴ በአፍሪካ ሁለተኛ በዓለም ደግሞ 159ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጧል። ሩፔርት አጠቃላይ ሀብት የጨመረው የቅንጦት እቃዎች ዘርፍ ከፍተኛ አፈጻጸም በማሳየቱ ነው።

ሌላኛው ደቡብ አፍሪካዊ ቢሊየነር ኒኪ ኦፐንሂመር በ13.3 ቢሊዮን ዶላር አጠቃላይ ሀብት በአፍሪካ ሦስተኛ ሲሆን ግብጻዊው ባለሀብት ናሴፍ ሳዊሪስ ደግሞ በ9.48 ቢሊዮን ዶላር አራተኛ ሆኗል።

ብሉምበርግ እንደፎርብስ ሁሉ የዓለም ሀብታም ሰዎች ባላቸው አጠቃላይ ሀብት ላይ ሊኖር የሚችለውን እለታዊ ለውጥ ይከታተላል።

## ሦስተኛው የዓለም ጦርነት ከተጀመረ በአውሮፓ ብቻ እንደማይወሰን ሩሲያ አስጠነቀቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሦስተኛው የዓለም ጦርነት ከተጀመረ በአውሮፓ ብቻ እንደማይወሰን ሩሲያ አስጠነቀቀች።

ሦስተኛ ዓመቱ ላይ የሚገኘው የሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት መልኩን እየቀያየረ እንደቀጠለ ይገኛል።

ከ20 ቀን በፊት ዩክሬን ምዕራብ ሩሲያ በኩል ባለችው ኩርስክ ግዛት በኩል ያልተጠበቀ ጥቃት በማድረስ በርካታ መንደሮችን መቆጣጠሯ ይታወሳል።

ሩሲያ ጥቃቱ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በውጭ ኃይሎች ላይ የተፈጸመባት ጥቃት መሆኑን አስታውቃለች።

ከዚህ በተጨማሪም ከጥቃቱ ጀርባ ምዕራባዊያን ሀገራት ሰራሽ የሆኑ ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎች እንዳሉ ይፋ አድርጋለች።

የሩሲያ ውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጊ ላቭሮቭ በሞስኮ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ እንዳሉት፤ የዩክሬን ኩርስክ ጥቃት የሦስተኛው የዓለም ጦርነትን የሚቀሰቅስ ነው ብለዋል።

ሚኒስትሩ አክለውም "ምዕራባዊያን ለዩክሬን በሰጡት መሳሪያ ሩሲያን እንድትመታ በማድረግ በእሳት እየተጫወቱ ነው" ሲሉ ተናግረዋል።

"ሦስተኛው የዓለም ጦርነት ከተጀመረ በአውሮፓ ብቻ የሚያበቃ አይደለም" ያሉት ሚኒስትሩ ምዕራባዊያን ዩክሬን በመጠቀም ወደ ከፋ ውድመት እየመሩ ነው ሲሉም አስጠንቅቀዋል።

ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ዩክሬን በኩርስክ ለፈጸመችው ጥቃት ተገቢው ምላሽ ይሰጣል ማለታቸው ይታወሳል።

የዩክሬን ፕሬዚዳንት ቮሎዶሚር ዘለንስኪ በበኩላቸው፤ ከኩርስክ ጥቃት በኋላ በሰጡት መግለጫ፤ የሩሲያ ያ ሁሉ ዛቻ ምንም ነው ሲሉ ተናግረው፤ ምዕራባዊን ሀገራት ተጨማሪ ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

እንደ ሩሲያ ዕምነት ከሆነ ዩክሬን በሩሲያዋ ኩርስክ ግዛት ጥቃት የፈጸመችው በምዕራባዊን ሀገራት ጦር መሳሪያ፣ የሳተላይት መረጃዎች እና ሌሎች ድጋፎች ታግዛ ነው።

ሩሲያ ከ2022 ጀምሮ ሉዓላዊ ደህንነቷ አደጋ ውስጥ ከገባ የኑክሌር ጦር መሳሪያዋን እንድትጠቀም የሚፈቅድላት ሕግ እንዳላት ፕሬዚዳንት ፑቲን በተደጋጋሚ ማስጠንቀቃቸው ይታወሳል።



ሰርጊ ላቭሮቭ

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# በዝንጀሮ ፈንጣጣ በሽታ ዙሪያ ተገቢውን ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል

የአፍሪካ የበሽታዎች መከላከያና መቆጣጠሪያ ማዕከል (ሲዲሲ) በአህጉሪቱ የዝንጀሮ ፈንጣጣ የተስፋፋባቸው ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎን ጨምሮ ሌሎች ሀገራት ላይ ክትባት ሊሰጥ እንደሚገባ ማዕከሉ ማሳሰቡ፤ የዓለም ጤና ድርጅት የዝንጀሮ ፈንጣጣን የዓለም የጤና ስጋት ነው ሲል ማወጁ፤ የአፍሪካ የበሽታዎች መከላከያና መቆጣጠሪያ ማዕከል፥ ክትባቱ በቅርቡ መሰጠት እንዲቻል በአግባቡ ለማስቀመጥና ለመጠቀም መዘጋጀቱን መጥቀሱ ለዛሬ መጣጥፌ መነሻ ሆኖኛል፡፡

የዝንጀሮ ፈንጣጣ በሽታ በዓለም የጤና ድርጅት የሕብረተሰብ ጤና ስጋት መሆኑ ከተገለፀ ጀምሮ በሽታው ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ የቅድመ መከላከል ሥራ እየተሠራ ነው፤ በዚሁ መሠረት፥ በድንበርና በተመረጡ አካባቢዎች ላይ ቅኝት የማድረግ፣ የልየታ ሥራ፣ በሽታውን መመርመር የሚያስችል የቤተ-ሙከራ አቅምን የማሳደግ እንዲሁም የባለሙያዎችን አቅም የማጎልበት ሥራ እየተከናወነ ነው። የዝንጀሮ ፈንጣጣ በሽታ በ13 የአፍሪካ ሀገራት መከሰቱን በመግለጽ፥ እስካሁን በኢትዮጵያ በበሽታው የተያዘ ሰው አለመኖሩን የጤና ሚኒስትር ዶ/ር መቅደስ ዳባ አረጋግጠዋል፡፡

የዝንጀሮ ፈንጣጣ ተብሎ የሚታወቀው ኤምፖክስ በቫይረስ የሚመጣ በሽታ ነው። ምልክቶቹ ትኩሳትና ሽፍታ ሲሆኑ በበሽታው ከተያዙ ሰዎች ወይም ከተበከሉ ቁሳቁሶች ጋር በመገናኘት ሊተላለፍ ይችላል። በሽታው ብዙውን ጊዜ ለከፋ ባይሰጥም፣ ለሞት ሊዳርግ ይችላል። የመከላከያ እርምጃዎች በበሽታው ከተያዙ ሰዎች ጋር ንክኪን ማስወገድ እና ንፅህናን መጠበቅ ነው። ክትባቶች እና ሕክምናዎችም አሉት።

በተለያየ ምክንያት በሽታ የመከላከል አቅማቸው ደካማ ለሆነ፣ ለህጻናት፣ ለነፍሰ ጡር ሴቶችና የጤና እክል ላለባቸው ሰዎች ግን ሕመሙ ሊበረታና ሞትን ሊያስከትል ስለሚችል ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል። ከፍ ብሎ ለመግለጽ እንደተሞከረው የዝንጀሮ ፈንጣጣ የሚተላለፈው ከቁስልና ከሰውነት ፈሳሽ በሚፈጠር ንክኪ እንዲሁም የተበከሉ ቁሶችን በመጠቀም ስለሆነ ከወዲሁ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

አያድርገውና ወደ ሀገራችን ቢገባ የጤና አጠባበቅ ስርአታችን በወጉ ያልተደራጀና ብዙ የሚቀረው ከመሆኑ ባሻገር የሕክምና አገልግሎት ወይም የክትባት ተደራሽነት ውስንነት ስላለብን ፈታኝ ሊሆንብን ይችላል። ስለሆነም ወደ ሀገራችን እንዳይገባ እየተደረገ ያለውን ጥረት ማጠናከርና ተቋማዊ ማድረግ ይመከራል።

ሌላው ከበሽታው ጋር ተያይዞ የሚፈጠር መገለል በአእምሮ ጤና እና በማህበራዊ ደህንነት ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ስለሚችል፤ የተሳሳተ መረጃም በሕዝብ ዘንድ ፍርሀትን ጎንቁሎ የመከላከል ጥረቱን እንዳያስተጓጉለው እና የማኅበረሰብ ምላሾች ላይ ሳንካ እንዳይፈጥር ከወዲሁ ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራትን ማከናወን ይገባል። ስለ ዝንጀሮ ፈንጣጣ ምልክቶች፣ መተላለፊያ መንገዶችና እንዴት መከላከል እንደሚገባ ሳያሰልሱ ማስተማር ግድ ይላል።

ከሁሉም በላይ የጤና አጠባበቅ መሠረተ ልማትን ወይም የጤና አጠባበቅ ተቋማትን እና አገልግሎታቸውን የዝንጀሮ ፈንጣጣን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ዝግጁ መሆናቸውን አበክሮ ማረጋገጥ ያሻል። እንዲሁም የጤና ባለሙያዎችን ማሰልጠን፣ አስፈላጊ የሕክምና ግብዓቶችን ማዘጋጀትና የምርመራ አቅምን መፈተሽ፤ ለክትባት መዘጋጀት፤ ክትትልና ሪፖርት ማድረግ ያስፈልጋል።

በመከላከል ሒደት ውስጥ የማኅበረሰብ ተሳትፎን ማሳደግ፤ ዓለም አቀፍ ትብብር ማጠናከር ማለትም ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና ከጎረቤት ሀገራት ጋር በመተባበር መረጃን፣ ሃብትን እና ተሞክሮን አንሰላስሎ መጠቀም፤ ማንኛውንም ወረርሽኝ በፍጥነት ለመከላከልና ተጽዕኖውን በብቃት ለመቆጣጠር የአደጋ ጊዜ ምላሽ ዕቅዶችን ማዘጋጀት እና መተግበር በኢትዮጵያ ውስጥ የዝንጀሮ ፈንጣጣ የስርጭትን አደጋ ለመቀነስ እና የሕዝብ ጤናን ለመጠበቅ ያግዛል።

የአፍሪካ የበሽታዎች መከላከያና መቆጣጠሪያ ዋና ዳይሬክተር ጂን ካሴያ (ዶ/ር) ሰሞኑን እንዳስታወቁት፡፡ ከዚህ በፊት በቫይረሱ ያልተጠቁ ቡሩንዲን፣ ኬንያን፣ ሩዋንዳንና ዑጋንዳን ጨምሮ በትንሹ 13 የአፍሪካ አገሮች በወረርሽኙ ተጠቅተዋል፡ ፡ ከዚህ ቀደም በሽታው ባልነበረባቸው አገሮች በ2024 ብቻ 2,863 በቫይረሱ የተጠቁ ሕሙማን እንደተመዘገቡና ከእነዚህ ውስጥ 517 መሞታቸውን፤ የቫይረሱ ሥርጭት በከፋበት ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎን ጨምሮ፣ በአኅጉሪቱ ያሉ ተጠርጣሪ ሕሙማን ቁጥር በ2022 ከነበረው 7,146 እና በ2023 ከነበረው 14,957 ልቆ በ2024 ወደ 17,000 ከፍ ብሏል፡፡ ይህ የተጠናከረ የቁጥጥር፣ የላቦራቶሪ ምርመራና የንክኪ ክትትል ሥርዓት በሌለበት የተገኘ በመሆኑ ቁጥሩ ከዚህ ሊልቅ እንደሚችልም ይገመታል ብለዋል፡፡

አሁን የተከሰተው የዝንጀሮ ፈንጣጣ ወረርሽኝ የጉዞ ገደብ ከሚጣልበት ደረጃ ባያደርስም፣ የአገሮችን ጥምረትና አፋጣኝ ምላሽ እንደሚሻ፤ እንደ ካስያ (ዶ/ር)፣ የዝንጀሮ ፈንጣጣ አኅጉሪቱ ከዚህ ቀደም ካስተናገደቻቸው ወረርሽኞች የተለየ አይደለም፡፡ በጤና ሥርዓት ውስጥ የተከሰተ ቀውስ በመሆኑ ግን በትብብር መሥራትን ይጠይቃል፡፡ ከግንቦት 2022 እስከ ሐምሌ 2023 ድረስ ቫይረሱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትኩረት የሚሻ ድንገተኛ የማኅበረሰብ ጤና እክል ተብሎ በዓለም ጤና ድርጅት ታውጆ ነበር፡፡ ሆኖም አፍሪካ በዚህ ወቅት ያስፈልጋት የነበረውን አስቸኳይ ድጋፍ አላገኘችም፡፡ በመሆኑም በዓለም አቀፍ ደረጃ የነበረው ሥርጭት ሲቀንስ በአፍሪካ እየጨመረ መጥቷል፡፡ ዓለም አቀፍ አገሮች አሠራራቸውን መቀየር እንዳለባቸና ከአፍሪካ ሲዲሲ ጋር በቅርበት በመሥራት ለአባል አገሮች ድጋፍ እንዲያደርጉም ቀሪ አቅርበዋል፡፡

በአፍሪካ የቫይረሱን ሥርጭት ለማወቅ በተሠራ ውስን ዳሰሳና በተገኘ ማስረጃ መሠረት ሁኔታው በዳሰሳው ግንዛቤ ከተገኘበት በበለጠ ከባድ ነው፡፡ የዓለም ጤና ድርጅት በ2022 ድንገተኛ የኅብረተሰብ ጤና እክል ብሎ ካወጀ በኋላ፣ የታማሚዎች ቁጥር ጨምሯል፡፡ የሕመሙ ሁኔታም ከባድ ነው፡፡ የኤች አይቪ ሕሙማንን ከማጥቃቱ ጋር ተያይዞም የሞት መጠን እየጨመረ ነው፡፡ የዝንጀሮ ፈንጣጣ በመጀመሪያ በሰዎች ላይ የታየው በዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ እ.ኤ.አ. በ1970 ነበር፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን ቫይረሱ በተለያዩ አገሮች ታይቷል፡፡ በዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ብቻ ከ15 ሺሕ በላይ በቫይረሱ ሲጠቁ 537 ደግሞ ሞተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ይህንን ጽሑፍ እስካጠናቀርንበት ዓርብ ነሐሴ 17 ቀን 2016 ዓ.ም. ድረስ በዝንጀሮ ፈንጣጣ (MPox) የተጠረጠረም ሆነ የተረጋገጠ ታማሚ እንደሌለ ጤና ሚኒስቴር አስታውቋል፡፡ የዝንጀሮ ፈንጣጣ (MPox) በሽታ በዝንጀሮ ፈንጣጣ ቫይረስ አማካይነት የሚመጣ ሲሆን፣ በወረርሽኝ መልክ ሊከሰት የሚችል በሽታ ነው፡፡ ትኩሳት፣ ራስ ምታት፣ የዕጢ ዕብጠት፣ የጡንቻና የጀርባ ሕመም፣ ሽፍታ፣ የቆዳ ቁስለት እንዲሁም የአቅም ማጣት ከበሽታው ምልክቶች መካከል ይገኙበታል፡፡ ልቅ ግብረ ሥጋ ግንኙነትን ጨምሮ ንክኪ የበሽታው መተላለፊያዎች ናቸው፡፡

ጤና ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ የኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩትና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የተለያዩ የኅብረተሰብ ጤና አደጋዎችን የቅድመ ዝግጅት፣ የቅኝትና የምላሽ እንዲሁም የድንበር ጤና ልየታና አገልግሎት ሥራዎችን የኅብረተሰብ ጤና አደጋዎች ማስተባበሪያና ምላሽ ማዕከል በማቋቋም እየሠራ መሆኑን ጠቁሟል፡፡ በተለይም ደግሞ በኬንያ አዋሳኝ ሦስት ክልሎች ማለትም በኦሮሚያ፣ በሶማሌና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች በሚገኙ የመውጫና መግቢያ ኬላዎች እንዲሁም በቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ከወትሮው በተጠናከረ ሁኔታ የቅኝትና የልየታ ሥራዎች እየተተገበረ ይገኛል ብሏል፡፡ በሽታው በቀጥታ ከሰው ወደ ሰው በንክኪ የሚተላለፍ እንደመሆኑ መጠን፣ ምልክቶችን የሚያሳይ ማንኛውም ሰው በአቅራቢያው በሚገኝ የጤና ተቋም ሪፖርት እንዲያደርግ፣ ወይም በ952 እና 8335 ነፃ የስልክ መስመር ጥቆማ እንዲያደርግ ሚኒስቴሩ ጥሪ አቅርቧል፡፡

ስለ ወረርሽኙ እየተሰጠው የሚዲያ ሽፋን እዚህ ግባ የማይባልና በመግለጫ ላይ የተንጠለጠለ መሆኑ ሊታረምና ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። የግድ ወረርሽኙ ሀገራችን መግባትና ሰዎችን መግደል መጀመር የለበትም። ለመከላከል በስፋት ማስተማርና መቀስቀስ ያሻል። በዚህ ከተግባባን አዘጋገቡ ከተለመደው አሠራር ወጥተው የማብራራት ጋዜጠኝነት መርህን (Explanatory Journalism) መከተል ይመከራል፡፡

የሲኤንኤን "Reliablel Source" አዘጋጅ ብራያን ስቴልተር በዚያ ሰሞን ብዙኃን መገናኛዎች በተለይ ዋና ዋናዎቹ የዩናይትድ ስቴትስ ቴሌቪዥኖች፣ ጋዜጦችና ሌሎች ማኅበራዊ ሚዲያዎች የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን እንዴት እንደዘገቡትና መዘገብ እንዳለባቸው ከሙያው ጎምቱዎች ዳን ራዘርንና ካርል በርኒስቲን፣ ከአንጋፋዎቹ የአሶሼትድ ፕሬስ (ኤፒ) ሳሊ ቡዝቤንን፣ የዎል ስትሬት ጆርናሉን ማት መሪ ጋር መክሮ ነበር፡፡ ይህ ተሞክሮ የዝንጀሮ ፈንጣጣ ወረርሽኝን ለመከላከል ቀምረን ልንጠቀመው ይገባል።

አንጋፋዋ የአሶሼትድ ፕሬስ ጋዜጠኛ ሳሊ ቡዝቤን ‹‹ወረርሽኝ የማብራራት ጋዜጠኝነት ጎልቶና ገዝፎ የሚወጣበት ትልቅ ሁነት ነው፡፡ (Pandemic is The Olympic of Explanatory Journalism) ብላለች፡ ፡ ኦሎምፒክ በአራት ዓመት አንድ ጊዜ የሚካሄድ፣ ከ200 አገሮች የተወከሉ እስከ 20 ሺሕ የሚጠጉ አትሌቶች የሚሳተፉበት፣ ለአሸናፊ አትሌቶች ከፍ ያለ ዕውቅና ከማስገኘቱ ባሻገር ለቀጣይ ስኬት መስፈንጠሪያ ስለሆነ፣ ለዝግጅቱ በብዙ ቢሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር የሚወጣበት፣ ከዓለም ዋንጫ ባልተናነሰ የስፖርታዊ ውድድሮች ሁሉ ቁንጮ ስለሆነ ነው እንግዲህ የማብራራት ጋዜጠኝነት አልፎ አልፎ ለሚከሰት ወረርሽኝ፣ ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች ዘገባ ፍቱን መድኃኒቱ ነው ያለችው፡፡ ለመሆኑ የማብራራት ጋዜጠኝነት ምንድነው?

ለአንባቢያን በሚገባ ቀላልና ግልጽ ዓረፍተ ነገር፣ እንግዳ የሆኑ ሐሳቦችንና ውስብስብ የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች የሚዘገቡበት የጋዜጠኝነት ዓይነት ነው፡ ፡ የብሩኪንግስ የኮሙዩኒኬሽን ተባባሪ ምክትል ፕሬዚዳንት ሪቻርድ ፋዋል፣ "Explanatory Journalism Cure the Internet?" በሚል ባስነበበን መጣጥፍ፣ የማብራራት ጋዜጠኝነት አንድን ጉዳይ ግልጽ፣ ቀጥተኛና ተደራሽ በሆነ አግባብ መዘገብ ነው፡፡ የዕዝራ ክሌንስን ቮክስ፣ የኒውዮርክ ታይምስ ‹‹ዘ አፕሾት››፣ የቡዝፊድና የብሉምበርጉ ኩይክቴክን በአብነት ይጠቅሳል፡፡ የማብራራት ጋዜጠኝነት በመረጃ ላይ የተመሠረተ ምክንያታዊ ዘገባ ለአንባቢያን ለማድረስ ከማገዙ ባሻገር፣ እግረ መንገድ የኅትመት ጋዜጠኝነትን መሠረታዊ ኃላፊነትን ለመወጣት ዕገዛ እንደሚያደርግ ያስረዳል፡፡

ሌላው የዚሁ ተቋም ከፍተኛ ተመራማሪ ቶማስ ኢ. ማን ዛሬ እንደ አዲስ የማብራራት ጋዜጠኝነት እየተቀነቀነ ቢሆንም፣ እ.ኤ.አ. ከ1985 ጀምሮ ፑሊትዘርን ያሸለመ የጋዜጠኝነት ዘርፍ መሆኑን ያስታውሳል፡፡ መረጃ ማዛባት በገነገነበት በዚህ የኢንተርኔት ዘመን እንደ ፈጣን መፍትሔም እየተወሰደ ይገኛል ይለናል፡፡ ቮክስ ከአምስት ዓመታት በፊት በዲዝኒላንድ ፓርክ የኩፍኝ ወረርሽኝ መቀስቀሱን ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ሁሉ በማሟላትና ግልጽ በሆነ ቋንቋ፣ ሙያዊ አገላለጾችን (ጃርገንስ)፣ ቀላል በሆነ ገለጻ በመተካትና መረጃ ሳያዛባ ያጠናቀረውን ዘገባ ፋዋል በምሳሌነት ይጠቅሳል፡፡

በዘገባው ኩፍኝ በተባለው አደገኛ ተላላፊ በሽታ በክትባት ላይ የተከፈተው የሴራ ዘመቻ የተነሳ ልጆቻቸውን የሚያስከትቡ ወላጆች መቀነስ፣ እንዲሁም ዓለም አቀፍ የሰዎች እንቅስቃሴ መጨመር ለወረርሽኙ በፍጥነት መዛመት አስተዋጽኦ እንደነበረው በአብነት ያነሳል፡፡ የማብራራት ጋዜጠኝነት የዜናዎችን ትክክለኛ መሆን አለመሆን ከማጣራት ባሻገር፣ በየደቂቃው የሚዥጎደጎደውን ዜና ከተዘገበበት ዓውድ አንፃር አንባቢ፣ አድማጭ፣ ተመልካችና ተከታይ በቀላሉ እንዲደርሰውና እንዲገነዘበው በማረቂያነት ያግዛል፡፡ በተጨባጭ መረጃና በአኃዝ የበለፀገ የጋዜጠኝነት ዓይነት ቢሆንም ለእውነት ወግኖ ከመሞገት ወደኋላ እንደማይል፣ ፖሊሲዎችን ከታሪካዊ ዓውዳቸውና ከአኃዛዊ መረጃዎች ጋር በማዋሀድ እንደሚያፍታታም ይገልጻል፡፡

የኮሎምቢያ ጆርናሊዝም ሪቪው (ሲጄ አር) ጋዜጠኛ አሌክሳንድሪያ ኔሰን "In a Pandemic, What is Essential Journalism?" በሚለው ጽሑፏ፣ የማብራራት ጋዜጠኝነት አሁን እንደምንገኝበት ዓይነት ክፉ ቀን ሲመጣ ጋዜጠኞች ጠቃሚ መረጃ በማሠራጨት ብቻ ሳይወሰኑ፣ መመርያ ሰጪ በመሆን ወደ ጋዜጠኝነት ጥንተ መሠረታቸው ይመለሳሉ፡፡ አድማጭ ተመልካቹ፣ አንባቢውና የማኅበራዊ ድረ ገጾቻቸው ተከታይ ምን ማድረግ? እንደሌለበት? መረጃና ዕርዳታ ሲፈልግ ማን ዘንድ መደወል እንዳለበት፣ ምን እንደሚፈልግ፣ የት መሄድ እንዳለበት አቅጣጫ ያመላክታል፡፡ በግል፣ በድርጅትና በመንግሥት ሚዲያዎች ስለዝንጀሮ ቫይረስ የሚዘገቡ ዜናዎች ምን ያህል የሚያብራሩ እንደሆነ፣ በእነዚህ አላባውያን አማካይነት መመዘን እንችላለን፡፡

ሻሎም ! አሜን።